# ዲቁና
## (ተግባራዊ ክርስትና)

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን
Ethiopian Evangelical
Baptist Church
2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG

ከቄስ ተፈራ ሙዘይን
ሲ/ር ኪርቱ ኒዩገሬን

**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ**
**በወንጌል ተልዕኮና ቲኦሎጊ መምሪያ**
**የዲቁና አገልግሎት ቢሮ**

አዲስ አበባ፤ 1998 ዓ.ም.

የመጀመሪያ ዕትም 1998 ዓ.ም.

አድራሻ:-
**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ**
**የዲቁና አገልግሎት ቢሮ**

ፖ.ሣ.ቁ. 2087
ስልክ : 011-550-7846
Email: diakonia@eecmy.org
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

መግቢያ ---------- 6

ምስጋና ---------- 10

ክፍል አንድ

1. ዲቁና ምንድነው? ---------- 11

1.1. የቃሉ ትርጉም ---------- 11
1.2. ዲቁና በመጽሐፍ ቅዱስ ---------- 13
1.2.1. ዲቁና በብሉይ ኪዳን ---------- 13

1.2.2. ዲቁና በአዲስ ኪዳን ---------- 17
1.3. ዲቁና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ---------- 21

1.3.1. ዲቁና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ---------- 25
1.3.2. ዲቁና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ---------- 26

1.3.3. ዲቁና በሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን ---------- 28

1.3.4. ችግረኞችን መርዳት በእስላም ---------- 29

1.4. ችግረኞችን መርዳት በማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ---------- 30

1.5. ሁለንተናዊ አገልግሎት ዲቁናና ልማት ---------- 31

የክለሳ ጥያቄዎች ---------- 34

## ክፍል ሁለት

2. የዲቁና አገልግሎት ስልጠናና አደረጃጀት---------------35
2.1. የሚናገለግላቸው እነማንን ነው?--------------------35
2.2. ችግረኞችን ለምን እናገለግላለን?--------------------39
2.3. ችግረኞችን እንዴት እናገለግላለን?--------------------46
2.3.1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች--------------------46
2.4. ስልጠናና አደረጃጀት--------------------------54
2.4.1. ያልተቀናጀና የተቀናጀ የዲቁና አሠራር-----------------54
2.5. የዲቁና አገልግሎት በገጠርና በከተማ--------------------56
2.6. ችግረኞችን ወደ ራስ መቻል መምራት------------------57
2.7. የዲቁና አገልግሎት የማን ኃላፊነት ነው?---------------58
2.7.1. ሥልጠና ለማ/ምዕመናን መሪዎችና ቋሚ አገልጋዮች-59
2.7.2. ሥልጠና ለምዕመናን----------------------------62
2.7.3. ሥልጠና ለዲቁና በጎ ፈቃድ አገልጋዮች------------ 63
የክለሳ ጥያቄዎች--------------------------------68

## ክፍል ሦስት

3. በዲቁና አገልግሎት ሊሰጡ የሚገባቸው ትኩረቶች-- -69
3.1. የሥራ ክቡሪነት--------------------------- ---69
3.1.1. ሥራ በብሉይ ኪዳን--------------------------69
3.1.2. ሥራ በአዲስ ኪዳን ----------------------------72
3.2. የሥራ ፈትነት ምክንያቶች-------------------------73
3.2.1 ሥራ ፈትነት የሚወገድባቸው መንገዶች--------------75
3.3. ዲቁናና የፈውስ አገልግሎት-----------------------76
3.4. ዲቁናና የማማከር አገልግሎት----------------------80
3.5. ዲቁናና የአካል ጉዳተኞች እንክብካቤ-----------------84
3.6. የአእምሮ እድገት ዘገምተኞች----------------------86
3.7. ዲቁናና ኤድስ-------------------------------87
የክለሳ ጥያቄዎች-------------------------------92

## ክፍል አራት

4. የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት በሕብረተሰብ መካከል------------93
4.1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕይታ---------------------------93
4.2 ሰብአዊ መብቶች---------------------------------- 98
4.3. የጾታና የሕጻናት መብቶች-------------------------104
4.4 ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ መሳተፍ
አለባትን?------------------------------------------107
የክለሳ ጥያቄዎች---------------------------------112
ዋቢ መጻሕፍት ------------------------------------ 113

# መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር የተመሠረተች የክርስቶስ አካል ናት:: ክርስቶስ ደግሞ የአካሉ ራስ ነው (ኤፌ. 5: 23):: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ታላቁ የወንጌል ተልዕኮን (ማቴ.28:18-20) ትዕዛዝ ተቀብላ ሕያው መልዕክት ለሰዎች ሁሉ በሁለመናዊ መልኩ ታስተላልፋለች:: ይህንንም ደግሞ በወንጌል ስብከትና *በተግባር መግለጡ* ተገቢ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ይህን የምታደርገው በቃል ስብከትና ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ በቂ አገልግሎት ለመስጠት ትምህርቱ በተግባር ላይ መዋል ስላለበት ነው:: ከዚህ እውነት በመነሳት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የሰውን ሁለመና ለማገልገል «ሁለንተናዊ አገልግሎት» በሚለው መርሆ አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ትገኛለች::

በሁለመናዊ ወንጌል ዓለምን መድረስ የምንችለው የሰዎችን ነፍስና ሥጋ በተግባራዊ ፍቅር ማገልገል የቻልን እንደሆነ ብቻ ነው:: የሰዎችን አካላዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ለማገልገል ሁለመናዊ ወንጌል ወሳኝ ነው:: ሁለመናዊ አገልግሎት ደግሞ እንደሚገባ ተግባራዊ የሚሆነው የዲቁናን አገልግሎት ተግባራዊ ማድረግ ስንችል ነው:: ምክንያቱም ዲቁና አገልግሎት የሰዎችን አካላዊና መንፈሳዊ ተግዳሮቶችን መቋቋም የሚቻልበት ብቸኛ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነው::

- የሰዎች የመንፈሳዊ ፍላጎቶች:- እግዚአብሔርን የማምለክና ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት የመኖር ፍላጎት ሲሆን፤
- አካላዊ ፍላጎቶች:- የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊ፤ የፖለቲካዊና ሥነ ልቦናዊ ፍላጎቶች፤እነዚህ ፍላጎቶች ሲሟሉ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር፤ ከራሳቸውና ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዲሁም ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የተስተካከለ ሊሆን ይችላል::

በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ሀገሮች የወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት የወንጌል አገልግሎት እየተካሄደ ነው:: የወንጌል ትምህርት፤ ስብከትና ዝማሬ እዲሁም ጸሎት አላነሰም:: የእግዚአብሔርም እጅ ተአምራትን ያደርጋል:: የምዕመናንም ቁጥር መጨመር ከጊዜ ወደ ጊዜ ይታያል:: ነገር ግን « ተግባራዊ የፍቅር እንቅስቃሴ» አይታይም::
አንድ ጊዜ አንድ ወንጌላዊ ስለአማኞች መንፈሳዊ ባሕርይ ጥናት ለማድረግ ክርስቲያን መሆኑን ሳይገልጥ ከአገር ወደ አገር በመዘዋወር

«በዚህ አካባቢ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉን? ካሉስ ምን ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ናቸው?» በማለት ቃለ መጠይቅ ያደርግ ነበር። ከሕዝቡ ያገኘው ምላሽ፤ አይጠጡም፤ አይሠክሩም፤ በሰው ላይ ክፋት አያደርጉም፤ ይጸልያሉ፤ ይዘምራሉ፤ እኛንም በልባችን ደስ ያሰኘን ሁሉ እንዳናደርግ ሊመክሩን ይፈልጋሉ። በአጠቃላይ የህግ ጠባቂዎች ይመስላሉ የሚል መልስ ነበር ያገኘው።

ነገር ግን ከጥናቱ ሊያገኝ የፈለገው፤ አማኞች የፍቅር ሰዎች ናቸው፤ ድሆችንና ችግረኞችን ባላቸው ሁሉ ይረዳሉ፤ ፍቅራቸውም ሰዎችን ይማርካል ብለው እንዲመልሱ በመፈለግ ነበር። ዛሬስ ቢሆን በዙሪያችን ባሉት ሰዎች ምን ዓይነት ምስክርነት ይኖረን ይሆን?

የዲቁና አገልግሎት ከአጋፔ ፍቅርና ቸርነት ማድረግ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ዓይነቱ ፍቅር መንፈሳዊ ፍቅር ነው። እምነታችን ተስፋ በተሞላበት መንፈስ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ አልፎ በተግባር ወደ ሌሎች እንዲደርስ ማድረግ ነው (ዮሐ. 15: 13፤ 3: 16)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝቡን በሙሴ አማካይነት ሲመራቸው በነበረ ጊዜ በመካከላቸው ያሉትን ችግረኞችንና ድሆችን ባላቸው ነገር ሁሉ እንዲረዱአቸውና እርስ በርስ ተደጋግፈው እንዲኖሩ የፍቅር ትእዛዝ ሰጥቶአቸዋል (ዘዳግ. 15:7-8)።

እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ተመላልሶ ሲያገለግል በነበረ ጊዜ የሚበሉትን አጥተው ለተራቡት ሕዝቦች የሚሆነውን ምግብ ደቀ መዛሙርቱ እንዲሰጡአቸው ሲነግራቸው እናያለን (ማቴ. 14: 16)። በተመሳሳይ መልኩ ከርሱ ጋር ሲጓዙ የነበሩ ሰዎች በረሃብ በተጠቁ ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ወይም ከሌላ ሀገር ሄዳችሁ ምግብ አምጡላቸው አላለም። ዛሬም ቢሆን ይህንን አገልግሎት መወጣት ያለባቸው የዘመኑ ደቀ መዛሙርት የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው። በኢትዮጵያ ያለች ቤተ ክርስቲያን የሌሎችን ሀገሮች ድጎማና ፕሮጀክት ብቻ መጠበቅ ትታ በመካከልዋ ያሉትን ችግረኞች በመንፈሳዊው ፍቅር ላይ በመመሠረት ምዕመናኖችዋን በማዘጋጀት በራሳቸው ሀብትና ጥሪት ማገልገል ያስፈልጋታል።
ይህች መጽሐፍ የዲቁናን ትርጉም በአጭሩ በመግለጽ ንጹሕና ነውር የሌለበትን አምልኮን ለማምለክ ድሆች ችግረኞች፤ መበለቶችና ወላጅ አልባ ልጆች ደርሰን እንድንረዳ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተ መሆኑን (የሐዋ. 6: 1-6፤ ያዕ. 1:27) ከማብራራቷም በላይ የቀድመውን የሐዋሪያት የዲቁና አገልግሎት መሠረት በማድረግ



በበለጠ ለመሥራት እንድንነሳሳ ታሳስባለች (የሐዋ. 2: 43-46፤ 4: 32-35፤ 6: 1-6፤ ያዕ. 1: 27)።

የዚህ መማሪያ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ዲቁና ምንም ዓይነት ትርፍ ወይም ጥቅም ሳንፈልግ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ፍቅር ለሌሎች መግለጽ የምንችልበትን መንገድ ማሳየት ነው። ስለሆነም የዲቁና አገልግሎት በየማኅበረ ምዕመናኑ መባ ከመሰብሰብ፤ ከማስተናገድ፤ የውበት ሥራዎችን ከመሥራትና ቅዱሳት ሚስጢራትን ከማዘጋጀት ያለፈ አገልግሎት መሆኑን የሚያስረዳ ነው። መጽሐፉ ሁለት ዓይነት ጥቅም ይኖረዋል።
አንደኛ በየመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች መደበኛ መማሪያ ሆኖ ያገለግላል። በሁለተኛ ደረጃ ለአንባቢያን ሁሉ በሚገባ መንገድ ቀለል ብሎ ስለተዘጋጀ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መጽሐፉን በመጠቀም በየማኅበራቸው የሥልጠና ትምህርት በመስጠት በተቀናጀ መንገድ ዲያቆናትን በመመልመል ችግረኞችን የመርዳት አገልግሎት ይጀምራሉ።

መጽሐፉ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለች ናት። የመጀመሪያው ክፍል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የዲቁና አገልግሎት ዕይታና መረዳት እንድሁም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የአገልግሎቱ መስፋፋት ሂደትና ልምዶችን የሚያከትት ሲሆን፤ ክፍል ሁለት የዲቁና አገልግሎት በማኅበረ ምዕመናን ደረጃ መተግበር እንዲቻል ለማድረግ የስልጠና፤ አደረጃጀትና የዲያቆናትን የሥራ ኃላፊነት ይተነትናል። ክፍል ሦስት ደግሞ ድሆችን መርዳት ከኢኮኖሚ አንጻር ብቻ እንዳልሆነና በሁሉም የኑሮ መስኮች ወደ ራስ መቻልና ዘለቄታዊ መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለውን ሥራ ፈጥሮ በራሳቸው መንቀሳቀስ እንዲችሉ የሚያደፋፍር ነው። እንዲሁም በረጂና በተረጂ መከካል ሊኖር የሚገባ ግንኙነትም የተስተከከለና ክፍተት የማይፈጥርበትን መንገድ የሚያሳይ ነው።

የመጨረሻውና አራተኛው ክፍል ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰብ ውስጥ ሊኖራት የሚገባውን የነቢይነት ዲቁና አገልግሎት ኃላፊነት የሚዳስስና እግዚአብሔር የፍትህና የሰላም፤ የነፃነትና የእኩልነትም አምላክ እንጂ የድነት አምላክ ብቻ እስመሆኑን የሚያስረዳ ነው። ይህም ከዘመናችን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፋዊ ነጻ ግቢይት ትስስር እና ከማህበራዊ ኑሮ ቀዉስ ተዕዕኖ የተነሳ ለችግሮቹም መፍትሔ ይሆናል ተብሎ ባጭሩ ለመግለጽ የተሞከረ ክፍል ነው።

አንዳንዴ ሰዎች በክርስቶስ ድነትን አግኝተው በምድር ኑሮአቸው ከአምላካቸው ያገኙትን ፍትህና ነፃነት እንዲሁም መብት አጥተው ሲቸገሩ እናያለን:: ከዚህ የተነሳ አንዱ ሌላውን ሲጫነው፤ ፍርድ ሲጣመምበት፤ የጾታ ልዩነቶች ሲደረጉና ሌቶች አለአግባብ ሲደፈሩ አይተን ዝም ማለት ለችግረኞች ፍቅር እንደጎደለን ያሳያል:: በተ ጨማሪም ይህ የዲቁና መማሪያ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሊያጋጥማቸው ከሚችሉ በሽታ፤ ጎጂ ባሕል ፤ ኢኮኖሚ፤ ማህበራዊ እና የፖለቲካ ጫና... ወዘተ ለማላቀቅ የተቻላትን ሁሉ ጥረት እንድታደርግ ይጠቁማል::

ውድ አንባቢያን መጽሐፉን ለማንበብ ጀምራችሁ ሳትጨርሱት ክአቋ ረጣችሁ ሙሉ መልዕክቱን ለማግኘት ሲያስቸግር ስለሚችል በተቻለ መንገድ ለራሳችሁ ሕይወት ጥቅም እንዲሁም በቤተ ክርስቲያናችሁ አገልግሎት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እንድትችሉ በማስተዋል አንብባችሁ እንድትጨርሱ ምክራችንን እንለግሳለን:: መጽሐፏ ሁሰንተናዊ እንደመሆኗ መጠን ሰዎች ሁሉ በመንፈስም ሆነ በአካለዊ ኑሮ በተግባራዊ ክርስትና ክድህነት ወደ ራስ መቻል ለማሸጋገር እና ለሁሰንተናዊ ለውጥ (Wholistic Transformation) መንገድ የሚታሳይ ስለሆነች ቀለል ባለ መልኩ ስለቀረበች ሁሉንም ልትጠቅም ትችላለች::



## ምስጋና

ይህንኑን አገልግሎት ለ35 ዓመታት በኢ/ወ/ቤ/መ/ኢ/ ውስጥ ሲያገለግለሉ የነበሩ ሲ/ር. ኬርቱ ኒዩግሪን የተባሉ ፊላንዳዊ ሚስዮናዊት በህገሪቱ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከHIV/AIDS ጋር የሚኖሩትን ሰዎች መርዳትና ከበሽታውም እንዴት መከላከል እንደሚቻል በማዕከላዊ ደቡብ ሲኖዶስ በሆሳዕና ማስተማርና ማካሄድ ጀመሩ:: ይህ አገልግሎት የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማር ጋር በልተነጣጠለ ሁኔታ ማካሄድ ሲጀመር አገልግሎቱ እየሰፋ ሄደ:: ከዚህም የተነሳ በቤተ ክርስቲያኒቷ ሁለመናዊ አገልግሎት መርሆ መሠረት ምዕመናን የዲቁና አገልግሎት የእምነት ፍሬአቸው እንደሆነ አምነው አገልግሎታቸውን እንድያበረክቱ ቤተክርስቲያኒቷ በብሔራዊ ደረጃ ለማገልገል በ16ኛው ዓቢይ ጉባዔ ወሰነች:: እነሆ አገልግሎቱም እየተካሄደ ነው:: በመሆኑም ለዚህ አገልግሎት መሠረት የጣሉና አሁን ግን በሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው የተመለሱ ሲ/ር. ኬርቱ ኒዩግሪን ማመስገን እንወዳለን::

ይህች መጽሐፍ ለመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች መማሪያ ሆና ከመቅረብዋ በፊት የወንጌል ተልዕኮና ቲኦሎጊ መምሪያ የክርስቲና ትምህርት አግልግሎት ቢሮ የዲቁና አገልግሎት የነበረውን ትምህርት በመጽሐፍ ደረጃ ለማሳድግ እንድቻል መርህ-ትምህርት እንድዘጋጅ መነሳሳትን ሰጠ:: በተጨማሪም ለጸሐፊዎች ወጪውን ሁሉ ሸፍኖ የሁለት ወር ተኩል ዓውደ ጥናት ኮርስ ከሰጠ በኋላ ሰአርትዖት ሥራው ደግሞ የመጀመሪያውን ጽሑፍ ለኢ/ወ/ቤ/ክ/መ/ኢ/ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች እንድሳክ ሐሳብ ሰጥቶ ትልቅ ዕገዛ በማድረግ የማሳተሙን ኃላፊነት ደግሞ ለዲቁና አግልግሎት ቢሮ በመስጠት ትልቅ አስተ ቃጽዖ ስላደረገ ልባዊ ምጋናችንን እናቀርባለን::

መጽሐፏ ለህትመት እንድትቀርብ አጠቃላይ ይዘቶችን አንድባንድ በማስተከከልና ተጨማሪ ሀሳቦችን በማዳበር እንዲሁም የኮ ምፒዩተር ሥራዎችን ያለአንዳች መሰልቸት የሠሩትን የቤተ ክርሰቲያኒቷ የዲቁና ረዳት አስተባባሪና የሥራ ባልደረባዬ የሆኑትን አቶ አመንሲሳ ኡልፋታን ከልብ አመሰግናለሁ::

# ክፍል አንድ

## 1. ዲቁና ምንድን ነው?

ዲቁና ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ቃልና ከመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተነሣ የጾታ፣ የቀለም፣ የዘር፣ የሃይማትና የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ሳይደረግ የተቸገሩ ሰዎች ከኢኮኖሚ፣ ከፖለቲካ፣ ከማኅበራዊና ከመንፈሳዊ ውጣ ውረድ እንዲወጡ የምታደርግበት አገልግሎት ነው። ቤተ ክርስቲያን ችግረኞችን የምትረዳው የክርስቶስ አካልና ምሳሌ ሆና በምድር የተመሠረተች በመሆንዋ እንጂ ከተረጂዎች ምንም ዓይነት ትርፍና ጥቅም በመፈለግ አይደለም።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር የወንጌልን ቃል ለማድረስ የሚትመራበት መሠረታዊ መርሆ «የሰውን ሁለመና ማገልገል» የሚለውን ነው። በዚህ መርሆ መሠረት የቤተ ክርስቲያኒቷ ሁለመነዊ አገልግሎት እውን የሚሆነው የዲቁናን አገልግሎት በተገቢ ሁኔታ መተግበር ስትችል ነው። ይህም ደግሞ ሲሆን የሚችለው እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያኒቷ አባል ባለው ስጦታና ብቃት ሁሉ የራሱ በሆኑ ነገሮች ወይም ሀብቶች እራሱንም ሆነ ሌሎች የተቸገሩትን ሰዎች እንደሚገባ ማገልገል ሲጀምር ነው።

እስካሁን ድረስ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ችግረኞች የሚረዱበት አገልግሎት በኢትዮጲያ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ዲቁና ተብሎ ባይጠራም፣ የዲያቆናትም አገልግሎት መባ በመሰብሰብ፣ በማስተናገድና ቅዱሳት ምሥጢራትን በማዘጋጀት ዙሪያ ብቻ ቢታወቅም፣ አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል። በመሆኑም በመጀመሪያ የቃሉን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም መመልከት አስፈላጊ ነው።

### *1.1 የቃሉ ትርጉም*

ዲቁና "Diakooia" ዲያኮንያ ከሚሰው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። «ዲያኮኒያ» አገልግሎት፣ እገዛን (እርዳታ)፣ በመሰብ ዙሪያ የሚደረግ የማዕድ ሥራን፣ ወዘተ ሊያጠቃልል፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከልዩ ልዩ አገልግሎቶች ጋር ተገናዝቦ (22 ጊዜ በሦስቱ ወንጌላት፣ 3 ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል፣ 8 ጊዜ በሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ)



በአጠቃላይ 33 ጊዜ ተጠቅሶአል ። የቃሉ ዋና ሐሳብ ራስን ዝቅ በማድ ረግ በታላቅ ትሕትና የተጎዱ ሰዎችን ማገልገል ማለት ይሆናል (ማቴ. 6:2-4፣ ዮሐ. 13:4-16፣ ሮሜ 12:7-8፣ ፊል.2:5-7፣ 1ኛ ጴጥ.4:11)።

Diakooos «ዲያኮኖስ» አገልጋይ ማለት ሲሆን ወንዶችንና ሴቶች ዲያቆናትንም ሊያጠቃልል ይችላል። ዲያቆናት የሚል ቃል በአዲስ ኪዳን 29 ጊዜ ተጠቅሶአል። ዲያቆናት የሚለው ቃል ከተለያዩ አገልግሎቶች ጋር ተያያዥነት አለው።

- ነገሥታት የእግዚአብሔር አገልጋዮች (ዲያቆናት) ተብለዋል (ሮሜ 13:4)
- ሐዋርያት የአዲስ ቃል ኪዳን አገልጋዮች (ዲያቆናት) ነበሩ (2ኛ ቆሮ. 3:6)
- ጳውሎስና ጢሞቴዎስ ራሳቸውን የጌታ ዲያቆናት ብለዋል (ፊል.1:1)
- ምእመናን የእርቅ አገልጋዮች (ዲያቆናት) ተብለዋል (2ኛ ቆሮ.5:18-20)
- ጌታችን ኢየሱስ በመጨረሻው ፍርድ ቀን የተራቡትን፣ የተጠሙትን፣ የተራቈቱትን የታሰሩትንና ያገለገሉትን ጻድቃን ( ዲያቆናት) ብሎ ይጠራቸዋል (ማቴ.25:40)።

Diakooeo «ዲያቆኔኦ» በጠረጴዛ፣ በማዕድ ዙሪያ ማገልገል፣ ማስተናገድ፣ ማደል ወይም ማከፋፈል የሚሰውን ያመለክታል።ይህም ቃል በአዲስ ኪዳን 36 ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን። በታማኝነት ማገልገል የከበረ ሥራ ስለሆነ በአዲስ ኪዳን ከሚከተሉት አገልግሎቶች ጋር ተያያዥነት አለው።

- እገዛ ከማድረግ ጋር (ማቴ. 25:44፣27:55፣ ዕብ.6:10)
- ከቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት ሥራ ጋር (1ኛጢሞ. 3:10-13)
- ለተቸገሩ ቅዱሳን ከተደረገ እርዳታ ጋር (ሮሜ 15:25፣ 2ኛቆሮ. 8:19)
- ኢየሱስ ከሰጠው አገልግሎት ጋር (ማቴ. 8:15፣ 20:28)
- ከማርታ አገልግሎት ጋር (ዮሐ.12:2)
- ጌታን በመስቀል ላይ ካገለገሉት ሴቶች ጋር (ማቴ.27:55-56)
- ከመላእክት አገልግሎት ጋር (ማቴ. 4:11፣ ማር. 1:13)
- ለደቀ መዛሙርት ከተሰጠው ትእዛዝ ጋር (ሉቃ. 22:26-27)

እሳይ የተጠቀሱት አገልጋዮች የራሳቸውን ጥቅም ሳይፈልጉ በረሃብ፣ በባርነትና በስደት ውስጥ የነበሩ ወገኖቻቸውን በፍቅር በማገልገላቸው ምሳሌ ትተውልን ሄደዋል:: አገልግሎታቸው ለገዛ ወገኖቻቸው ይሁን እንጂ እውነተኛ የፍቅር አገልግሎት ነበር::

4. የሰራፕታዋ ባልቴት:-

የሰራፕታዋ ባልቴት በአገርዋ ከነበረው የሦስት ዓመት ተኩል ድርቅ የተነሣ የምትበላው እህል አልቆባት ለመጨረሻ ጊዜ ትንሽ እንጎቻ ለመጋገርና ከልጅዋ ጋር በልታ ሞትዋን ለመጠበቅ የተዘጋጀች ሴት ነበረች:: ነቢዩ ኤልያስ ተርቦ ስለነበረ ሴትዮዋን ውሃና ቁራሽ እንጀራ ለመናት:: እርስዋም እምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን በማድጋ ካለው እፍኝ ዱቄት በማሰሮም ካለው ጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም አለችው:: ቢሆንም ከዚያችው ለእኔ እንጎቻ አድርገሽ አምጪልኝ ከዚያም ላንቺና ለልጅሽ አድርጊው:: ይህን ብታደርጊ ድርቁ ከምድር እስኪወገድ ድረስ ያለሽ ትንሽ ነገር አያልቅም አላት:: ይህንን በሰማች ጊዜ ለኤልያስ አስቀድማ የሚበላውን እንጎቻና ውሃ በእምነት ሰጠችው:: እንደ እግዚኣብሐር ቃል ስለታዘዘች የድርቁ ዓመታት እስኪያልፉ ድረስ የእግዚአብሔር በረከት አልጎደለባትም:: ይህ ክፍል ያለንን ለተራበ ማካፈል መጉደል ሳይሆን ለእግዚአብሔር መታዘዝ መባረክ እንደሆነ ያስተምረናል (1ኛነገሥ17፣8-16):: «ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል» (ምሳ. 19፣17)::

5. እራቱ ለምጻሞች:-

የሶርያ ንጉሥ በእስራኤል ላይ የሠለጠነበትና ከድርቅ የተነሣ የአህያ መንጋጋ በሃምሳ ብር፣ የዶሮና የርግብ ኩስም በአምስት ብር ይሸጥ የነበረበት ከዚያም በላይ እናቶች ልጆቻቸውን እስከመብላት የደ ረሱበት የመከራ ዘመን ነበር (2ኛነገ.6፣25-29):: ከዚህ የተነሣ አራት ለምጻሞች በአገራችን በረሃብ ከምንሞት ይልቅ የምንገደል ቢሆን እንኳ ዙሪያችን ወዳሉ አገሮች ሄደን እህል እንፈልግ ተባብለው ከሰማርያ ወደ ሶርያ መንገድ ሄዱ:: እዚያም ሲደርሱ እግዚአብሔር ሶርያውያንን አስደንግጦአቸው ድንኳኖቻቸውንና ያላቸውን ንብረት ትተው ሸሽተው ነበር:: ወደ የድንኳኑ ገብተው የሚበቃቸውን አግኝተው ከበሉና ከጠገቡ በኋላ:- «ዛሬ የመልካም የምሥራች ቀን ነው፣ እኛም ዝም ብለናል እስኪነጋም ድረስ ብንቆይ በደለኞች እንሆናለን፣ ኑ፣ እንሂድ ለንጉሡ ቤተሰቦች እንናገር ተባባሉ»(2ኛነገ.7:9-10):: ሄደውም



ነገሩአቸው:: የተራበውም ሕዝብ ሶሪያውያን ጥለው የሸሹትን ሀብትና ንብረት ለራሳቸው ወሰዱ፣ በሉ ጠገቡም::

እነዚህ ለምጻሞች በበሽታ የተጠቁ፣ በረሃብም የተጎዱ የተናቁና ምንም የሌላቸው ነበሩ:: ነገር ግን የወገኖቻቸው ችግር ተሰማቸው:: ሕዝባቸውም ከመከራ የሚድንበትን መንገድ ከፈቱ:: የምሥራችም አብሣሪዎች ለመሆን በቁ:: ከእነዚህ ለምጻሞች የምንማረው ሌሎችን ለመርዳት የብዙ ችሎታ፣ የብዙ ሀበት(ገንዘብ) ባለቤት መሆን ብቻ ላይሆን የሚያስፈልገው ለሌላው ማሰብ ነው::

ስለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው በማለት በስፋት የሚያስተምረን (መዝ. (41)፣1-3 ፣ ዘዳ. 15:7-11፣ ዘሌ.25፣35-43)::

በተጨማሪም በኢሳ. 58፣1-12 ያለውን ክፍል ስናነብ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተለያዩ የሃይማኖት ሥርዓቶችንና ወጎችን ከመጠበቅ ይልቅ በሕዝቡ ላይ የግፍ ሥራ እንዳይሠራ እንደሚፈልግ ክክፍሉ እንመለከታለን:: እግዚአብሔር ለሌላው ወንድሙና እኅቱ አስቦ በፍቅር የሚያገለግለውን ሰው ላይባርከው አይተውም:: ስለዚህም ሰዎች የበደልን እስራት ቢፈቱ፣ ቀንበር የሆነባቸውን ከባድ ሸክም ቢያስወግዱ፣ የተገፋውን አርነት ቢያወጡ፣ የተራቆተውን ቢያለብሱ፣ ከሥጋ ዘመዳቸው ባይሸሸጉ፣ የተጨነቀችውን ነፍስ ቢያጠግቡ...

- ብርሃንን እንደ ንጋት ብርሃን ያበራላቸዋል፤
- ፈውስን ያበቅልላቸዋል፤
- ጽድቅን ይሰጣል፤
- በእርሱ ክብር ይጠብቃቸዋል፤
- ጩኸታቸውንና ልመናቸውን ይሰማል፤
- ሁልጊዜም ይመራል፤
- ነፍስን በመልካም ነገር ያጠግባል... ወዘተ ይላል::

በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሐር ትልቁ ዓላማ ሰዎችን ካሉበት መከራና ችግር አውጥቶ እርስ በርሳቸው በፍቅር መረዳዳት እንዲችሉ ማድረግ እንጂ የቤተ መቅደሱን የአምልኮ ሥርዓት ማስጠበቅና ማስከበር ብቻ አልነበረም (ኢሳ. 1፣11-17፤ መዝ.(68)፣ 5-6፣ መዝ.12፣5፣ (146)፣6-9፣ አሞጽ4፣1፣ 5:10-15፣21-24፤ ሚክያስ 6፣8::

ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ስለሆነ ወደፊት ስለሚሆኑ

ነገሮች ትንቢት የተናገሩ ነቢያት እንኳ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን ያህል እንደሚጠነቀቅና እንደሚንከባከባቸው ጽፈዋል::

- ተጨንቆ የነበረ ሕዝብ ብርሃን እንደሚያይ (ኢሳ. 9፣1-3)፣
- ለድሆች በጽድቅ እንደሚፈርድና ልባቸው የተሰበረውን እንደሚጠግን ለተሰበሩት፣ ለታሰሩት፣ ለአልቃሾች... የምሥራችና መጽናናት ሆኖ እንደሚደርስ (ኢሳ.11፣4፣61:1-3)፤
- ለዓይነ ስውራን፣ ለታሰሩና በጨለማ ለተቀመጡ ነጻ አውጪ እንደሚልክላቸው እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱ ለሰዎች የነፍሳቸውና የሥጋቸው አገልጋይ ወይም ዲያቆን መሆኑን ያስገነዝበናል (ኢሳ. 42፣6-7 ፣ኢሳ. 53፣1-12)::

### 1.2.2. ዲቁና በአዲስ ኪዳን

በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ዲቁና የሚለውን ቃል በአማርኛ በግልጽ ባናገኝም፣ ከወንጌል ባለቤት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የዲቁናን አገልግሎት በስፋት እናገኛለን:: የኢየሱስን አመጣጥ ስንመለከት በብሉይ ኪዳን በትንቢት መጻሕፍት ስለእርሱ የተነገረውን ፈጻሚ በመሆን ሥጋ መልበሱን እንመለከታለን:: የክርስቶስ «ሥጋ መሆን» የሰዎችን ችግር ለመካፈል ራሱን ማዘጋጀት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ሲያስተምርና ወንጌል ሲሰብክ ከሠራቸው ነገሮች አንዱ በሕዝቡ ያለውን ሕመምና ደዌ መፈወስ፣ በልዩ ልዩ ሥቃይ ተይዘው የታመሙትን፣ አጋንንት ያደሩባቸውን፣ ሽባዎችንና ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ በመቀበል መፈወስና መርዳት ነበር (ማቴ.4፣23-24፣ሉቃስ 4፣17-19):: ይህ የሰውን ሁለንተና ማገልገልን ያመለክታል::

የአዲስ ኪዳን ዋና ዲያቆን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን እንደ እረኛ ሆኖ አገልግሎአል (ዮሐ.10፣11-15::) ከመንጋው አንድ እንዲጠፋበት አይፈልግም ነበር:: ከመቶ በጎች አንዱ ቢጠፋ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ አሰማርቶ አንዲትዋ ለመፈለግ ከሄደ እረኛ ጋር ራሱን አመሳስሎአል (ማቴ.18፣12-14፣ሉቃ.15፣2-7):: ምክንያቱም ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና :: ቤዛነቱም ሰዎችን በዘላለም ኪዳን ደም ከዓለም ርኵሰት አንጽቶ ሕዝቡ ማድረግ ነው (ዮሐ.3፣17፤ ዕብ.13:20)::

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ሲያገለግል ውስጣዊ ነገራቸውን



አውቆና ተረድቶ ያገለግላቸው ነበር (ዮሐ. 2፣25):: የመጀመሪያ ተአምራቱን በቃና ገሊላ በሠርግ ቤት በእናቱ ዘመዶች ቤተ ሰብ በደረሰባቸው ጭንቀት ተካፋይ በመሆን ውሃን ወደ ወይን ለውጦ ኀዘናቸውን ወደ ታላቅ ደስታ ቀየረላቸው (ዮሐ.2:1-11)::

የእግዚአብሔር ቃል ሰውን ከመንፈሳዊና ከምድራዊ የኑሮ አዘቅት ውስጥ አውጥቶ ከእግዚብሔር ጋርና እርስ በርሳቸው ሚዛናዊ የሆነ የፍቅር አገልግሎት እንዲራቸው ያደርጋል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርንና ሰውን መውደድ ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያና ሕግ መፈጸም እንደሆነ የአንድ ሕግ አዋቂ ጥያቄን ከመለሰበት ክፍል እናገኛለን (ማር. 12፣29-34)::

እነዚህ ሁለቱ ሕጎች በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ የተሰጡ ሳይሆን ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያንም የተሰጡ ናቸው:: እግዚአብሔር ያኔ ከአይሁድ ሕዝብ የፈለገውን ፍቅር አሁንም ከቤተ ክርስቲያን ይፈልጋል:: የብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ባልተለወጠ መልኩ የአዲስ ኪዳንም አምላክ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ገጽታ ዎች ያለውን ወንጌል በቃሉ አጽንቶ በተግባርም አሳይቶ አስተማ ረ (ማቴ.22:35-40):: ይህም እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የፍቅር አምልኮና፣ ከባልንጀራው ጋር ያለውን ተግባራዊ የክርስትና ኑሮ የያዘ ነው:: ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር የሚፈልጉ ክርስቲያኖች ከወንድሞቻቸው ጋር ጤናማ የሆነ ኅብረት እንዲፈጥሩ ይፈለጋል (ዮሐ.13:34-35፣ 1ኛ ዮሐ.3:14-18):: ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያየ ችግር ውስጥ የነበሩ ሰዎችን በፍቅር ሲያገለግላቸው ነበር:: የሕይወትንም ውሃ ይሰጣቸው ነበር (ማር.1፣29-31፣1፣34፣ 1፣40-44፣ 2፣1-12፣ 4፣35-41፣ 6፣36-49፣ ዮሐ.8፣1-11)::

የኢየሱስን ልብ ከሐዋርያት ምስክርነትና ለራሱ ከተቀበለው ምሕረት የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስ «እኛስ የክርስቶስ ልብ አለን» በማለት በድፍረት ሲናገር በ1ኛ ቆሮ.2:16 እናገኛለን:: ይህ ደግሞ ጳውሎስ እውነተኛ የጌታ ተከታይ ወይም ደቀ መዝሙር ሆኖ የመምህሩን ትምህርት፣ ኑሮና ሕይወት የሚያንጸባርቅ መሆኑን ያሳያል::

ኢየሱስ ክርስቶስ «በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» (ዮሐ.14፣12)

ሲል ስለ ተአምራዊ ሥራዎቹ ብቻ መናገሩ ሳይሆን እርሱ በፍቅርና በኀዘኔታ ልብ የተራቡትን እንደመገበ፣ የተቸገሩትን ከልዩ ልዩ ችግር ውስጥ እውጥቶ ከኅብረተሰቡ ጋር እንደቀላቀላቸው እኛም ይህንኑ እንድናደርግ መፈለጉን ያስተምረናል።

የኢየሱስን ልብ የሚያረካውና የሚያስደንቀው ሰዎች በፍቅር ተነሳሥተው ያላቸውን ለሌሎች ሲያካፍሉ ነው። አንዲት ድሃ መበለት ወደ ቤተ መቅደስ ገብታ ያላትን ሁለት ናስ ስትጥል በገንዘብ ማጠራቀሚያ ላይ አይቶ ለደቀ መዛሙርቱ ይህች ድሃ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች (ማር.12፤41-44) በማለት አድናቆቱን ገለጸ። ሌሎች ከብዙ ሀብት ጥቂቱን ሲጥሉ እርስዋ ግን ከጉድለትዋ ያላትን ሁሉ ጣለች። ውስጣቸው ወይም ልባቸው የተለወጠ ሰዎች ያላቸውን ሳይሆን ውስጣቸውን የለወጠውን ጌታ አይተው ይታዘዛሉ። ዘኬዎስ የተባለ ቀራጭና ኃጢአተኛ ሰው ጌታ ወደ ጓዳውና ወደ ቤቱ ሲገባ «ካለኝ እኩሌታውን ለድሆች አሰጣለሁ... ከማንም በግፍ የወሰድኩትንም ቢሆን እራት እጥፍ እመልሳለሁ»አለ (ሉቃ.19፤1-10)። ካለን ነገር ለተቸገሩት ማካፈል የእግዚአብሔርን ልብ ያረካል።

በተቃራኒው ደግሞ በምድር በሕይወት ሳለ ባለው ሀብት ችግ ረኛን መርዳት ስላልፈለገው ሰው ጌታችን ያስተማረውን ምሳሌያዊ ትምህርት እንመለከታለን (ሉቃ.16፤19-31)። አንድ ኑሮው ሁሉ የተ መቻቸለት ባለጠጋ ሰው ነበረ ። አልዓዛር የሚባል ድሃ በቊስል ተወርሶ በሀብታሙ ደጅ ይተኛ ነበር። የዚህን ድሃ ቊስሎች የሃብታሙ ውሾች ይልሱ ነበር። እርሱ ግን ከባለጠጋው ከሚጣል ምግብ ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር። ድሃውም ሞተ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት። ሀብታሙም ሞቶ ተቀበ ረ፣ ወደ ሲኦልም ወርዶ ይሠቃይም ጀመር። ሀብታሙ ከሥቃዩ የተነሣ በተራው አልዓዛር ከአብርሃም እቅፍ መጥቶ በጣቶቹ ውሃ ነክሮ መላሱን እንዲያበርድለት አብርሃምን ለመነ። በመካከላቸውም ታላቅ ገደል ነበርና መገናኘት አልተቻለም።

ይህ ሰው በሕይወት ዘመኑ ከነበረው ሀብት ለዚህ ቊስለኛ ድሃ ቢያካፍለው ምንም አይጎድልበት ነበር። ለድሃና ለችግረኛ ማካፈል ድኅነትን የሚያስገኝ ባይሆንም የዳነና የጸደቀ ሰው ሊያሳየው የሚገባ የክርስትና ሕይወት ነው። ይህም ክርስቲያን ከሚያፈራቸው መንፈሳዊ ፍሬዎች አንዱ ነው። ወንድማችንን በችግሩ ጊዜ አለማየትና አለመርዳት መንፈሳዊ ዕውርነት ነው፣ የፍቅር ማነስ ነው፣ የወንጌልን ትእዛዝ መተላለፍ ነው፣ ወንድምንም የመጥላት ምልክት ነው



(1ኛዮሐ.2፤8-11)። በምድር ሳለን ካልተዋደድን ወደ ጌታ ከሄድን በኋላ መውደድም መጥላትም አንችልም።

ሌላውን ሰው እንደ ራሳችን ማየትና እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ መውደድ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ፣ በስብከቱና በሥራዎቹ ብዙዎችን ከነበሩበት ችግር ውስጥ ማውጣቱ ሁለንተናዊ አገልግሎት መስጠቱን የሚያሳይ ነው። የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሆንን ሁላችን ይኸው አገልግሎት ይጠብቀናል። ዳግመኛ የተፈጠርነውም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ ነው (ኤፌ.2፤10)። የተቸገሩትን መርዳትና ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በእግዚብሔር አብ ዘንድ ንጹሕና ነውር የሌለበት መንፈሳዊ አምልኮ መሆኑን በያዕ.1:27 ተጽፎልናል።

እግዚአብሔርን የመውደዳችንና በፍጹም ልብ የማምለካችን ምንነት ደግሞ የሚገለጠው ለባልንጀራችን በተግባር በምናሳየው ፍቅር ነው። «እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን እውቀናል እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል»(1ኛዮሐ.3፤16)።
ሐዋርያትና ሌሎችም ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኋላ እርስ በእርሳቸው በተግባር ያሳዩት እንዲህ ዓይነቱን ፍቅር ነበር። የዲቁናን አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የእግዚአብሔር ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሕይወታችን መፍሰስ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ፍቅር ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አንዱ ነው (ገላ. 5፤22)።

«ያመኑትም ሕዝቡ አንድ ልብ፣ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው... በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና። ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር (የሐዋሥ. 4፤32-35)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ትክክለኛና ግልጽ የሆነ የዲቁና አገልግሎት ያስጀመረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተሰጠው የእግዚብሔር ፍቅር ነው። አንድም ችግረኛ አልነበረም፣ ያለውን ሀብትና ንብረት የራሱ እንደሆነ ያሰበ አንድም ሰው አልነበረም የሚለው ቃል ትክክለኛ የፍቅር አገልግሎት በመካከላቸው እንደነበረ ያመለክታል።

ከኢየሩሳሌም ከተማ ወደ ልዩ ልዩ የአሕዛብ አገሮች የደረሰው ወንጌል በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን የዲቁና አገልግሎት አስጀምሮአል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ፍቅር ለሮሜ ምእመናን ሲመሰክር: «በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም» (ሮሜ 5፤5) ይላቸዋል።

- *<u>ኦሪጅን፡-</u>* ለድሆች፣ ለመበለቶች፣ ለችግረኞችና ለስደተኞች ለመስጠት ስንል እኛ የምንበላውን ምግብ መቀነስ፣ የምንለብሰውንም ልብስ ቀለል ማድረግ፣ ለራሳችን ከምናጠራቅመው ሀብት ይልቅ ስጦታችን መብለጥ አለበት ሲል፤

- *<u>ጀስቲን፡-</u>* ከማንኛውም ነገር በላይ ለራሳችን ሀብትና ብልጥግና የምንፈልግ የነበርን፣ ዛሬ ግን ለሌላቸው የምናካፍል ሆነናል:: እንዲሁም ጠላቶቼን የምንገድል የነበርን፣ ክርስቶስን ካገኘን በኋላ የምንዋደድ ሆነናል በማለት ለንጉሡ በጻፋው ደብዳቤ ገልጾአል::

- *<u>ተርቱሊያን፡-</u>* ጠያቂ ለሌላቸው ሰዎች የምናደርገው እንክብካቤ በጠላቶቻችን ፊት የፍቅራችንን ጥንካሬ ከማሳየቱም በላይ ወደ ጌታ እንዲመጡ አድርጎአቸዋል ብሎአል::

- የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛው የፍቅር አገልግሎት ስለገባት ዲያቆናትን በአገልግሎት ስታሰማራ ድሆችን እንዲመግቡ፣ እንግዶችን ተቀብለው ቤት እንዲሰጡ፣በሽተኞችን እንዲጠይቁ፣ መበለቶችንና ወላጅ ዐልባ ልጆችን እንዲንከባከቡ፣ ለአባሎቻቸው መንፈሳዊ ነገር እንዲያስተምሩና እንዲያሳድጉ ወንዶች ዲያቆናትን ሲመድቡ፣ ሴት ዲያቆናት ደግሞ ሴት በሽተኞችን እንዲጎበኙ፣ ገላቸውንም እንዲያጥቡ ልብሶቻቸውንም እንዲቀይሩ፣ ለጥምቀት እንዲያዘጋጁ፣ ለሕመምተኞች የጌታ እራት እንዲሰጥ እንዲያደርጉ፣ እስረኞችን እንዲጎበኙ፣ ከአቅማቸው በላይ የሆነውን ለቄሶችና ለጳጳሳት እንዲያስታውቁና በጌታ እራት ቀን ከየቤተ ክርስቲያኑ መባ ሰብስበው ለችግረኞች እንዲያዳርሱ ያደርጉ ነበር::

- *<u>ጳጳስ ጆን ክርሶስቶም</u>*፡- ቸርነት ስለማድረግ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ማኅበራዊና መንፈሳዊ ችግራቸውን ለመፍታት በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ሁሉ በከፍተኛ መንገድ ያንቀሳቅስ ነበር::

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን፣ የዲቁና አገልግሎት ችግረኞችን ከመርዳት ጎን ከጳጳሳት ጋር በመሆን በቅዱሳት ምሥጢራት አገልግሎትና በማኅበራዊ እንክብካቤ ላይ ትኩረት ይሰጥ ነበር:: ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ሲባል ዲያቆናት ከምእመናን መካከል ተ መልምለው በሁለት እየተከፈሉ ያገለግሉ ነበር:: አንደኛው ሊተላለፍ የሚችል ማለትም ከዲቁና ወደ ቅስና የሚሸጋገር አገልግሎት ሲሆን፣



ሁለተኛው ደግሞ ጊዜያዊ የበጎ ፈቃድ አገልጋይ ተብሎ ኅብረተሰባዊ ዲቁና አገልግሎት ይሰጥ ነበር:: ከዚህ አደረጃጀት ውጪ ምእመናን እንደ ዲያቆናት እንዲቈጠሩ ከተፈለገ፣ *አንደኛ፣* የማኅበራዊ ጥሪ፣ *ሁለተኛ* ፣ጊዜአቸውንና ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገው መስጠት *ሦስተኛ* ደግሞ ሥልጠና መውሰድና አካባቢአቸውን ጠንቅቀው ማወቅ ነበረባቸው::

ይህ አገልግሎት እጅግ ጠቃሚ ሲሆን በተለያየ ጊዜ የአገልግሎቱ ይዘትና አሠራር ሲቀያየር ቈይቶአል:: ስለሆነም አገልግሎቱ በሦስት ደረጃ ተከፋፍሎ መሠራት ተጀመረ:: እነርሱም፡-

1. ማኅህበረ ምእመናናዊ ዲቁና (Congregational Diakonia)
2. ድርጅታዊ ዲቁና (Professional or Institutional Diakonia)
3. መንግሥታዊ ዲቁና (State – Civil Diakonia)

1. <u>ማኅበረ ምእመናናዊ ዲቁና</u> ፡- ዲያቆናትን ከምዕመናን መሐል ለአገልግሎት በመመልመል የሚሠራ ሲሆን የዲያቆናቱ የሥራ ዘመን እስከ ሕይወት ፍጻሜ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ነበር:: ይኸኛው ከመንግሥታዊ ዲቁና ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው አገልግሎት ነው::

2. <u>ድርጅታዊ ዲቁና</u>፡- ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመና አገልጋዮችን ዲያቆናት ብሎ ያልጠራው ክፍል ነው:: ምእመናኑና ሕዝቡ በእነዚህ አገልጋዮች ስለሚገለገሉ ሰዎች ለማስተማርና በሽተኞችን ለመንከባከብ ይችሉ ነበር::

3. <u>መንግሥታዊ ዲቁና</u>፡- ይህ የአገልግሎት ተቋም የሉተራንና የአንግሊካን አብያተ ክርስቲያናት ባሉበት እንደ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎት እንዲሆን ታስቦ በመንግሥት ደረጃ በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከመንግሥታዊ አገልግሎቶች ጋር ተቈጠረ::

በአዲሱ የካቶሊክ ዐውደ ጥበብ «እንሳይክሎፔድያ» የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን የዲያቆናት አገልግሎት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ላይ የተመሠረተ መሆኑን በመግለጽ የዲያቆናት አገልግሎት ሥልጣን ከቄሶችና ከጳጳሳት ሥር መሆኑን ጽፈዋል (ሐዋ ሥራ 6: 1-7፣ 1 ጢሞ. 3: 8-13፣ ፊልጵ. 1: 4 ከ1 ጢሞ. 3: 1-7 እና ቲቶ 1: 5-9)::

*የአንጾኪያ ቅዱስ አውግስጢስ* ከሦስቱ የአገልግሎት ክፍሎች (ጳጳሳት፣ቄሶችና ዲያቆናት) የዲያቆናት አገልግሎት ክፍል ዝቅ ብሎ ያለ መሆኑን ገልጾአል:: እንዲሁም *ሲፒሪያን* የተባለ ሰው «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዲያቆናት ድሆችን ለመንከባከብና ጥንቃቄ ማድረግ ከፍተኛ የሆነ አስተዳደራዊ ኀላፊነት አላቸው» ብሎአል:: *በሁለተኛው የቫቲካን ካውንስል* ዲያቆናት የጥምቀት፣ የጌታ እራትና የአስተዳደር ጉዳዮች አስፈጻሚ መሆናቸውን ይገልጻል:: ይህንንም ውሳኔ ሉተራውያን፣ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ፣ የአንግሊካን፣ የሪፎርምድ ሜቶድስት፣ የመጥምቃውያን፣ የአድቬንትስትና የጴንጤ ቆስጤ አብያተ ቤተ ክርስቲያናት ተቀብለውት ነበር::

እንዲሁም በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት በቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ጊዜ ቀሳውስትንና ጳጳሳትን ሲያግዙ፣ የመልእክት ክፍሎችን እንዲያነቡ፣ የጌታ እራት መስጠት እንዲችሉ፣ በጥምቀትና በሠርግ ጊዜ እንዲረዱአቸው፣ በአስተዳደር ሥራዎች መሳተፍ እንዲችሉ ተስማምታ ነበር::

በተጨማሪም የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን እንግዳ መቀበልን ክርስቶስን እንደመቀበል አድርጋ ትቈጥር ስለ ነበር ከራስዋ ምእመናን አልፋ ከሩቅ ለሚመጡትም ልግስና ታድረግ ነበር:: ከዚህ የተነሣ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ዲያቆናት ቄሶችንና ጳጳሳትን ከመርዳት አልፈው በተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች ተሰማርተው ነበር::

### 1.4.1. ዲቁና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኢትጵያ ከተመሠረቱ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ቀደምት ናት:: የክርስትና ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ የገባው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምዕራብና ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተብላ ለሁለት ከመከፈልዋ በፊት እንደሆነም ይታወቃል:: እንዳንድ ሰዎች የክርስቲና ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ሐዋርያት *በእስጢፋኖስ* ሞት ምክንያት በዙሪያ ወዳሉ አገሮች በተበታተኑበት ዘመን ወንጌላዊ (ዲያቆኑ) ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ከኢየሩሳሌም ወደ ሀገሩ ሲመለስ ወንጌል ካስተማረበትና ካጠመቀበት ታሪክ ጋርም ያያይዛሉ (ሐዋሥ.8፣30-40)::

በተለይም ክርስትና በግልጽ ወደ ሀገራችን የገባው በ*ንጉሥ*



*ኢዛና* ዘመን ከግሪክ አገር ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ወንድማማች *በፍሬምናጦስና ኤዴስዩስ* በ330 ዓ.ም. ገደማ እንደሆነ ታሪክ ይነግረናል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የዲቁናን (ችግረኞችን የመርዳት) አገልግሎትዋን የተቀበለችው ከመጽሐፍ ቅዱስና ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስለነበረ እስከ 9ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ጽድቅ የሚገኘው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን እንደሆነና መልካም ሥራ ደግሞ የእምነት ፍሬ ውጤት መሆኑን ትቀበል ነበር:: ነገር ግን ከደረሰባት የተለያየ ስደት፣ መከራና ውጣ ውርድ የተነሣ ለ600 ዓመታት ያህል የክርስትና ትምህርቷን በብቃት ማስተማር አልቻለችም::

በዚህ የጨለማ ዘመን ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ውጭ የሆኑ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥር መስደድ ጀመሩ:: የመስጠት አገልግሎት ወይም ድሆችን መመገብ፣ በጻድቃንና በሰማዕታት ስም የሚደረጉ ልዩ ልዩ ልግስናዎች የሚያጸድቁና የዘላለምን ሕይወት የሚያስገኙ ሆነው ተቈጠሩ:: ከዚህ የተነሣ የቤተ ክርስቲያኒቷ መሠረተ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቢሆንም እንኳ በመሃሉ የገቡ ሥርዓቶች፣ ወጎችና ባህሎች እያደር እንደ ሃይማኖት ሆነው ቀርተዋል::

በመሆኑም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስያን ብዙ ችግረኞች በተዝካር፣ በማኅበር፣ በሰንበቴና ለሙታን በሚደረጉ ልዩ ልዩ በዓላት የዕለት ጉርሳቸውን ያገኛሉ:: ይህ የሞተውን ሰው ከኵነኔ ወደ ጽድቅ እንዲያሻግርና ይቅር እንዲያስብልለት ጭምር የሚደረግ የጽድቅ ተግባር ነው:: ከዚህ የተነሣ ምእመናንዋ ከየትኛውም የሃይማኖት ክፍል ይልቅ በየመንገዱ ዳር የወደቁትንና የተቸገሩትን እንዲሁም በየገጠሩ በቤተ ክርስቲያኒቱ ለማገልገል ልዩ ልዩ ሥልጠናና ትምህርት የሚሰጡአቸውን (የቆሎ ተማሪዎችን) ይረዳሉ::

### 1.4.2. ዲቁና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዲቁና አገልግሎት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ከነበረው አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያለው ነው:: በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያለ ጾታ ልዩነት ከምእመናን መካከል ዲያቆናት ይመረጡ ነበር:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ለዲያቆናትም የሥራ ድርሻ እያከፋፈለች ተግባራዊ ታደርግ ነበር:: የዲያቆናቱም ሥራ እንደሚከተለው ነበር::

1. በየሳምንቱ ከምእመናን መባንና የገንዘብ መዋጮን መሰብሰብ፣

2. ይህንንም ገንዘብ ለመበለቶችና ለወላጅ አልባ ልጆች መስጠት፣
3. እስረኞችንና ምርኮኞችን በግልም በጋራም መርዳት፣
4. ባሮችን ማገልገል። ይህም አማኞች የሆኑትን ባሮች በገንዘብ እየገዙ ነጻ ማድረግ ነበር።
5. የታመሙትንና የሙት ቤተሰቦችን መርዳት፦ በሽተኞችን በማሳከም፣ የሞቱትን ለመቅበር ለማይችሉ አስፈላጊውን የገንዘብ እገዛ ማድረግ። ይህን አገልግሎት ለአረማውያን ጭምር ይሰጡ ነበር።
6. መንገደኞችን መቀበል። ባይተዋር የሆነ ሰው በሮሜ ካለፈ ተቀብላ ማስተናገድ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተግባር ነበር። ይህንንም «እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም» የሚለውን ቃል በማለብ ያደርጉ ነበር። ከጊዜ በኋላ ብዙ አታላዮች ስለ ተፈጠሩ እንግዳን ከሁለትና ከሦስት ቀናት በላይ ማቆየት አስፈላጊ ሆኖ አልታየም። አለበለዚያ እንግዶቹ መታወቂያ እንዲያሳዩ ይጠየቁ ነበር።

እነዚህንና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ትሰጥ የነበረች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የልግስና አገልግሎትዋ ቀስ በቀስ የተቋም ወይም ድርጅታዊ ሥራ እየሆነ መጣ። ስለዚህ ገዳማትን፣ ሆስፒታሎችን፣ ት/ቤቶችንና መዋዕለ ሕፃናትን በመሥራት ማገልገል ስለጀመረች የዲቁና አገልግሎት በልማት ሥር ውስጥ እየተካተተ ሄደ።

7. በጻድቃንና በሰማዕታት ስም ማገልገል። በጻድቃንና በሰማዕታት ስም ለተቸገሩት እንዳች ማድረግ ዋጋ እንዳለው ታስቦ ዲያቆናት በዚህ ሥር ማገልገል ጀመሩ። አገልግሎቱ እየሰፋ በመሄዱ ሮምን በሰባት ዲያቆናትና በተባባሪ ዲያቆናት ሥር በመክፈል እርዳታዎችን ያደርሱ እንደነበር ሊዮሲብየስ ጽፎአል። በሰባቱም ዲያቆናት ሥር 1500 ችግረኞች ይረዱ ነበር። በተለይም ከ4ኛ እስከ 7ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው የሴት ዲያቆናት አገልግሎት ወርቃማ ዘመን ተብሎ ይታወቃል።



## 1.4.3. ዲቁና በሉተራን ቤተ ክርስቲያን

የሉተራን ቤተ ክርስቲያን በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የወጣችና በዶ/ር ማርቲን ሉተር አማካይነት የተመሠረተች ናት። ማርቲን ሉተር የቤተ ክርስቲያን አዳሽ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በዘመኑ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጳጳሳትና ቄሶች የክርስትናን ሕይወትም ሆነ ሥርዓት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ ሁኔታ ልማዳዊ አድርገውት ነበር። ሆኖም ችግረኞችን ስለ መርዳት (የዲቁና አገልግሎት) መሠረታዊ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ማርቲን ሉተር ያውቅ ነበርና የበለጠ ተጠናክሮ እንዲሠራ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ጋር አያይዞት እናገኘለን። ማርቲን ሉተር ራሱ በዚህ አገልግሎት እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ሰው ነው። ሉተር ከመንፈሳዊ ተሐድሶ ጎን ድሆችን፣ መበለቶችንና ችግረኞችን መርዳት ከእምነት ፍሬዎች አንዱ እንደሆነ ከማስተማሩም በላይ ተግባራዊ ያደርግ ነበር። በግሉም ከሌላው ሕዝብ በላይ ለዚህ አገልግሎት ገንዘብ ያዋጣ ነበር። የሃይማኖታችንን አንደኛ አንቀጽ ሲያብራራም፣ «እግዚአብሔር እኔን ፈጥሮኝ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ሲሰጠኝ እኔን ማፍቀሩን እያሳየኝ ነው» ካለ በኋላ በምድር እያለን ጤና፣ ሀብትና ንብረትም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው በማለት አስተምሮአል። እግዚአብሔር ሰውን የሚባርከው ለሌሎችም በረከት እንዲሆን ነው እንጂ ራስ ወዳድ እንዲሆን አይደለም።

ሉተር ስለ ፍቅር አገልግሎት ሲገልጥ «ከእምነት ፍቅርና ደስታ ይመነጫል። ከፍቅር ደግሞ የሰውን ምስጋና የማይጠብቅ ችግረኞችን ለመርዳት የተዘጋጀ ልብ ይመነጫል» ብሎአል። በተጨማሪም ሰዎች የምስጋናን መሥዋዕት እንኳ እንደ ሥራ አድርገው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡ ከሆነ የደኅንነቱን ሥራ ከንቱ ያደርግበታል በማለት በሥራ መጽደቅ እንደማይቻል ገልጾአል።

የዲቁና አገልግሎት ለደኅንነታችን የምንፈጽመው መልካም ምግባር ሳይሆን ደኅንነትን በጸጋ ያገኘንና በእምነት የራሳችን ያደረግነው መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ የዳነ ሰው ከሚያፈራቸው መንፈሳዊ ፍሬዎች አንዱ ዲቁና (ተግባራዊ የፍቅር አገልግሎት) ነው። በጸጋ ዳንን ስንል ጸጋን ርካሽ ነገር ማድረግ የለብንም። ይልቁንም ጸጋ ዋጋ ተከፍሎ የተገኘ ስጦታ ነው። እኛም ለተቀበልነው የጸጋ ስጦታ ዋጋ መተመን አንችልም። ጌታ ኢየሱስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ዕዳችንን ከፍሎአል። ከዚህ ከእግዚብሔር ፍቅር የተነሣ ችግረኞችን፣ ድሆችን፣ መበለቶችን፣ ወላጅ አልባ ሕፃናትንና አረጋውያንን የምናገለግልበት የአገልግሎት ዘርፍ ነው። ሐዋርያው

ያዕቆብ እምነት በሥራ ካልተገለጠ የሞተ ነው በማለት ክርስትናችንን በተግባር እንድንገልጥ ያስተምረናል (ያዕ.2:20)።

የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎቷ የትኩረት አቅጣጫ በወንጌሉ አንደኛ ገጽታ ላይ ማለትም ሰው በክርስቶስ አምኖ እንዲድን ብቻ በመስበክ ላይ ብቻ ሳይሆን ወንጌልን በሙላት ለሰዎች ሁሉ በማቅረብ (የሰውን ሁለንተና በማገልገልና) እና ወንጌል በተሰበከበት ሁሉ የክርስትናን ኑሮ በመኖር ለሌሎች ጨውና ብርሃን መሆን ይጠበቅባታል። በተግባር የማይገለጥ ክርስትና ክርስትና ሊባል አይገባምና። ባልንጀራዎቻችን የሆኑ ችግረኞችን ለመርዳት ካለን ነገር አለማካፈል ከወንጌል በረከት መጉደል ይሆናል።

ከማርቲን ሉተር ዘመን ቀጥሎ በሉተራን ቤተ ክርስቲያን የዲቁና አገልግሎት ከዘመን ወደ ዘመን ከአገር ወደ አገርም የተለያየ መልክ ቢይዝም በምዕራባውያን አገሮች ለዲቁና አገልግሎት የሠለጠኑ ዲያቆናት በየማኅበረ ምእመናን ተመድበው ያገለግላሉ።

### 1.4.4. ችግረኞችን መርዳት በእስላም

እስልምና ድሀንና ችግረኛን ከሚረዱ የሃይማት ክፍሎች አንዱ ነው። የእምነቱ ተከታዮች የቁርአንን ትምህርት ተግባራዊ ያደርጋሉ። የሚረዱአቸውም ሰዎች የእምነታቸው ተከታይ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን የተቸገረውን ሁሉ ነው። ወላጅ አልባ የሆኑትን ልጆችን ሰብስበው የሚያሳድጉበትም በታና ት/ቤት አላቸው። በዚህ የሚረዱ ሕፃናት ቁራአን ይማራሉ።

ሙስሊሞች በልዩ ልዩ በዓላት ጊዜ የተቸገሩትን እየሰበሰቡ ካላቸው ነገር ሁሉ ያካፍሉአቸዋል። ለምሳሌ፡- በመውሊድ (በነቢዩ መሓመድ ልደት) ዕለት ቁራአን ድሀን እንዲረዱ ስለሚያዛቸው ለችግ ረኞች እርዳታ ያደርጋሉ። ይህም ሰው ሁሉ ለራሱ በሚደሰትበት ዕ ለት ችግረኛ ወንድሙን ማስደሰት እንዳለበት ስለሚነገር ነው።

*በዘካ (በስጦታ ቀን)* ማንኛውም ሙስሊም በዓመት ከሚያገኘው ገቢ ከመቶ 2.5ኀ ወይም ከእህሉ፣ ከከብቱና ካለው ነገሩ ሁሉ ስጦታ መስጠት ዋጅብ ወይም ግዴታ ነው። ሙስሊሞች ሁለት ዓይነት ስጦታዎች አሉአቸው። እነርሱም የግዴታ(ዋጅብ) እና የፍላጎት(ሱና) የሚባሉ ናቸው። ስለዚህ ዘካ በገንዘብ ላይ የተደነገገ ግዴታ ነው። የግዴታ ምጽዋት የሚከፈለው ለድሆች፣ ለምስኪኖች፣ በርስዋም ላይ



ለሚሠሩ ሠራተኞች ልቦቻቸውም በእስልምና ለሚለማመዱት ጫንቃ ዎችንም ነፃ ለማውጣት ለባለዕዳዎች በአላህ መንገድ ለሚሠሩና ....ከአላህ የተደነገገች ግዴታ ናት።

*__በረመዳን ጊዜ፡-__* በዚህ ጾም መጨረሻ ላይ አንድ ሙስሊም ካለው ነገር ከመቶ እጅ አሥሩን ከዚያም በላይ አጠራቅሞ ለሌለው ችግረኛ እንዲሰጥ ይታዘዛል። ነጋዴ ከሆነ የሱቁን ዕቃና ጥሬ ገንዘብ ሳይቀር ያሳያል። ጾም ሊፈታ አንድ ቀን ሲቀር የእስልምና ተከታይ የሆነ ሁሉ ስጦታ ይሰጣል። ብዙ ብር የሌለው ከሆነ ግን እህል ያከፋፍላል።

*በአረፋ(በእድአል አድሃ) ጊዜ፡-* ይህ ደግሞ የእርድ በዓል ቀን ነው። ይህ ቀን ሙስሊም የሆነ ሁሉ ዶሮ እንኳ አርዶ ደም ማፍሰስ ያለበት ቀን ነው። በዚህ ቀን ድሀ ወገኑ ደም ሳያፈስ እንዳይቀር ይደ ረጋል። በዚህ ጊዜ ድሀ ጦሙን አያድርም። በተለይ በመስጊድ ካረዱትም ሆነ በቤታቸው ካለው ሥጋ ለሚለምኑት ሳያካፍሉ ትተ ዋቸው አያልፉም። በአጠቃላይ ሙስሊሞች አንድ ሰው ተቸገርኩ ብሎ ከቀረበ ዝም ብለው ማለፍ አይፈልጉም።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ በእስልምና እምነት ለድሀውና ለችግረኛው ስጦታ የሚሰጥበት ትልቁ ምክንያት አላህ ለጽድቅ እንደሚቀበልላቸው በማመን ነው።

### 1.4.5. ችግረኞችን መርዳት በማኅበራዊ ጉዳዮች ውስጥ

በሁሉም ኅብረተሰብ ውስጥ የጉርብትናና የመረዳዳት ባህል ይኖራል። በተለይ በኢትዮጵያ በገጠርም ሆነ በከተማ ክልል በሞት ጊዜ እድር፣ በሕመም ጊዜ በሽተኛን ወደ ሐኪም ቤት ተሸክሞ መውሰድ፣ እንዲሁም በኀዘን ጊዜ ያዘኑትን ማጽናናትና መራራት በደስታና በሰርግ ጊዜ በጉልበትና በገንዘብ መረዳዳት የተለመደ ነው። እነዚህ ተግባሮች የግድ ክርስቲያናዊ ብቻ ናቸው ማለት አይቻልም። እድር በከተማም ሆነ በገጠር ሃይማትን፣ ዘርንና አካባቢን ሳይለይ የመ ረዳዳት ባሕርይ አለው። በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የአፍሪካ ኅብረተሰብ በጣም ጠንካራ ነው። የእርስ በርስ መቀራረብና የዕቃ መዋዋስ፣ አብሮ የመብላትና የመጠጣት ልምድም አለው።

በኢትዮጵያ በገጠሩ ኅብረተሰብ «ደቦ» ማለትም ሥራን በጋራ መሥራትና መረዳዳት የተለመደ ነው። ሰዎች በቡድን ወጥተው ለችግ

አገልግሎት ነው። ስለሆነም የኅብረተሰቡ እውነተኛ አገልጋይ ሆኖ ይኖራል።

እግዚአብሔር ሰሙሉ ሰውነት የሚያስብ መሆኑ በወንጌል ውስጥ በግልጽ ይታያል። አላይ የተጠቀሰው የቤተ ክርስቲያኒቱ ጽሑፍ ስለልማት ሲያብራራ፣ «በቤተ ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ልማት ወይም እድገት ማለት ሰዎች ችሎታቸውን ከግብ የሚያደርሱበት የነጻነት አሠራር መሆኑን አመልክቶ፤ ሰው ያለ እግዚአብሔር ዓለምን ሊያደራጅ ይችላል። ዳሩ ግን ሰው ዓለምን ሊያደራጅ የሚችለው ለሰው ጉዳት ብቻ ነው» ብሎአል። እንዲሁም ልማት በክርስቲያናዊ አመለካከት ያለ እግዚአብሔር ሲሆን ጥፋትን ሊያስከትል ይችላል። በዘመናችን ቴክሎጂ እጅግ ከፍ ብሎ ከማደጉ የተነሣ ሰው ዓለምን በሰዓታት ልዩነት ሊያጠፋ የሚችል መሣሪያ መፈልሰፍ ችሏል።» ክርስቲያናዊ ልማት ግን የሰውን ምድራዊና መንፈሳዊ እድገት ያማከለ መሆን አለበት። ችግረኞችን በፍቅር ለመርዳት የሚያስብ ሰው «ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም» (ኤፌ.4፥28) የሚለውን ቃል ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባዋል።

ልማት ችግረኞችና ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ከሚረዱባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በልማት የመጠጥ ውሃ ያጡ ጉድጓድ ተቈፍሮ ውሃ አግኝተዋል። ትምህርት ላልነበራቸው ትምህርት ቤት ተሠርቶ የመማር ዕድል አግኝተዋል። ክሊኒኮች፣ የጤና ኬላዎች፣ ሆስፒታሎች ተሠርተው ሰዎች ሕክምና ተደርጎላቸዋል ... ወዘተ። ልማት ለሰፊው ኅብረተሰብ እድገትን የሚያመጣ ዓለም አቀፋዊ ዲቁና ሲሆን፤ በዚህ መጽሐፍ የተገለጸው ዲቁና ግን በየማኅበረ ምእመናኑ ከክርስቲያናዊ ፍቅር የተነሣ በዙሪያችን ያሉትን ችግረኞች በተቀናጀ መንገድ ማገልገልና ወደ ሞት የቀረቡትን እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ መርዳት፣ መሥራት የሚችሉትን ደግሞ ምርታማ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ከዚህም በላይ ክርስቲያች የኅብረተሰብ አካል ሆነው ለድህነትና ለችግር የሚዳርጋቸውን ማንኛውንም ነገር በሰላማዊ መንገድ የማስወገድና የመከላከል ኃላፊነት አለባቸው።



## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ዲቁና ማለት ምን ማለት ነው?
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የብሉይና የአዲስ ኪዳን የዲቁና አገልግሎት መረዳት ተመሳሳይነትና ልዩነት ጻፍ።
3. ኢየሱስን እንደ ዋና ዲያቆን የሚያስቆጥሩ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
4. የዛሬይቷ ቤተ ክርስቲያን የዲቁና አገልግሎት ከጥንቱ ቤተ ክርስቲያን የዲቁና አገልግሎት ጋር አስተያይተህ ደከማና ጠንከራ ጎናቸውን ጻፍ።
5. በጽድቅና በሥራ (ተግባር) መሃከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
6. በቤተ ክርስቲያን የዕድገት ታሪክ ውስጥ የዲቁና አገልግሎት በምን መልኩ መረዳትና አደረጃጀት እንደ ተስፋፋ ግለጽ።
7. ችግረኞችን ስለመርዳት ከሌሎች የኃይማኖት ቤቶችና ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች አመለካከትና መተግበር ጋር ስታነጻጽር እንዴት ትረዳለህ?
8. በምትኖርበት አከባቢ ሰዎች ስለዲቁና አገልግሎት ያላቸው አመለከከት ምን ይመስላል?
9. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዲቁና ሁለንተናዊ አገልግሎት ነው ሲባል ምን ማለት እንዴሆነ ግለጽ። በክፍሉ ውሰጥ ያገኘኸውን ግንዛቤ ለሕይወትህና ለአገልግሎትህ ያበረከተልህን አስተዋጽኦ ዘርዝር።

# ክፍል ሁለት

## 2. የዲቁና አገልግሎት ሥልጠናና አደረጃጀት

ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ዲቁናና ዲያቆናት ለሚሉ ቃላት የስም ትርጉም ለውጥና ማብራሪያ ሲሰጥና ሥራውም ሲገመገም ቆይቷል። ከዚህም የተነሣ ብዙዎች ትክክለኛው የዲያቆናት አገልግሎት ይኸኛው ነው ብለው መግለጽ የቸገራቸው ይመስላል። ቢሆንም ብዙ ሰዎች ዲያቆን የሚል ስም ባይሰጣቸውም የሥራው ተካፋዮች ሆነዋል። ዲያቆናት ተብለው የሚጠሩት እነማን እንደሆኑ በይበልጥ ለማወቅና የአገልግሎት ብቃት ደረጃን ለማሳደግ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተ ምራል። የዲቁና አገልግሎት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት መሆኑን በቅድሚያ በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ዋነኛው ተግባር ነው።

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሂደት እንደምናየው የዲያቆናት ቀዳሚ ሥራ ማኅበራዊ አገልግሎት መስጠትና የቅዱሳት ምሥጢራትን ዝግጅት መፈጸም ነው። እንዲህ ከሆነ በዘመናችን ዲያቆናት ምን ዓይነት ሥልጠና ተቀብለዋል? ማንንስ ይረዳሉ? አገልግሎታቸውስ የሚካሄደው በልምድ ነውን ወይስ በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ ነው? የሙሉ ጊዜ ነው ወይስ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ? ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በምን ይለያሉ? በእነማን የተመረጡ ናቸው? የሚመረጡትስ ወንዶች ብቻ ናቸው ወይስ ሴቶችም? በዚህ በሁለተኛው ክፍል እላይ የተገለጡ ሐሳቦችን በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን።

### 2.1.. የምናገለግላቸው እነማንን ነው?

የሰው ልጆች በኃጢአት ከወደቁ በኋላ ችግርና መከራ በዓለም እየተፈራረቀ ይገኛል። ከተከሰቱት ችግሮችና መከራዎች አንዱ የሰ ዎች እርስ በርስ ላይ መጨካከንና ለሞት መዳረስ (ዘፍ 4:1-7) ነው። ሁለተኛው አዳም (ክርስቶስ) ደግሞ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በኃጢአት ምክንያት የሚሠቃዩትን የሰው ልጆች ለማዳን ወደ ዓለም መጥቶ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ። ይህን በማደረጉም ራሳቸውን ለመሰሎቻ ቸው መስጠት የሚቻልበት ፍቅር አስተማረ። «እኔ ለእናንተ እንዳደ ረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና» (ዮሐ.13:15)። በመንፈሱም ደግሞ ይህንኑን ፍቅር ባመኑት ልብ አፈሰሰ (ሮሜ. 5:1-11)። ስለዚህ ከክርስቶስ የተሰጠንን



ልብ ተጠቅመን የዲቁናን አገልግሎት ከቤተሰብ ጀምረን እስከ ኅብረተሰብና ዓለም አቀፍ ደረጃ ቢናሰፋ ብዙ ችግረኞች፥ ወላጅ አልባ ልጆችና ባልቴቶች ሊረዱ ይችላሉ። በአካባቢያችን በሽተኞች፣ አቅመ ደካሞች፣ የነፍስና የሥጋ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሞልተዋል። እኛ ክርስቲያኖች እነዚህን ብናልፋቸው ወደ ማን ይሄዳሉ? አንድ የቆየ መዝሙር አዝማች እንዲህ ይላል፦

*ሸክም ይሰማሃል ወይ ክርስቲያን ወንድሜ ሆይ?*
*ለሚጠፉት ወገኖች ልብህ ያዝንብሃል ወይ?*
*ጥፋታቸው ተሰምቶህ አዝነህ ትጸልያለህ?*
*በራስህ ተመክተህ ወይስ በመፍረድ ላይ ነህ?*

ሰው በተለያየ ምክንያት ችግረኛ ሊሆን ይችላል። በበሽታ የሚሠቃዩ፥ በረሀብ፥ በእርዛት፥ በአካል ጉዳተኝነት፥ ኢ-ፍትሐዊ በሆነ ተግባር በጭቆና የሚሳቀቁ፣ በጦርነት ምክንያት ከአካባቢአቸው የሚሰደዱና ሥራ አጥተው የሚንከራተቱ ብዙ ናቸው። በዚህ ሁሉ የሰው እርዳታ የሚፈልጉ አሉ። ጌታ ኢየሱስ ጠላት ወዳጅ ሳይል ለተ ቸገሩት ሁሉ ዘላቂ የሆነ መንፈሳዊና አካላዊ መፍትሔ ይሰጣቸው ነበር። ከዚህ በመነሣት የቤተ ክርስቲያን ዲቁና አገልግሎት እነማንን ማጠቃለል እንዳለበት እንደሚከተለው ማየት ይቻላል። እነርሱም፦

ሀ. ክርስቲያኖች ለ. ክርስቲያን ያልሆኑ ሐ. ጠላቶች ናቸው።

ሀ. ክርስቲያኖች፦ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ መርዳት እንደሚያስፈልጋቸው የሮሜ ምእመናንን ያሳስባል (ሮሜ 12:13)። በሮሜ ከተማም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ባለው ኅብረተሰብ ላይ የተለያየ ችግር ይደርስበት ነበር። በመሆኑም የሚቸገሩትን ቅዱሳን በሚያስፈልጋቸው እርዱ እያለ ይመክራቸዋል። ዛሬም ቢሆን በክርስቲያኖች መካከል የተለያየ ችግር ያለባቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ችግረኞች በክርስቶስ ያገኘናቸው ሰማያዊ ቤተሰቦቻችን ናቸው። ሰመንፈሳዊ ቤተሰቦቻችን ማሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት መሆኑን ሐዋርያው ያስገነዝበናል። «...ለእርሱ ለሰሆኑት ይልቁንም ለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖቱን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው» 1ኛጢሞ 5:8። ለሥጋ ዘመዶቻችን እንደምናስበው ሁሉ በጌታ ወገኖቻችን ለሆኑ ቅዱሳንም ማሰብ ይገባናል። በቤተ ክርስቲያናችን ከእኛ ጋር የሚያመልኩ ነገር ግን የሚበሉትና ፣ የሚጠጡት፣ ጠያቂም የሌ ላቸው የታሰሩ፣ የታመሙና፣ ያዘኑና አጽናኝ የሌላቸው፥ ኀደኛ ያጡ

ብቸኞች ቅዱሳን እሱ። እነዚህን ወገኖች በሚያስፈልጋቸው መርዳት የሁሉም ክርስቲያን ኃላፊነት ነው። ይህን ፈጽመን ብንገኝ በእግዚአብሔር ዘንድ የማይረሳ ዋጋ አለን። «እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ አስካሁንም ስለምታገለግሉአቸው ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና»(ዕብ 6:10) በማለት ቃሉ ያረጋግጣል።

ሠ. <u>ክርስቲያን ያልሆኑ፡-</u> የቤተ ክርስቲያን ዲቁና አገልግሎት ለክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ላላመኑትም ሰዎች ጭምር አስፈላጊውን አገልግሎት ይሰጣል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች መካከል ልዩነት እንዳናደርግ አስተምሮአል። «እርሱ በክፉዎችና በበጎ ዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና»(ማቴ 5:45) ይላል። ይህ ክፍል እግዚአብሔር ለሁሉም ቸር አምላክ መሆኑን ያሳያል። እግዚአብሔር ላላመኑ ሰዎች ፀሐይን፣ ዝናብን፣ ምግብን፣ ልብስን፣ ጤናንና መጽናናትን ከልክሎአቸው አያውቅም። ምናልባት ሰዎች የእግዚአብሔር ፍቅር ስላልገባቸው ወደ እርሱ መጠጋት ያቅታቸው ይሆናል እንጂ ለሁሉም በጎነቱንና ቸርነቱን አያሳንስም።

«ኢየሱስም ወጥቶ ብዙ ሕዝብ አየና እረኛ እንደሌላቸው በጎች ስለነበሩ አዘነላቸው» ማር.6:34 ብሎ ወንጌላዊ ማርቆስ ጽፎአል። ምንም እንኳን ለያምኑ ተአምራት ለማየት ወደ ኢየሱስ ቢመጡም በምድረ በዳ ረሀብ በጎዳቸው ጊዜ አዘነላቸው፤ የሚበሉትንም ምግብ ባርኮ ሰጣቸው፤እስኪተርፋቸውም በልተው ጠገቡ። ጌታ ኢየሱስ ሁሉንም በፍቅር የመቀበል፣ የማስተናገድና የመርዳት ተግባር ፈጸመ። በእርሱ የሚያምኑም እርሱ የሠራውን ሥራ እንደሚያደርጉ እንዲያውም ከዚያም የሚበልጥ ሥራ እንደሚሠሩ በዮሐንስ 14:12 ላይ ተናግሮአል ። በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ የእርሱን ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ብዙ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ደሴት ፈጥረው ከሁሉም ነፃ ሆነው መኖር ይፈልጋሉ። ቃሉ ግን እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት ይቃወማል። «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» ሲል ከራሳችሁ ደሴት ውጡና በብዙ ነገር ወደ ማታውቁአቸው ሰዎች ሂዱ ማለቱ ነው። ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ የዲቁና አገልግሎት ለመስጠት ሲባል የተላክንባቸውን ሰዎች ቋንቋ፣ ዘር፣ ሃይማት፣ ባሕል፣ ባሕርይና ችግር ላናውቅ እንችላለን። ይሁን እንጂ በሁሉም ዘንድ የክርስቶስ መልእክተኞች እንድንሆን ስለ ተጠራን ወደ ተለያዩ ሰዎች መሄድ ችግራቸውንም መካፈል የክርስቲያን ተግባርና ኃላፊነት ነው። አንድ ክርስቲያን



ሊያስተውለው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር የክርስትናን እምነት ላልተቀበሉ ችግረኞች የምናደርገው እርዳታ እውነተኛ ከሆነው ከክርስቶስ ፍቅር የተነሣ ብቻ የምናደርገው አገልግሎት መሆኑን እንጂ እንዲድኑ የምናበረክትላቸው ጉቦ ስጦታ ወይም ሽልማት አለመሆኑን ነው። ድነት ከስጦታ ጋር የተያያዘ ነገር አይደለም። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ በዚህ የፍቅር አገልግሎታችን ውስጥ አልፈው ወደ እውነተኛ የክርስትና ሕይወት ያልመጡትን ወደ ራሱ የሚጠራበት መንገድ ሊሆን ይችላል። ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ እየተመላለሰ ሰዎችን ያገለግል በነበረበት ጊዜ እርሱ ያደረጋቸውን የተለያዩ ድንቆችና ተአምራት ያመኑና ያላመኑ ሰዎች ነበሩ ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው አሥሩን ለምጻሞች ሲፈውሳቸው የተከተለው አንዱ ብቻ ነበር (ሉቃ 17:11-19)። ክርስቲያናዊ በጎ ሥነ ምግባርን ለድነት መመሪያ አድርጎ መጠቀም ትክክል አይደለም። የድነት ጥሪ ከክርስቶስ እንጂ በጎ ተግባር አይደለም። ዋናው ነገር የፍቅር አገልግሎት ለሁሉም ሰው ሊሰጥ የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ነው። ይልቁንም በእኛ ሕይወት ፍቅርና ርኅራኄ ሲታይ መቅረቱ ለብዙዎች መሰናክል ይሆናል።

ሐ. ጠላቶች፡- መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን «ጠላትህ ቢራብ አብላው፣ ቢጠማም አጠጣው»(ሮሜ 12:20) ይላል። ጠላት የሚለው ቃል በተለያዩ ሰዎች የተለያየ ሐሳብና ትርጉም የሚሰጠው ቢሆንም፣ በማንኛውም መንገድ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእኛ አስተ ሳሰብና አመለካከት ውጪ ለሆኑ ሰዎች እንደ ማንኛውም ሰው ያለምንም ልዩነት ማገልገል እንደሚገባን ቃሉ ያስስበናል። የሰው ልጅ ንጹሕና ቅዱስ ሆኖ በእግዚአብሔር አምሳያ እንደተፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በሰው ልብ ክፋት የገባውና ሰው ለሰው ጠላት ሆኖ የተነሣው በሰይጣን ተታሎ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ነው። ስለሆነም ጠላትነት በኃጢአት የመውደቅ ውጤት ነው (ዘፍ 4:1-7)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕይወት ስለ ሕይወት፣ ጥርስ ስለጥርስ፤ዓይን ስለዓይን፤ እጅ ስለእጅ፤ እግር ስለእግር በማለት ጠላቶቻችንን እንድንበቀል ይናገራል (ዘጸ. 21:23-25)። ሰዎች እርስ በርሳቸው ይበቀሉ ነበር እንጂ በፍቅር ይቅር አይባባሉም ነበር። በሌ ላ አባባል ሰዎች የሕግ እንጂ የፍቅር ተገኀርዎች አልነበሩም። ይሁን እንጂ በአዲስ ኪዳን የተለየ አዲስ ትእዛዝ አናገኛለን። ይኸውም የአዲስ ኪዳን መሠረቱ ፍቅር ነው። ጌታ ኢየሱስ «ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህን ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ»

(ማቴ 5:43-44) በማለት አስተምሮአል:: ጌታ ኢየሱስ በሰዎች ውስጥ የነበረውን የጥል ግድግዳ በማፍረስ አስደናቂ ፍቅሩን አወጀ:: ይህንንም ጠላቶቹን በመውደድ በተግባር አሳየ:: አሳልፎ የሚሰጠውን የአስቆሮቱ ይሁዳን ከሌሎች ደቀ መዛሙርት እኩል ስለወደደ እንደሌሎቹ ሁሉ እግሩን ዝቅ ብሎ አጠበ:: ሰዎች በጠላትነት ተነሥተው በመስቀል ላይ ሲቸነክሩትና ሲገድሉት፤ «አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» በማለት ጸለየ (ዮሐ. 13:3-14፣ሉቃ 23:34):: ኢየሱስ እስከ ሞቱ ድረስ ፍቅሩን በተግባር ገለጸ::

ዛሬም ቢሆን ሰይጣን አንዱን በአንዱ ላይ ጠላት አድርጎ ያስነሣበታል:: የፍቅር ልብ ካለን የዚህ ዓይነቱን ተግባር እንጠላለን:: ክርስቲያኖች የክርስቶስ ልብ ስላለን( 1ቆሮ. 2:16) እርሱ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ያሳየውን ፍቅር መግለጥ እንችላለን:: ስለዚህ ጠላቶቻችን ሲረግሙን እንመርቃለን፣ ሲያሳድዱን እንጸልያለን:: ሆኖም በሥጋ ሲታሰብ ይህ ቀላል ላይሆን ይችላል:: ነገር ግን ጠላቶቹ ሳለን የወደደንን ስለ እኛም ነፍሱን አሳልፎ የሰጠውን ጌታችንን በምናስብበት ጊዜ በጸጋው እንችላለን ( ሮሜ. 5: 10፤ኤፌ. 2:3)::

ጠላቶቼን እንድወድ ጌታ አስተማረኝ፣
በመስቀል ተቸንክሮ ፍቅሩን ገለጠልኝ::
መልካም ፍቅር ኦ መልካም ፍቅር፣
ተወለደ ሊጠላ ለኛ <u>ለመስቀል::</u>/2/
ያዳምን ልጆች ኃጢአት በደሙ ለመክፈል:: /2/

## 2.2 ችግረኞችን ለምን እናገለግላለን?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የዲቁና አገልግሎት በተለያየ ምክንያት ይሰጣል:: ከእነዚህም ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

### 2.2.1. መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያዘን

ከእግዚአብሔር የተሰጡን ትእዛዛት ብዙ ሲሆኑ ከእነዚህ አንዱ ችግረኞችን መርዳት ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዛትን በሙሉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎአቸዋል:: አንደኛው፤ እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹምም ነፍስህ፣ በፍጹምም አሳብህ፣ በፍጹምም ኃይል መውደድ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው (ማር.12:28-34):: በዚህ ክፍል በስፋት የምንዳስሰው ሁለተኛውን አሳብ ነው:: እግዚአብሔርን መውደዳችን የሚታወቀው በመታዘዛችን ሲሆን መታዘዛችን የሚታወቀው ደግሞ ባልንጀራችንን በሚያስፈልገው ነገር በመርዳታችን



ነው:: እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እያለ ለወንድሙ የማያስብ እርሱ ሐሰተኛ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚያየውና የሚያመልከው በመንፈስ ነው:: ወንድሙን ግን በአካል በአጠገቡ ያየዋል:: የወንድሙን ችግርና ጉስቁልና በዓይኑ እያየው ካለው ያላካፈለው እንዴት በአካል የማያየውን እግዚአብሔርን ሊወደው ይችላል?(1ዮሐ.4:20)::

ባልንጀሮቻችንን የመውደድ ትእዛዝ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስለሆነ ልንፈጽመው ይገባናል:: ያዕቆብም በመልእክቱ «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ» እያለ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንድንፈጽም ያሳስበናል (ያዕ. 1:22) ::

እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ስለሆነ የችግረኞች ጉዳት ያሳስበዋል:: ስለሆነም በድሀ ወንድሞቻቸው ላይ እንዳይጨክኑ፣ የለመኑአቸውን እንዲሰጡና አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ አዝዞአል (ዘዳ. 15:7-11):: ጌታ ኢየሱስ «የምትወዱኝ ከሆናችሁ ትእዛዜን ጠብቁ»(1ዮሐ 14:15-23) ይላል:: በተጨማሪም ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቱ፤ «የምጽፍላችሁ አዲስ ትእዛዝ አይደለችም አሮጌይቱ ትእዛዝ የሰማችኋት ቃል ናት::. . በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስካሁን በጨለማ አለ:: ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል:: ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ:: በጨለማም ይመላለሳል» (1ኛዮሐ. 2:7-11) ብሎ በግልጽ ያብራራል::

### 2.2.2 የክርስቶስ ፍቅር ግድ ስለሚለን

እግዚአብሔር ትእዛዙን የሰጠን ከፍቅር የተነሣ ቢሆንም፣ እኛ ደግሞ መታዘዝ የምንችለው የእርሱ ፍቅር ግድ ስለሚለን ነው (2ኛቆሮ. 5:14-15):: በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልባችን የፈሰሰው የእግዚአብሔር ፍቅር የኢየሱስን ሥራና የፍቅርን ፍሬ ያስከትላል እንጂ ተስፋው አያሳፍረንም (ሮሜ 5:5፣ዮሐ. 14፣12:23):: በ2ኛጴጥ.1:5-8 «..ትጋትን....በእምነታችሁ....በጎነትን....እውቀትን፣ ራስን መግዛትን ፣መጽናትን፤ እግዚአብሔርን መምሰልን ፣የወንድማማች መዋደድን...ፍቅርንም ጨምሩ...እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና» በማለት ያስተ ምረናል:: እንዲሁም ሐዋርያ ጳውሎስ በ1ኛቆሮ. 13:1-13 በክርስትና ሕይወት ውስጥ ፍቅር ተወዳደሪ የሌለውና እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻል:: ስለሆነም እውነተኛ ፍቅር ከሞት ይልቅ የበረታ

ነው፣ሁሉንም ያድናል፣ሁሉንም ያሸንፋል:: «እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ስጥቶአልና እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል» ይላል (1ዮሐ. 3:16::) ይህ ማለት ፍቅርን ምናባዊ ወይም ስሜታዊ ሳይሆን ተጨባጭና የሚተገበር መሆኑን ያመለክታል::

« እግዚአብሔር የፍቅር ሰዎች እንዲያደርገን፤
ራሳችንን እንፍቀድ ፍቅሩ እንዲገዛን::
ፍቅር የሌለው ሰው ጌታን እንዴት ያውቃል?
እርሱ እኮ ፍቅር ነው ፍቅሩን አሳይቶናል::

በፍቅር የሚምር በእግዚአብሔር ይማራል፤
ፍቅር የሌለው ለው ነፍስ ገዳይ ተብሏል::
መገለጥ ልሳኑ ሌላ ሁሉ ቢኖረን፣
ፍቅር ከሌለን ግን ሁላችን ከንቱ ነን::»

## 2.2.3. ክርስቲያን መሆናችንን ስለሚያሳይ

የዲቁና አገልግሎት የምንሰጠው ለመዳን ሳይሆን ስለዳንን ነው:: ሕይወት የሚገኘው በመልካም ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ነው:: ይህ ባይሆን ኖሮ ጌታ ኢየሱስን የሕይወታቸው ጌታ አድርገው በእምነት ያልተቀበሉት ሁሉ በመልካም ሥራቸው ብቻ ወደ መንግሥተ ሰማያት በገቡ ነበር:: አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወቱ ጌታና አዳኝ አድርጎ ሲቀበልና በእርሱ ምሪት መኖር ሲጀምር ክርስቲያናዊ የሆነ መልካም ምግባር በሕይወቱ መታየት ይጀምራል:: የብርሃን ልጅ የብርሃንን ሥራ ያደርጋልና:: ጌታ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኃላ ስለ ፍቅር ሲናገር፣ «እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ» (ዮሐ.13:35) ብሎ ፍቅርን የክርስትና ሕይወታችን መታወቂያ አድርጎ ገልጾታል::

አንድ ሰው በመዳኑ ምክንያት ከሚያሳያቸው መልካም ተግባሮች አንዱ ችግረኞችን መርዳት ነው:: የችግ ረኞች ረዳት የሆነው ጌታ ሕይወቱን በሚለውጥበት ጊዜ ቀድሞ ግድ ያልነበረው ሰው ሁሉ ወገቡን ታጥቆ የተቸገሩትን መርዳት ይጀምራል:: ሳጡትም ሁልጊዜ ርኅሩኅ ይሆናል:: ዘኬዎስ ጌታ ኢየሱስ ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ ከንብረቱ እኩሌታውን ለድሆች እንደሚሰጥ ተናገ ረ (ሉቃ. 19:1-10):: የፈረንሳዩ ተወላጅ ራኡል ፎልሮ ስለ «እውነተኛ ፍቅር» በሚናገረው መጽሐፋቸው ውስጥ፣ «ፍቅር የመንግሥተ ሰማያት በር መክፈቻ ነው:: የዓለምም ታላቅ ኃይል እርሱ ብቻ ነው::



የማይረታና የመፍጠር ኃይል ያለው እርሱ ነው» ብለዋል::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ችግረኞችን ሲረዱ የቆዩ ሰዎች ዋጋቸው በሰማያት ታላቅ ነው በማለት በማቴ 25፣34 - 36:40 ይህንኑን ያረጋግጣል:: «ንጉሡ በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል:- እናንተ የአባቴ ብሩካን፤ ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ:: ተርቤ አብልታችሁኛ ልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛ ልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና::... እውነት እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል»:: በጎ ሥራ የማይሠሩ ክርስቲያች እምነት መፈተሽ አለበት:: የክርስቶስ ልብ አለን ወይም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል ካልን በስም ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ሕይወት በሕይወታችን መታየት አለበት::

ስምማ ሞልቶናል ሥራ ግን የት አለ?
ሰው እግዚአብሐርን ሳይሆን ራሱን አታለለ::
ፍቅር ነው የወለደን አረ እንምሰል እርሱን፣
ወንድምን መጥላት ታዲያ ከማን ተማርን?

ቃሉ እንደሚናገር ራሳችንን እናስለምድ፣
ምሳሌ እየሆንን ወንድምን በመውደድ::
ልክ እግዚአብሔር እኛን እንዲሁ እንደወደደን
ባልንጀራችንን እንውደድ በሁኔታዎች ላይ ሳንወሰን::

## 2.2.4 እግዚአብሔርን ስለሚያከብር

እንደ እግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ የምናበረክታቸው አገልግሎቶች ሁሉ እግዚአብሔርን ያከብራሉ:: ጌታ እየሱስ በተራራ ስበከቱ «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ»(ማቴ 5:16) በማለት አስተምሮአል:: ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት የክርስቲያችን መልካም ሥራ ሲያዩ እንደሆነ ይህ ቃል ያረጋግጣል:: እግዚአብሔር ሊጠራን ፍሬያማ ሕዝብ እንድንሆን ይፈልጋል:: «ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል» (ዮሐ 15:8):: የጌታ ተከታይ መሆን ለሌሎች መትረፍ ነው:: ለሌሎች የሚተርፍ ሕይወት ስንኖር የሚደኑ ይበዛሉ:: ሐዋርያት ይኖሩት የነበ ረው የፍቅርና የአንድነት ኑሮ ዕለት ዕለት ነፍሳት እንዲጨምሩ ያደርግ ነበር:: በተግባራችን የክርስቶስን ምሳሌነት ብናሳይ ሌሎች

ስለ እኛ እግዚአብሔርን ያከብራሉ:: ሐዋሪያው ጳውሎስ የመቄዶንያና የአካይያ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች መካከል የነበሩትን ድሆች በመርዳታቸው እግዚአብሔርን እንዳከበሩ ይናገራል(2ኛቆሮ 9:11-13):: እውነተኛ ፍቅር ከሌሎች ጋር ማኅበራዊ ኑሮን መኖር ብቻ ሳይሆን ራሳችንን ለሌሎች መሥዋዕት ማድረግ ነው:: በልግስናችን ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያከብሩ ስናይ ታላቅ ደስታ ይሰማናል:: እርሰ በርስን መዋደድ እውነተኛ የደስታ ማግኛ መንገድ ነው:: በዚህ የበረከት ሕይወት መኖር ራሱ በረከትን መለማመድ ነው::

## 2.2.5. የተቸገሩትን መርዳት በረከት ስለሆን

ካለን ነገር ለሌላቸው ማካፈል ኪሳራ ሳይሆን ማትረፍ ነው:: ማጉደል ሳይሆን መባረክ ነው:: ችግረኞችን መርዳት የፍቅር ምልክት ነው:: በተጨማሪ ፎልሮ «ማፍቀርም ማካፈል እንጂ መስጠት ብቻ አይደለም:: በእውነተኛ ፍቅር የሚኖር ሰው ሁልጊዜ ድል አብራው ትኖራለች» ብለዋል:: ችግረኞችን የሚረዱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካቸዋል:: «እጅህን በምትጥልበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ስለዚህ በሥራህ ሁሉ ይባርክሃልና (ዘዳ 15፣10):: «በተነ ለምስኪችም ሰጠ ጽድቁ ለዘላለም ይራል » (2ቆሮ. 9:10) ይላል:: ቅዱሳን የተቸገሩትን ሰዎች በሚረዱበት ጊዜ እግዚአብሔር በሥራቸው ሁሉ ይባርካቸዋል:: ጽድቃቸውም ለዘላለም ይኖራል:: እግዚአብሔር የሚዘሩትን ዘር ይሰጣቸዋል፣ ያበረክትላቸዋል፣ የጽድቃቸውንም ፍሬ ያሰድጋል:: የእቅማችንን ያህል መርዳት ለራሳችን በረከት ነው:: «ስጡ ይሰጣችሁማል፣ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና የተጨቆነና የተነቀነቀ፣ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል»(ሉቃ.6:38) ይላል:: መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው:: ብዙዎቻችን የንፉግነት ሕይወት ስለሚያጠቃን አንሰጥም፣ ስለማንሰጥም አንባረክም:: ንፉግ ሰው እውነተኛ ድሀ ነው:: መሬት ለገበሬ በየዓመቱ የምርትን በረከት የምትሰጠው ጥቂት ተዘርቶ ነው:: የትኛውም ነገራችን እንዲባረክልን ከፈለግን እንደ እግዚአብሔር ቃል ብንሰጥ በረከቱ ወደ እኛ ይመጣል:: «ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሠራት አንታክት»(ገላ. 6:9-10) ::

መጽሐፍ ቅዱስ «ያለውን የሚበትን ሰው አለ፤ ይጨመርለታልም፤ ያለ ቅጥ የሚነፍግ ሰውም አለ ፤ ይደኸያልም» (ምሳ.11:24) ይላል:: እንግዲህ ለመባረክ ከፈለግን የተቸገሩትን ወገኖች እንርዳ:: ችግረኞችን መርዳት ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር በረከቶችን መካፈል እንደሆነ ነቢዩ ኢሳያስ በምዕ.58:6-12 ተናግሮአል:: የተቸገሩትን መርዳት በረከት እንደሆነ አላይ ከተጠቀሱት



የእግዚአብሔር ቃሎች ተገንዝበናል::

የዲቁና አገልግሎት በምክንያታዊ አስተሳሰብ **እኛ በሂሳብ** አሰልተን ማግኘት ያለብንን በረከት ከወዲሁ **ለመቆጣጠር** የምናደርገው ተግባር አለመሆኑን መረዳት ይገባናል። በረከት **መለኮ**ታዊ ስጦታ ሲሆን የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሞ መገኘት ግን ለእኛ ለክርስቲያች የተሰጠን ኃላፊነት ነው::

## 2.2.6. የተቸገሩትን መርዳት ተገቢ ስለሆን

የተቸገሩትን መርዳት የሚገባን ክርስቲያኖች ስለሆንን ብቻ አይደለም:: ሰዎች በመሆናችን ብቻ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረን ስለሆንን ነው:: የተቸገረውን ሰው ሁሉ መርዳት ይገባናል:: ከሉቃ. 10:29-37 ባለው ክፍል አንድ ሳምራዊ በወንበዴዎች እጅ የተደበደበውን ሰው እንደረዳ ጌታ ይናገራል:: አይሁዳውያንና ሳምራውያን ምንም ዓይነት መቀራረብና ዝምድና አልነበራቸውም:: ሳምራዊው የአይሁድን እምነት የሚከተል ሰው አልነበረም:: ምንም ዓይነት ጥቅም ሳይሻ ሰው ከመሆኑ የተነሣ ብቻ በውስጡ በነበረው ርኅራኄ ሲረዳው ቻለ:: በሰዎች መካከል ምንም ዓይነት የዘር፣ የጎሳ፣ የሃይማት፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልዩነት ሳናደርግ በሰብአዊነቱ ብቻ ሰውን መርዳት ከሁላችንም ይጠበቃል:: ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገልግሎት ስላበረከተች አንዲት ክርስቲያን ሴት እንመልከት::

በአዲስ አበባ ከተማ የውጭ ዜጎችን በማሸት(ማሳጅ) አነስተኛ ገቢ የምታገኝ አንዲት ክርስቲያን ሴት ነበረች:: ከዕለታት አንድ ቀን ይህች ሴት አንድ የታመመና የሚረዳው አጥቶ በአስፋልት ዳር የወደቀ ሰው አገኘች:: ወደ እርሱም በመቅረብ በፍቅር ታነጋግረው ጀመር:: እርሱም የዕለት እንጀራና መታከሚያ ገንዘብ አጥቶ ሞትን በመጠባበቅ ላይ መሆኑን ነገራት:: ይህች ክርስቲያን እኅት በሁኔታው አዝና በኮንትራት ታክሲ ሆስፒታል ወሰዳ አስተኛችው:: በሚያስፈልገው ሁሉ እየረዳችው እንዲከታተሉት ለሌሎች ወገኖች ነግራ አሳከመችው:: ከብዙ ጊዜ በኋላ ይህ ሰው ድኖ፣ ጥሩ ልብስ ለብሶና አምሮበት በአንድ መንፈሳዊ ስብሰባ ላይ ይህችን ሴት ያገኛትና ሰላም ሊላት በታላቅ ደስታ ሲቀርባት እርስዋ ግን ማን እንደሆነ ስላላወቀች ይቅርታ! የምታውቀኝ አይመስለኝም ተሳስተሃል አለችው:: እርሱ ግን ያኔ ከአስፋልት ዳር አንሥተሽ የረዳሽኝ እኔ ነኝ በማለት ራሱን አሳወቃት:: እርሷም በመደሰት ሰላምታ ከሰጠችው በኋላ ስለዳነ እግዚአብሔርን አመሰገነች:: ችግረኞችን የምንረዳው ከትርፋችን ሳይሆን ከእግዚአብሔር ባገኘነውና በተለማመድነው የፍቅር ግብግ

ቋሚና ዘላለማዊ ነው። የእግዚአብሔርን ፍቅር የተለማመደ ሰው የወንድሙንም ፍቅር ይለማመዳል። ተከታዮቹ ይህ ፍቅር እንዲኖራቸው ኢየሱስ ይፈልጋል። «እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ» (ዮሐ 13:34-35) በማለት ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር እኛን በወደደበት ፍቅር ሌሎችን እንድንወድ ይፈልጋል። የዚህ ዓይነቱ ፍቅር አጋፔ ተብሎ ይጠራል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛቆሮ. ምዕ. 12 ውስጥ ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንደተሰጡ ከተናገረና ስጦታዎቹም ጠቃሚዎች መሆናቸውን ካሰረዳ በኋላ በ13ኛው ምዕራፍ ስለ ፍቅር ያስተምራል። ወደ ትምህርቱ ከመግባቱ በፊት ግን «ፍቅር» ከሌለ የአገልግሎት ስጦታዎች ሁሉ «ከንቱ» ናቸው በማለት ያብራራል። ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ ማሰሪያ ነው። አገልግሎታችን በፍቅር ከተከናወነ እውነተኛ የሆነውን የክርስትና ሕይወት ያንፀባርቃል። የእግዚአብሔር ቃል «...ልጆች ሆይ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ» በማለት ስለ ተግባራዊ ፍቅር ያስጠነቅቀናል (1ዮሐ. 3:16-18)። የብዙ ችግረኞች ጥያቄ ከገንዘብና ከቁሳዊ አቅርቦት ያለፈ ነው። እውነተኛውን ፍቅራችንን ይሻሉ። ምክንያቱም ቁሳዊ እርዳታ አካልን ሲለውጥ፣ ፍቅር ግን ውስጣዊ ሕይወትንና መንፈስን በደስታ ይለውጣል። ከቁሳዊ እርዳታ ይልቅ ፍቅራችንን ብናካፍላቸው እጅግ ደስተኞች ይሆናሉ። የችግረኞች ተስፋ የሚታደሰውና ደስታቸው አጥፍ ድርብ የሚሆነው በሀብት ላይ ሀብት ሲጨምሩላቸው ብቻ ሳይሆን በማያልቅ ፍቅር ሲቀርቡአቸው ነው። እውነተኛ ፍቅር እግር ስላለው ወደ ችግረኞችና ድሆች ይጓዛል፣ ዐይን አለው ችግረኞችን ያያል፣ ልብ አለው ለችግረኞች ይራራል፣ አእምሮ አለው ለችግረኞች ያስባል፣ እጅ አለው ከበረከቱ ያካፍላል፣ እምነት አለው ለችግረኞች ይጸልያል። ፍቅር በጎደለው ነገር ሁሉ ይደርሳል።

2.. ራስን በመስጠት

ከመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ልንማር እንችላለን። ችግረኞችን ለመርዳት ከመነሣታቸው በፊት አስቀድመው በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታና ለአገልጋዮቹ እንደ ሰጡ ተመስክሮላቸዋል። አስቀድሞ ራሱን ለእግዚአብሐር የሰጠ ክርስቲያን ለችግረኛ ወንድሙ ለመስጠት አይከብደውም። ከየትኛውም ስጦታችን በፊት ራሳችንን መስጠት ቅድሚያ አለው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ምእመናንም የነገራቸው(12:1-2) ይህንኑ ነበር፣ ራስን መስጠት ለአእምሮ የሚመች አገልግሎት መሆኑን ያብራራል።



እግዚአብሔር ከስጦታችን ይልቅ አስቀድሞ እኛን ይፈልጋል። አንድ ጊዜ አንድ ሀብታም ገንዘብ በኪሱ ሳይዝ ወደ መንገድ ወጥቶ ሳለ አንድ ለማኝ አገኘውና ገንዘብ እንዲሰጠው ለመነው። ሆኖም የሚሰጠው ገንዘብ ባይረውም ቆም አለና ይቅርታ አድርግልኝ ምንም አልያዝኩም በማለት መለሰለት። ለማኙም ይህን ሀብታም የእኔ ጌታ በጣም አመሰግንሃለሁ አለው። ሀብታሙ ሰው ግን የሚቀልድ መስለውና ለምን ታመሰግነኛለህ? አለው። ለማኙም ከገንዘብ በላይ ለእኔ ጊዜህን ሰጥተህ ቆም ብለህ ማነጋገርህ ለእኔ ትልቅ ስጦታ ነው አለው። ይህም ለችግረኛ ሰው ከገንዘባችን ይልቅ ራሳችንንና ጊዜያችንን እንድንሰጥ ያሳየናል። ቁሳዊ ነገርን ከመስጠቱ ይልቅ ራሳችንንና ጊዜያችንን መስጠቱ ነው ከባድ የሆነው። አስቀድሞ ራሱን ለጌታ የሰጠ ክርስቲያን ለጌታ ስለሚስማማ ለራሱም ለሰውም ይስማማል። ወደዚህ ውሳኔ ለመድረስ እንደ ጳውሎስ ራስን መካድ ያስፈልጋል (ፊል. 3:4-11)። ራሱን የካደ ክርስቲያን መደገፊያውና ትምክህቱ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለጌታ ብሎ ጣል ያደርጋል። እንደ ጌታ ፈቃድ ብቻ እየተ መላለሰ አምላኩን ያከብራል። ሰውነቱንም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ይሰጣል። ሰው ሁለንተናውን ለእግዚአብሔር ሰጠ ማለት ያለውን ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጠ ማለት ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ይህን ሰው እውነተኛ አገልጋይ አድርጎ ይጠቀምበታል።

2.3.3. ጊዜያችንን በመስጠት

ጊዜ እግዚአብሔር ለሁላችንም የሰጠን ክቡር ስጦታ ነው። እያንዳንዱ ደቂቃ በገንዘብ የማይገኝ ውድ ነገር ነው። ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ጊዜ በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባናል። ለአገልግሎት፣ ለግል ሥራ፣ ለእረፍት ጊዜያችንን በጥንቃቄ መመደብ ያስፈልገናል። ማንኛውንም የእግዚአብሔርን ስጦታ ለክብሩ እንደምንጠቀም ሁሉ፣ ጊዜያችንንም እግዚአብሔር በሚከብርበት ነገር ልናውለው ይገባል። ከስንፍና ሓሳቦች መራቅ ጊዜን ለመጠቀም ይረዳል። ይሁን እንጂ ለአንድ አገልጋይ የተደራረበ አገልግሎት ካለው አንዱንም በታማኝነት ሊወጣ አይችልም። ቤተሰቡንም ሊጎዳ ይችላል። ስለዚህ የጊዜ አመራርን (Time Management) በሚገባ መጠቀም ያስፈልጋል።

ጊዜ ከችግረኛ ሰው ጋር ለመገናኘት በጣም አስፈላጊ ነው። ብዙ ችግረኞች ከስጦታችን በላይ ጊዜ ሰጥተን እንድናወያያቸው ይፈልጋሉ። ረጋ ብለን በጥሞናና በትዕግሥት ስለ ችግራቸው መስማት ከፈለግን ጊዜ መስጠት አለብን። ጊዜ መድበን እንድንጸልይላቸውም ይፈልጋሉ። የተቸገሩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሰው

ረሀብተኞች ናቸው። ማን ጓደኛ ያደርጋቸዋል? ማን ያስጠጋቸዋል? ብዙ ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አይጎበኙንም ብለው ሲናገሩ ይሰማል። ምናልባትም ከምእመናን ቊጥር ብዛት የተነሣ ሊሆን ይችላል። አገልጋዮች ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው እንዲሰጡ ችግረኞች ይፈልጉአቸዋል። ስለዚህ ለዚህ አገልግሎት ከእግዚአብሔር ሽክም የተቀበሉ ተጨማሪ አገልጋዮች(ዲያቆናት) ያስፈልጋሉ።

### 2.3.4. በትሕትና

አንድ ጊዜ የአንድ ሆስፒታል ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ አድርገው የጽዳት ሥራ አንሠራም ባሉ ጊዜ አንድ እፍረቃዊ ጳጳስ ተጠርተው ሄዱ። ጳጳሱ ሠራተኞቹን አባብለው ወደ ሥራቸው መመለስ ባልቻሉ ጊዜ ሸርጡን፣ ባልዲውንና መጥረጊያውን ለእኔ ስጡኝ አሉ። የማጠቢያ ክፍሎቹንና ሽንት ቤቶቹን ራሳቸው ማጽዳት ጀመሩ። ሠራተኞቹም አፍረው በየተራው ሥራቸውን ቀጠሉ። ከዚህ የምንማረው ከቃላችን (ከንግግራችን) ይልቅ ተግባር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ነው። በትሕትና ወደ ሰዎች መቅረብ ለአገልግሎት ራስን የመስጠት ምልክት ነው። ሌላውን የሚያገለግል ሰው ራሱን በከፍታ ቦታ ማስቀመጥ አይችልም። ነገር ግን በትሕትና ዝቅ ብሎ ለማገልገል ራሱን ያዘጋጃል። ሐዋርያው ጴጥሮስም ሆነ ያዕቆብ እግዚአብሔር ለትሑት አገልጋይ ጸጋን ሲሰጥ ትዕቢተኛውን ግን እንደሚቃወም በመልእክቶቻቸው ጽፈዋል(1ጴጥ. 5:5፣ያዕ 4:6)።

እግዚአብሔር በሰጠን የአገልግሎት ሥፍራ ሆነን ታላላቆች ተብለን ለመጠራትና ለመታወቅ መፈለግ የትዕቢት ምልክት ነው። ትሑታን ግን እግዚአብሔርንም ሰውንም ለማገልገል ይመቻሉ። የዲቁና አገልግሎት የትሕትና፣ የዝቅተኝነትና ራስን ለሌሎች በረከት አድርጎ የማቅረብ አገልግሎት ሲሆን በዚህ ረገድ ፍጹም ወደር የማይገኝለት አገልጋይ ኢየሱስ እንደሆነ እናውቃለን። እርሱም ለእኛ ምሳሌ ትቶልን አልፎአል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵ. ምዕ. 2:5-8 ባለው ክፍል ውስጥ የኢየሱስ ተከታዮች የክርስቶስን ምሳሌነት እንዲከተሉ ያስተምራል። በትምህርቱም የወገንተኝነትን ሥራ አትሥሩ፣ ከንቱ ውዳሴን ከሰዎች አትፈልጉ፣ ባልንጀራችሁ ከእናንተ እንደሚሻል በትሕትና ቊጠሩ፣ በማለት ስባልንጀራችን ማሰብ እንዳለብን ያስገነዝበናል። ስለ ትሕትና አገልግሎት እውነተኛና መሠረታዊ ተግባሮችን ለመረዳት (በፊል 2:1-11) ያለውን ክፍል በድጋሚ መመልከት ይጠቅማል። ክርስቶስ



ከእግዚአብሔር ጋር በባሕርይ እኩል ነው። ነገር ግን የባርያን መልክ ወሰደ። ሥልጣን ሁሉ የእርሱ ሲሆን አልተቀናቀነም። የማዘዝ ሥልጣን እያለው ግን ታዘዘ። አምላክ ነው፤ ነገር ግን ሰው ሆነ። ክብርና ብፅዕና ሁሉ የእርሱ ነው። ነገር ግን ድሀ ሆኖ መኖርን መረጠ። ራሱን ባዶ አደረገ። ለምን ይህን ሁሉ አደረገ? አንዳች ጥቅም ለማግኘት ይሆን? አይደለም። እኛን ስለ ወደደ ብቻ ይህን ሁሉ አደረገ። ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለዓለም ሕዝብ ለማሳየት ሲል ትሑት አገልጋይ ሆነ። በትሕትና ለማገልገል የሚፈልግ ሰው በተጨማሪ ለለትሕትና የሚከተሉትን ነጥቦች ቢመለከት ሊረዳው ይችላል።

ትሕትና፡-

- ራስን ዝቅ ማድረግ፣
- ሌላው ሰው እንዲጠቀም መፈለግ፣
- ሌላው ሰው ከእኛ እንደሚሻል ማሰብ፣
- የጸጋ መቀበያ መንገድ መሆኑን ማወቅ (1ጴጥ 5:5)፣
- ከሌላው መማር የምንችልበት መሆኑን መረዳት (ሉቃ. 10:37-42)፣
- በእግዚአብሔር ዓይን ከፍ የምንልበት እንደሆነ ማስተዋል (ኢሳ. 57:15) እና ሌሎችንም ያካትታል።

### 2.3.5. ከጉድለትም ከማጣትም በመስጠት

የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ድህነታቸው ጥልቅ ነበር። ይሁን እንጂ ለተቸገሩት ወገኖች በመስገስ ይታወቁ ነበር። «እንደ አቅማቸው መጠን ከአቅማቸውም የሚያልፍ ነገር ወደው እንደሰጡ ተመስክሮላቸዋል (2ቆሮ. 8:1-3)። መስኮታዊ ፍቅር አይቻልም የተባለውን እንዲቻል ያደርጋልና። እኔ ደካማ ነኝ ምንም የለኝም የሚለውን ሰው አንተ ብርቱ ነህ ድህም አይደለህም ይለዋል። ብዙ ሰዎች ችግረኞችን ላለመርዳት ድህነታቸውን እንደ ምክንያት ያቀርባሉ። እንዲረዱ ሲጠየቁ የለንም ይላሉ። የተቸገሩትን አለመርዳት የሀብት ሳይሆን የፍቅር ማነስን ያሳያል። ሰዎች ሃብታቸውን ይወዳሉ። ለለ አግባብ ስለሚጠቀሙበት ሀብታቸው ያልቅባቸዋል። ሀብትን በአግባብ መጠቀም ለእግዚአብሔር ክብር ማዋልና ችግረኛውንም መርዳት ነው። እውነቱን ያየን እንደሆነ ለማኝ ካገኘው ነገር ምንም ያላገኘውን ለማኝ መርዳት ይችላል። እውነተኛ ፍቅር ካለ የለስተ እጅ ይዘረጋል። ከዚህ ሐሳብ በመነሣት ጌታ ኢየሱስ

በቤተ መቅደስ ውስጥ መባ የሚጥሉትን አይቶ ያላትን ምንም ሳታስቀር ከጉድለትዋ የጣለችውን መበለት ከሁሉ አብልጣ መጣልዋን ከተናገረው ቃል መረዳት ይቻላል (ማር. 12: 41-44)::

ሰዎች ለችግረኞች ማካፈል የማይፈልጉት ስለሌላቸው ብቻ ሳይሆን ያላቸው ነገር የእግዚአብሔር እንደሆነ ስለማያስተውሉም ነው:: ለምሳሌ በአንድ ከተማ ጥግ የሚኖሩ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት ለዲቁና ስልጠና እንዲሄዱ ለታክሲ የተሰጣቸውን ትንሽ ገንዘብ ለዲቁና አገልግሎት ለማዋል ብሰው በአውቶቡስ በመሄድ እንድ ላይ አሥራ ሁለት ብር አተረፉ:: በዚህ ብር ጥቂት ገንዘብ ጨም ረውበት ጨርቅ ገዙ:: በአንድ ክርስቲያን ልብስ ሰፊ አማካይነት አሰፍተው በስድሳ ብር ሸጡ:: እግዚአብሔርን ጠይቀው ለየትኛው ችግ ረኛ ቅድሚያ እንደሚሰጡ ካወቁ በኋላ ፍጹም ድሀ ለሆነችው አራስ ሴ ት ብር 20.00፣ ለአንድ ድሀ ተማሪ የትምህርት ቤት ክፍያ ብር18.00 ፣ በቀረው ብር ለአንድ መድኃኒት መግዛት ሳልቻለ በሽተኛ መድኃኒት ሊገዙ ቻሉ:: እነዚህ ምንም የሌላቸው አገልጋዮች ከልብ ለለተነሣሡ ብቻ ከጉድለታቸው ከለጡት ልግስና የተነሣ ችግረኞች ወገኖችን እንዴት እንደረዱ ስንመለከት፤ ከዚህ ያለፈ ሀብት ያለን ሰዎች የበለጠ ማድረግ እንደምንችል እንገነዘባለን::

## 2.3.6. በደስታ

ደስታ ብልጭ ብሎ ድርግም የሚል ስሜታዊነት አይደለም:: የመቄዶንያ ምእመናን በውስጣቸው ከነሰረ የተትረፈረፈ የመንፈስ ቅዱስ ደስታ የተነሣ በቂ ሀብት ሳይኖራቸው የተቸገሩትን ድሆች መርዳት ቻሉ:: ጳውሎስ፣ ጢሞቴዎስና አፍሮዲጡ የመባ ጥያቄ ሰመዳን ብሰው ሳይሆን ከእውነተኛ ደስታ የተነሣ ችግረኞችን ይረዱ ነበር (2ኛቆሮ. 8:2):: ደስተኛና መልካም ልብ ሲኖር ፊት ያበራል:: በኀዘን የምናመጣውን ማንኛውንም ስጦታ እግዚአብሔር አይቀበለውም:: የተቸገረውን ሰው መርዳት ለእግዚአብሔር እንደማድ ረግ ይቄጠራል:: «... እውነት እላችኋለሁ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ...»(ማቴ.25:40):: በደስታ ከለገስን እኛም ሆንን ተረጂው ደስ ይለናል:: «እግዚአብሔርም በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም» (2ኛቆሮ. 9:7)::

## 2.3.7. ውለታ ባለመጠበቅ

በየትኛውም ሀገር ሰዎች በባሕላቸው ይረዳዳሉ:: ኢትዮጵያም በመረዳዳት ባሕል ከሚታወቁ ሀገሮች አንዷና የመጀመሪያዋ ናት::



ሆኖም ግን ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲረዳዱ ብዘውን ጊዜ በጥቅም ላይ የተመሠረተ ይመስላል:: ተረጂው ለረጂው መክፈል ያለበት ዋጋ ወይም ውለታ ሊፈጥር ይችላል:: ማኅበራዊ መረዳዳት መልካም ቢሆንም እኛ ክርስቲያኖች ግን እውነተኛ በሆነ ፍቅር መንፈሳዊ ዕርዳታን ለሁሉም ሰው ማድረግ ይገባናል:: ለእርዳታችን አጸፋ ወይም ብድራት የምንፈልግ ከሆነ የፍቅር አገልግሎት አይሆንም:: ዋጋችንን በምድር የምንቀበል ይሆናል (ማቴ. 6:2-4)::

የእግዚአብሔር ቃል ግን ውለታ መላሾች የማይሆኑትን እንድንረዳቸው ወደ ቤታችንም ወስደን እንድንመግባቸው ይነግረናል (ሉቃ.14:12-14):: ግብዣ ስናዘጋጅ ብዙ ጊዜ ሀብታሞችን፣ ባለሥልጣናትን፣ የተማሩትን፣ ትልልቅ ሰዎችን መጥራት እንወዳለን:: እግዚአብሔር ግን ከዚህ ያለፈ ነገር እንድናደርግ ይመክረናል:: ወደ ግብዣህ ምንም ነገር የሌላቸውን ሰዎች ጥራ ነው የሚለው:: ይህ ሲሆን በለማይ ከጌታ ዘንድ ልዩ ብድራት አለ:: በአጠቃላይ ዲቁና ውለታን ባለመጠበቅ የሚፈጸም አገልግሎት በመሆኑ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር ይገለጽበታል::

## 2.3.8. በእምነት

በኢትዮጵያ በገጠርና በከተማ ያለውን ችግር ስንመለከት ሊያስፈራን ይችላል:: አቅም የሰንም እንዴት መርዳት እንችላለን ብለን ተስፋ እንቈርጥ ይሆናል:: ጌታ በምድረ በዳ ከሴቶችና ከሕፃናት ሌላ አምስት ሺህ ሕዝብ እንደመገበ ከቃሉ እናያለን (ማቴ 14:15-21፣ ማር. 6:35-44፣ ሉቃ 9:12-17):: ደቀ መዛሙርቱ መጀመሪያ እምነት አልነበራቸውም:: ነገር ግን ጌታ ያላቸውን ሰምተው ሕዝቡን ሃምሳ ሃምሳ እያደረጉ በሳር ላይ አስቀመጡ:: ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራ ከእጁ ተቀብለው ለሁሉም ሰጡአቸው:: የተረፈውንም አሥራ ሁለት መሶብ በደቀ መዛሙርቱ ቍጥር አነሡ:: በዘመናችንም ጌታ ይህንን ማድረግ ይችላል:: አንድ ጊዜ በማዕከላዊ ደቡብ ሲዶስ በሆሣዕና ማኅበራዊ ጤና፣ ከቡና ቤት ወደ ጌታ የመጡ ሴቶች የሚ ረዱበት በጀት በድንገት በግንቦት ወር ተቋረጠ:: በወቅቱ የሚረዱ አሥራ ሁለት ሴቶች ነበሩ:: እግዚአብሔር ደግሞ እነርሱን ለምታገለግል እኅት የቃሉን ማስረጃ ከ2ኛ ነገሥት 4:1-7 ያለውን ክፍል በመስጠት «አታሳንሺ፣ አገልግሎትሽን ቀጥይ፣ ባዶዎች ሁሉ ይሞላሉ» የሚል ድምፁን አሰማ:: እርስዋም ከግንቦት እስከ ጥር ወር ድረስ ያለ ምንም በጀት በእምነት አገልግሎትዋን ቀጠለች:: በዚህ ወቅት ሃያ አዳዲስ ነፍሳት ተጨምረው ሠላሳ ሁለት ነፍሳት ሆኑ:: እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ዓይነት መንገድ እየረዳቸው ሠራተኞቹም

እዳዲሶቹም ያለእንዳች ጉድለት ለመቋቋሚያ የሚያስፈልጋቸውን አግኝተው በእምነት እየበረቱ ሄዱ፡፡ የእኛ እምነት አይነስ እንጂ እግዚአብሔር በጥቂት ነገር ሰውን ማኖር ይችልበታል፡፡

እምነት ሰዎች ራሳቸው የሚፈጥሩት ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ስጦታ ነው፡፡ ይህ ስጦታ አለን ማለት ሥራ ሳንሠራ መና ከሰማይ ይወርድልናል ብሎ የመጠበቅ መንገድ አይደለም፡፡ ነገር ግን እምነት ያለው ሰው በጥቂት ነገር በእግዚአብሔር ታምኖ ለመሥራት የተዘጋጀ ትጉህ ሠራተኛ ይሆናል ማለት ነው፡፡

#### 2.3.9. በምሥጢር

አገልግሎታችን የግብዝነትና የታይታ ሊሆን አይገባም፡፡ «ምጽዋት (መባ) ስትሰጥ በስውር ይሁን፡፡ ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፡፡ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጽ ይከፍልሃል» (ማቴ 6:3-4)፡፡ የተቸገሩትን ስንረዳ በሕዝብ ሁሉ ፊት ለጋስ ተብለን ለመጠራት መሆን የለበትም፡፡ የምንሰጠውን ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ የዲቁና አገልግሎት አስተባባሪዎች በኩል ብናደርገው ከማንም ውዳሴ አንቀበልም፡፡ ችግረኞችም ሌትና ቀን በምንሄድበት መንገድ እየጠበቁን አያወድሱንም፡፡ ስጦታችን ለዝናና ለሙገሳ መሆን የለበትም፡፡ ዋጋችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ይሆንልናል፡፡ ስጦታችን በምሥጢር ይሁን ስንል ስላደረግነው የልግስና አገልግሎት የቤተ ክርስቲያን ደረሰኝ ወይም ፊርማ አያስፈልግም ማለታችን አይደለም፡፡ በደረሰኝ መስጠት ለአሠራሩ ግልጽነትና ጉልህነት ጠቀሜታ አለው፡፡

በምሥጢር ማገልገል አሰብን ስንል ገንዘብን ለሰ መስጠት ብቻ ማሰብ በቂ አይሆንም፡፡ በምክር አገልግሎታችን ወቅት የሰውን ምስጢር መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎች ውስጣዊ ነገራቸውን ለሁሉ ሰው መግለጽ አይፈልጉም ይሆናል፡፡ ስለሆነም ምሥጢራቸውን ሁሉ የመጠበቅ ኀላፊነት አለብን፡፡

#### 2.3.10. በእቅድ

የዲቁናን አገልግሎት በግልም ሆነ በጋራ ለመፈጸም ለማገልገል እቅድ ያስፈልጋል፡፡ ማንኛውም ግለሰብ ባለው የገቢ ምንጭ መጠን ለሚጠቀምባቸው ነገሮች ዕቅድ ያወጣል፡፡ በዕቅዱም መሠረት ይኖራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የዲቁና አገልግሎት ለመስጠት ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የሚገቡን ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ ካለን ገንዘብ፣ ጉልበት፤ ዕውቀት፤ ጊዜ፤ ቊሳቊስ...ወዘተ በቀን በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት ውስጥ ምን ያህል እንደሚያስፈልገን በመገመት ለንት ለንተኛ ውን ደግሞ ለዲቁና አገልግሎት ማዋል እንዳለብን በጥንቃቄና



በማስተዋል ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ ችሮታ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚደረግ ከሆነ ዘለቄታ ያለው ስለማይሆን ከቤተሰብ ጋር በመወያየት የታቀደ ነገር ቢሆን እጅግ ይመረጣል፡፡

የማኅበረ ምእመናን የዲቁና አገልግሎት በተመሳሳይ ሁኔታ በተቀነባበረ መልኩ በዕቅድ የሚሠራ አገልግሎት ነው፡፡ አንዲት ማኅበረ ምእመናን በአንድ ዓመት ውስጥ ስንት ዲያቆናትንና ምእመናንን መቼ? እንዴት? በምን? እቅም ማሠልጠን እንደምትችል ማቀድ ያስፈልጋታል፡፡ ስንት ሰዎችን መርዳት እንደሚያስፈልግ ማቀድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም «የዲያቆናት ኀላፊነት» የሚለውን ርእስ ይመልከቱ፡፡

### 2.4 ሥልጠናና አደረጃጀት

#### 2.4.1 ያልተቀናጀና የተቀናጀ የዲቁና አሠራር

የሰዎችን ዕለታዊ ችግር ለማስወገድ ብቻ ሲባል ጥቂትና ጊዜያዊ እገዛ አድርገን ለዘለቄታ የሚሆናቸውን የመፍትሔ መንገድ ባንቀይስ ምንም ጠቀሜታ ሊሰጣቸው አይችልም፡፡ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ አገልግሎታችንን ብንፈጽም ታላቅ ሥራ እንሠራለን፡፡

##### ሀ. ያልተቀናጀ ዲቁና

በሰብአዊ ርኅራኄ ተነሣስተን በግል የምናደርገው እርዳታ ያልተቀናጀ ዲቁና ተብሎ ይታወቃል፡፡ ያልተቀኛጀ ዲቁና ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ጠንካራ ጎን የምንለው አገልግሎቱ የኮሚቴን ውሳኔ በመጠበቅ ጊዜ ሳይወስድ አፋጣኝ እርዳታ ሲሰጥ ነው፡፡ ደካማ ጎን የምንለው ደግሞ የችግሩ መንስኤና መፍትሔ ምን እንደሆነ ጥናት ሳይደረግ በስሜታዊነት የሚሰጥ ልግስና ነው፡፡ ይህም አሠራር ክትትል፣ ሪፖርትና ግምገማ አይታይበትም፡፡ በዚህ አሠራር ችግረኛ በትክክል ቢረዳም ከረዳው ግለሰብ ጋር ባለውለተኛነትን ይፈጥራል፡፡ ብዙውን ጊዜ ችግረኞችን ለዘለቄታው አይረዳቸውም፡፡ ራሳቸውን ወደሚችሉበት ደረጃም አያደርሳቸውም፡፡ አንዳንዴ አገልግሎቱ ችግራቸውን መናገር ለሚችሉት ብቻ የሚሰጥ ሲሆን፣ አጋጣሚን ጠብቆም ሊደረግ ይችላል፡፡ ይህ አሠራር እስከ ዛሬ በተለምዶ በቤተ ክርስቲን ውስጥ ሲሠራበት ይታያል፡፡

ሰ. የተቀናጀ ዲቁና

የምእመናንን የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የችሎታ፣ የጉልበትና የጊዜ እርዳታ በማስተባበር የተቸገሩትን መርዳት ማለት ነው። እርዳታ ጊዜያዊ ወይም ዘለቄታዊ ሊሆን ይችላል። ዋናው ነገር ግን ራእዩ ያላቸው ምእመናን በላቸው ነገር በዲቁና እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ማድረግ ነው። የተቀናጀ ዲቁና የሚያስተባብር አካል ይኖረዋል። አስተባባሪው አካል ግለሰብ ወይም ቡድን ሊሆን ይችላል። የተቀናጀ ዲቁና ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ በጥናት ላይ የተመሠረተ፤ ክትትል ያለውና ሪፖርትና ግምገማም የማይታይበት አሠራር መኖር አለበት። ለችግረኛው እርዳታ ከመደረጉ በፊት ለዘለቄታ መፍትሔ እንዲሆን ስለ ሁኔታው፣ ስለ ዝንባሌውና ስለ ችሎታው፣ ወዘተ ማጥናት ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ አገልግሎቱ ግቡን ላይመታ ይችላል። ይህ ዓይነት አገልግሎት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት።

1. በአጋጣሚና በስሜት የሚሰጥ ሳይሆን በሁሉም ምእመናን ኃላፊነትና ለእያንዳንዱ ሰው በተሰጠው መክሊት በመጠቀም ላይ ተመሥርቶ በማስተዋል የሚሰጥ እርዳታ ይሆናል።

2. ተረጂዎቹ በሥራ እንዲጠመዱና ስለ ሥራ ማሰብ፣ ማቀድና መተግበር እንዲማሩ ያደርጋቸዋል። ይህም ሰዎች ከስንፍናና ተስፋ ከመቊረጥ ተላቅቀው ሥራን እንዲሠሩ የሚያበረታታ ነው (2ተሰ. 3:6-13)።

3. አንድን ችግረኛ ሁልጊዜ መርዳት አስቸጋሪነት ስላለው በተቀናጀ መልኩ መሥራት ለረጂዎቹም ሆነ ለተረጂው ሸክምን ያቀላል። ችግረኛውን ከችግሩ አውጥቶ ምርታማ ያደርገዋል።



4. በዚህ አገልግሎት ችግረኛውን ከችግርና ከልመና ማውጣት ለራስ፣ ለኅብረተሰብና፣ ለአገር ትልቅ ጥቅም አለው። ይህ ሰው አንድ ቀን ከድህነቱ ተላቅቆ ሀብት ማፍራትና ሌሎች ችግረኞችን መልሶ መርዳት ወደሚችልበት ደረጃ ይደርሳል።

ያልተቀናጀ ዲቁና ከዚህ በፊትም በኅብረተሰቡ መካከል እየተሠራበት ያለና የሚኖር ቢሆንም እንኳ ችግረኞችን ለመርዳት የተቀናጀ ዲቁና ውጤታማነት አለው።

## 2.5. የዲቁና አገልግሎት በገጠርና በከተማ

### ሀ. በገጠር

በገጠር ውስጥ ችግሮቹም ሆኑ ችግረኞቹ ከአካባቢ ወደ አካባቢ ይለያሉ። በአንዳንድ ቦታ የተፈናቀሉና ከጦር ሜዳ የተመለሱ ይበዛሉ። አንዳንዴ የእርሻ መሬት ማጣት፣ የንግድ መስመር መጥፋት፣ ድርቅ፣ሥራ አጥነት፣ ወላጅ አልባነት፣አለመማር፣ የንጽህናና የጤና ጉድለት...ወዘተ የሚታዩ ችግሮች ናቸው። አንዳንዴም በባሕል ተጽዕኖ ምክንያት አንዱ ለሌላው ሠርቶና ጥገኛ ሆኖ ራሱን ማኖር እንዳይችል እንደ ነውር ይቈጠራል። በቂ ኢኮኖሚም አያገኝም።እነዚህንና የመሳሰሉ ችግሮችን እንዴት ባለ መንገድ መፍታት ይቻላል? በገጠር ሕዝቡ የሚኖረው የጉልበት ሥራ በመሥራት ስለሆነ፤ አካባቢን ከአካባቢ ጋር፣ ወጣቶችን ከወጣቶች ሴቶችንም ከሴቶች ጋር ማደራጀትና የጋራ ሥራ እንዲሠሩ በማለማመድ በመካከላቸው የሚገኘውን ችግረኛ እንዲያቅፉና በጉልበት ሥራ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ እንዲያደርጉ ማደፋፈርና ማስተባበር ያስፈልጋል። የእርሻ መሬት ያለው ገበሬ ከሆነ መሬቱን በኅብረት ማረስ፣ የዘር እህል ማሰባሰብና ዘርቶ መስጠት፣ ቤት የሌለው ከሆነም በጋራ በማኅበር ወጥቶ አነስተኛ መኖሪያ እንኳ ሠርቶ መስጠት፣ ተማሪ ከሆነ በጋራ አዋጥቶ ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ገዝቶ መስጠት፤ ነጋዴም ከሆነ አነስተኛ መንቀሳቀሻ የሚያገኝባቸውን ዘዴዎች መፍጠር፤ ወላጅ የሌላቸውን ሕፃናት እንደ ወላጅ በጋራ መንከባከብና ማሳደግ፣ ጧሪ ያጡ አረጋውያንን እንደ አባትና እናት በጋራ መንከባከብ፣ ከአቅም በላይ ሲሆን ለቀበሌና ለረጂ ድርጅቶች ማሳወቅ . . . ወዘተ ይቻላል።

በተለይም የገጠሩ ኅብረተሰብ በቂ የሆነ ገንዘብ ባይረውም እንኳ ጉልበቱን ጊዜውንና ጥሬ ንብረቱን መስገስ ስለሚችል ምንም ማድረግ እንደማይችል ማሰብ የለብንም።

ለ. በከተማ:-

የዲቁና አገልግሎት ለመስጠት የከተማውን ይዘት ማየት ያስፈልጋል:: ከተማው ጠባብ ወይም ሰፊ፣ ያደገ ወይም ያላደገ ሊሆን ይችላል:: የከተማ ችግር ከገጠሩ ይለያል:: ለምሳሌ በከተማ ጎልተው የሚታዩ ችግሮች ሥራ አጥነት፤ በቂ ያልሆነ ደመወዝ፣ የመኖሪያ ቤት ማጣት፤ ሌብነት፣ የጎዳና ተዳዳሪነት፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ ዝርፊያ፣ በአልኮል መጠጥና በሐሺሽ በመሳሰሉትም ሕይወታቸውን መጉዳት፣ ራስን በአልባሌ ቦታ መጣል... ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ:: በከተማ ብቸኝነት ስለሚበዛ ሌላውን አንዱ ሌላውን አያውቅም:: የተለያዩ ዘሮችና ብሔረሰቦች በአንድ አካባቢ ሊኖሩ ይችላሉ:: ነገር ግን የከተማ ማኅበራዊ ሁኔታ የምዕራባውያኑን እየመሰለ በመሄድ ላይ ስለሆነ በአጠገባቸው ያለውን ችግረኛ ማወቅና ማስጠጋት አልቻሉም:: እንግድነትም ሊከብድ ይችላል:: እንዲሁም የከተማ ምእመናን ብዙውን ጊዜ የተበታተኑ ናቸው:: በከተማ፣ በሆስፒታል፣ በማረሚያ ቤቶች ጠያቂ ያጡ ይበዛሉ::

ከእነዚህና ከመሳሰሉትም ሁኔታዎች የተነሣ በከተማ የዲቁና አገልግሎት ለመስጠት ከባድ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ሀብትና ንብረት ያላቸውንና ሌሎችንም ቅዱሳን እንደ የሰጡታቸው ማስተባበር ይቻላል:: ማኅበራኑ ምመናን ካላቸው ነገር ለችግረኞች እንዲያዋጡና በካዝና እንዲያስቀምጡ ማድረግ የሚቻለው በዲቁና አስተባባሪ ኮሚቴ በኩል በመጠቀም ነው:: በኮሚቴው አማካይነት የችግሩን ሁኔታ ማጥናት፣ ጊዜያዊውና አንገብጋቢው የቱ እንደሆነ ማወቅ የዘለቄታ እርዳታ ፈላጊዎችን መለየት ያስፈልጋል:: በጥናቱ መሠረት የእርዳታ ዘዴዎችን መፍጠር ይቻላል:: «የዓለምን ጨለማ ከማውገዝ ይልቅ እያንዳንዱ ሰው አንድ ሻማ ማብራት ይቀላል» እንደሚባለው ሁሉ ምእመናን በነፍስ ወከፍ አንዱ ሌላውን ሊረዳ ቢዘጋጅ የብዙዎች ችግር ሊቃለል ይችላል::

## 2.6. ችግረኞችን ወደ ራስ መቻል መምራት

የተቀናጀ ዲቁና አገልግሎት ዋናና ትልቁ ነገር ችግረኞችን በተረጂነት መዝገብ አስፍሮ በየጊዜው በሰዎች ድጋፍ እንዲኖሩ ማድረግ ሳይሆን ካሉበት ሁኔታ ተላቀው ራሳቸውን ወደሚችሉበት ማምጣት ነው::ኑሮአቸውን ለማሻሻል ሠርተው እንዲኖሩ የችግረኞችን ፍላጎትና ችሎታ በማጥናት እንደየምርጫቸውና ተሰጥኦአቸው በሥራ ለማስማራት ልዩ ልዩ ስልቶችን ከእነርሱ ጋር መቀየስ በጣም ይጠቅማል::



የዲቁና አገልጋዮች እንደየሰው ምርጫ ወደ ሥራ የማሰማራትና የማቋቋም ኃላፊነት አለባቸው:: የሚቻል ከሆነም ሰጥቶ ሥራውን ተግተው እንዲሠሩ መከታተል ተገቢ ነው:: ከሰዎቹ ምርጫ ውጪ ማድረግ ለተግባራዊነቱ እንቅፋት መፍጠር ይሆናል:: በአጠቃላይ ያልተቀናጀና የተቀናጀ ዲቁና አገልግሎት እርስ በርስ በመደጋገፍ ችግረኞችን የመርዳት አገልግሎት የተሟላ ያደርጋል::

## 2.7. ድቁና አገልግሎት የማን ኃላፊነት ነው?

ከበዓለ ኀምሳ ቀን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ተመሠረተች:: መሥራቾቹም(ሐዋሪያት) ከጌታ በተማሩ መሠረት ችግረኞችን ሲረዱ ነበር:: የኢየሱስ አገልግሎት ነፍስና ሥጋን የሚመለከት ነበር:: ሐዋርያትም የእርሱን ፈለግ ተከትለው ከቃል አገልግሎት ጎን ምእመናን ያላቸውን ሁሉ በአንድነት አምጥተው ችግረኞችን በመርዳትም ሲተጉ ነበር:: ነገር ግን የምእመናን ቍጥር እየበዛ በሄደ ጊዜ የማዕድ(ዲቁና) እና የቃሉን አገልግሎት ለመከፋፈል ሰባት ዲያቆናትን በማስመረጥ በመሃከላቸው የነበረውን ማጉረምረም አስወገዱ::

### ሀ. የቤተክርስቲያን መሪዎች

የዲቁና አገልግሎት በመሠረቱ የማኅበረ ምእመናን አገልግሎት በመሆኑ እንደ ሐዋርያት ዘመን ዛሬም የዲቁና አገልግሎት ማኅበራዊና አካላዊ አገልግሎት እንዳይዘነጋና ችግረኞች እንዳይረሱ ከሁሉም በላይ መሪዎች ኃላፊነት አለባቸው:: በመጀመሪያ ደረጃ ራሳቸው በፍቅር ችግረኞችን በማሰብ ለምእመናን ምሳሌ መሆን አለባቸው:: ባላቸው ኃላፊነት የዲቁና አገልግሎት አስፈላጊነትን በየደረጃው ማስታማርና ማነቃቃት፤ አደረጃጀቱን መከታተልና አገልጋዮችን ማስመርጥ የመሪዎች ኀላፊነት ነው::

ክትትሉን በየደረጃው ተግባራዊ ለማድረግ ቀላል መንገዶች አሉ:: በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ስብሳባዎች ስለ ዲቁና ማሳሰብና ማስታማር፤ ስለዲቁና ውይይትና እንዲደረግና ሪፖርት እንዲቀርብ በአጀንዳ ቀርጾ ማቅረብ፤ የማኅበረ ምእመናን መሪዎች ከእርስ በርሳቸው እንዲማማሩ መንገድ መክፈት፤ በአገልግሎታቸው ወደ ኋላ የቀሩትን አነሣስተው አገልግሎታቸውን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል:: በየደረጃው ያሉ መሪዎች ተመሳሳይ ክትትል የማድረገና የማነቃቃት ኃላፊነት አለባቸው::

### ለ. የዲያቆናት

የሐዋርያት ሥራ 6:1-6ን በምናነብበት ጊዜ የዲቁና አገልግሎት ለጥቂት አገልጋዮች ብቻ የተሰጠ ሊመስል ይችላል:: ግን አይደለም::

ይህ ክፍል እንደሚያስረዳን ከሆነ በሐዋርያት ተመርጠው የተሾሙ ሰባቱ ዲያቆናት ድሆችን ለመርዳት ሁሉንም መናገር ከራሳቸው ብቻ እንዲያመጡ አልታዘዙም። የእነርሱ ሥራ ሐዋርያት ቃሉን ለማስተማር ሲተጉ ከሁሉም አማኞች የተሰበሰበውን እርዳታ ለድሆችና ለመበለቶች በትክክል ማደልና ሌሎችንም አማኞች ለዚህ አገልግሎት ማስተባበር ነበር። ሰባቱ ዲያቆናት በአገልግሎቱ ውስጥ የራሳቸውን ድርሻ የሚያበረክቱ ቢሆንም ዋና ሥራቸው ግን እርዳታውን አስተባብረው የተገኘውን ነገር በታማኝነትና አድልዎ በሌለበት መንገድ ማከፋፈል ነበር።

*ሐ. የሁሉም ምእመናን*

የዲቁና አገልግሎት የማንኛውም ክርስቲያን ተግባር ነው (ማቴ. 25:31-46፤ ዮሐ.14: 12)። ጌታ ኢየሱስ ለፍርድ ዳግም ሲገለጥ በቀኙ የሚቆሙት የዲቁና አገልግሎት አስተባባሪዎች ብቻ አይደሉም። ሁሉም ክርስቲያን በቀኙ ይቆማል። ስለዚህ የተቸገረውን ሰው ረድተሃል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ሁሉን ይመለከታል።

ይህ አገልግሎት ትርፍ ሥራ ሳይሆን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ትልቁ የክርስቲያን ተግባር ነው። ክርስቶስ የአገልግሎቱን ምሳሌ ለእኛ ትቶልን የሄደው ተከታዮቹ ሁሉ በዚህ አገልግሎት ተሳታፊዎች እንዲሆኑና የሚፈለግባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ነው። እምነትና በጎ ሥራ ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም። በክርስቶስ ያመነ ሁሉ አገልጋይ ሊሆን ተጠርቶአል (1ጴ ጥ.2:9)። ክርስቲያን በምድር ሕይወት ዘመኑ የጌታን በጎነት ለሌሎች ያስተላልፋል። ራሳቸውን ሰጥተው በፍቅር የሚያገለግሉ አገልጋዮችን ሕዝቡ በሚገባ ያውቃቸዋል። የአገልጋይ ትልቁ ዓላማ በሕዝቡ ታወቆ ለመጠራት ሳይሆን ሕዝቡን ለመጥቀም መሆን አለበት። ምንም እንኳን እንደ ኢየሱስ ተአምር ሠሪዎች ባንሆንም በእርሱ ፍቅር ተሞልተን አስፈላጊውንና ከእኛ የሚጠበቅብንን ማድረግ የሁላችን ኃላፊነት መሆኑን ማወቅ ይገባናል። ይህም ማለት በዲቁና የሚገለገሉ ሰዎች በተዋረድ ሰሎችን ለመርዳት ራሳቸውን ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል።

## 2.7.1. ሥልጠና ለማኅበረ ምዕመናን መሪዎችና ቋሚ አገልጋዮች

የዲቁና አገልግሎትን በእያንዳንዱ ማኅበረ ምእመናን ተግባራዊ ለማድረግ ከሁሉ አስቀድሞ ለመሪዎችና ለቋሚ አገልጋዮች ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል። እነዚህ አገልጋዮች የተቀናጀ ዲቁና አገልግሎት



የሚሰጠውን ጠቀሜታ ሲረዱ ለአገልግሎቱ የሥልጠና፣ የትምህርትና የአደረጃጀት መንገዶችን ሊከፍቱ ይችላሉ። በሥልጠናው አማካይነት የዲቁና አገልግሎትን ወደ ምእመናን ያደርሳሉ።

በመሆኑም ከዚህ በፊት በተቀናጀና ባልተቀናጀ መልኩ ከዚህ በፊት ምን ያህል የዲቁና አገልግሎት እንደሰጡ ግንዛቤ ይጨብጣሉ። መስመር የጠበቁ የአደረጃጀት ስልቶችንም ይቀይሳሉ። በዚህ ሥልጠና ወቅት ይህ አገልግሎት ለማኅበረ ምመናን እንደ ጀርባ አጥንት ሆኖ እንደሚረዳ ይገነዘባሉ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት እንዳለውም ያውቃሉ። በማኅበረ ምእመናቸው ውስጥ ያሉትን ችግረኞች ለመርዳት የተቀመጠውን ገንዘብ ያለ ዕቅድ ከመጠቀም ይልቅ በዲቁና አገልግሎት አማካይነት በተቀናጀ መንገድ ሲረዱ ይችላሉ። በመሪዎችና በምእመናን መካከል ስለሚፈጠረው አንድነትና ፍቅርም ጌታን ያመሰግናሉ። ፍቅራቸው ለሕዝብ ስለሚታይ ጌታን የማያውቁ እንኳን ወደ እርሱ ሊመጡ ይችላሉ። በተጨማሪም ለዚህ አገልግሎት ራሳቸውን የሰጡ መሥዋዕትነት ከፍለው የሚያገለግሉ የዲቁና አስተባባሪዎችን ሊያገኙ ይችላሉ። በሥልጠናው ወቅት እነዚህንና ሌሎችንም ጠቃሚ ሐሳቦችን ይጨብጣሉ። መሪዎች ከሠለጠኑ በኋላ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል።

ሀ. ለዚህ አገልግሎት እውነተኛ ሸክም በውስጣቸው ኖሮአቸው ጊዜያቸውንና ራሳቸውን መስጠት የሚችሉ የዲቁና አገልጋዮችን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መመልመል ነው። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በሐዋ.ሥራ 6:1-6 ያለውን ክፍል ማየት መልካም ነው።

1. በመልካም ጠባይና ምግባር የተመሰከረላቸው
2. መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸው
3.ኅብረተሰቡን ያማካለ አመራረጥ
4. እምነት ያላቸው
5. ከተመረጡ በኋላ በምእመናን ፊት በጸሎት መለየት።

*ሐዋርያት ይህን ያደረጉበት ምክንያት በምእመናን መካከል የነበረውን ልዩነት ለማስወገድ፣ ከግሪክ ወገን የሆኑትንም ሆነ ሌሎችን መበለቶች በታማኝነት ለመርዳትና አገልግሎታቸውን ሚዛናዊ በማድረግ የቃሉን፣ የጸሎቱንና የማዕዱን ሥራ በትክክል ለመወጣት ነበር። ይህ አሠራር ጥበብ የተሞላ እንደነበረና በመካከላቸውም ሰላምን*

እንደፈጠረ እናያለን:: የማኅበራኑ ምእመንን መሪዎችም ይህን እንዲያደርጉ ሥልጠና መስጠቱ ጠቃሚ ነው::

ሰ. መሪዎች ራሳቸው ለዚህ አገልግሎት ጊዜ መስጠት አለባቸው

ሐ. ዓላማና ግብ ይዘው መነሣት

መ. መሪዎችና ቋሚ አገልጋዮች ሥልጠና ከተከታተሉ በኋላ ምእመናንን ማሠልጠን

ሠ. ከመሪዎች ውጪ ሌሎች አስተማሪዎችን ጋብዘው እንዲያስተምሩ ማድረግ፣ በመደበኛ አምልኮ ጊዜም በዓመት ውስጥ የተወሰኑ ሳምንታትን ለዲቁና ትምህርት መመደብ፤ ምእመናንን ለዚህ አገልግሎት ማነሣሣትና መጋበዝ

ረ. ራሳቸውን ከሰጡ ፈቃደኞች ምእመናን መካከል ለዲቁና አገልግሎት አገልጋዮችን መልምሎ ማሠልጠን

ሰ. ከሠለጠኑ የዲቁና አገልጋዮች ቡድን ውስጥ አስተ ባባሪ ኮሚቴን ማስመረጥና ሙሉ ኃላፊነት መስጠት

ሸ. ይህ ኮሚቴ ዕቅዱንም ሆነ ሪፖርቱን ለመሪዎች እንዲያቀርብ ማድረግ:: ሪፖቱም በመሪዎ በኩል ለሚመለከተው ሁሉ (ለሰበካ-ለሲዶስ-ዋና መ/ቤት) ማድ ረስ:: እንደ ማኅበረ ምእመናኑ ስፋት ከዲቁና ኮሚቴ ሥር ንዑሳን ኮሚቴዎችን ማስመረጥ

ቀ. ይህን የአገልግሎት ቡድን ከሌሎች የአገልግሎት ቡድኖች እንደ እንዱ ቈጥሮ በምእመናን ፊት ማስመ ረቅና ማስተዋወቅ

በ. ኮሚቴው በበለጠ እንዲንቀሳቀስ እንደ አስፈላጊነቱ በምክር መርዳት፣ እንዲሁም ለማኀደር፤ ለእቅድና ለሪፖርት የሚሆን አስፈላጊው የቢሮ ዕቃ እንዲኖረው ማድረግ

ተ. በማኅበረ ምእመናኑ ዓመታዊ ባጀት ሲሠራ ለዲቁና አገልግሎትም ባጀት መመደብ

ቸ. አገልግሎቱን ወደ ምእመናን ለማድረስ አመቺነት እንዲኖረው እገልግሎቱን እንዲከታተል አንድ ተወካይ ከማኅበረ ምእመናንዋ ቋሚ አገልጋዮች መካከል መመደብ



### 2.7.2. ሥልጠና ለምእመናን

ለምእመናን የዲቁና አገልግሎት ሥልጠና የሚሰጣቸው ከዚህ በፊት ስለ አገልግሎቱ ከሚያውቁት ይልቅ በአዲስ መልክ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ማወቅ እንዲችሉ ነው:: ቀደም ሲል እንዳልነው የዲቁና አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተናገድ፣ ማጽዳት፣ መባ መሰብሰብና በቅዱሳት ምስጢራት ዙሪያ ያለውን ዝግጅት ማከናወን ነው:: ነገር ግን የዲቁና አገልግሎት ከዚህም ያለፈ ነው:: ክርስቶስ የሰዎችን ሁለንተናዊ ነገር በፍቅር እንዳገለገለ እኛም ፈለጉን ተከትለን ማገልገል ነው:: ከዚህ በፊት የዲቁና አገልግሎት ለአንድ ለተወሰነ የዲያቆናት ቡድን የተሰጠ ኃላፊነት አድርገን ዳር ቆመን እናይ ነበር:: አሁን ግን ክርስቲያን ተብሎ የሚጠራው ቀርቶ ሌላውም ኅብረተሰብ የዲቁና አገልግሎት እንደሚመለከተው ማስተማር ይገባል ::

በመሆኑም በዚህ ሥልጠና ወቅት ምእመናንን ሁሉ የሚያቅፍ የዲቁና ትምህርት ሊሰጥ ይገባል:: ይህ አገልግሎት ሁሉንም የሚያሳትፍ መሆኑን ለምእመናን ካሳወቁ በኋላ ራሳቸውን ለአገልግሎት እንዲያዘጋጁ መወያየት፣ ጸጋቸውን ማነሣሣትና መለየት ያስፈልጋል:: በመቀጠልም ለዚህ እገልግሎት ራሳቸውን እንዲሰዩ ፈቃደኝነታቸውን ማወቅና ራሳቸውን የሰጡትን በተለይ መዝግቦ መያዝ ያስፈልጋል:: በተደራጀና ባልተደራጀም መልኩ በየአካባቢያቸው ሌሎችን እንዲያሳትፉና አገልግሎቱን እንዲደግፉ ማድ ረግ ይገባል:: ይህ ሥልጠና በይበልጥ የሚረዳው ከምእመናን መካከል አገልጋዮችን ለማግኘትና ሁሉንም ምዕመናን በአገልግሎቱ ለማሳተፍ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::

የእግዚእብሔር ሥራ በጣት በሚቈጠሩ ጥቂት ሰዎች የሚሠራ አይደለም:: ሁሉም ሰው በገንዘቡ፣ በእውቀቱ፣ በጉልበቱ፣ በጸሎቱ፣ በሙያው፣ በጊዜው፣ በንብረቱ ማገልገል ይኖርበታል:: ምንጊዜም ቢሆን ምእመናንን የሚያቅፍ እገልግሎት ውጤታማ ነው:: ችግ ረኞችን፣ መበለቶችንና ድሆችን በቅርቡ ማግኘት የሚችሉት ምእመናን ናቸው:: እንደዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ሲያገኙ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዱ በማለት ወደ አንዲት ካዝና ከማሳየት ይልቅ በጋራ በመወያየት መፍትሔ ማግኘት ይቻላል:: የከበዳቸውን ወደ ዲያቆናት አገልግሎት ኮሚቴ ይመራሉ:: በዚህ ጊዜ ተስፋ ቈርጠው ላሉት ከገንዘብ ይልቅ ፍቅራቸውን በተግባር ያሳያሉ:: ዕለታዊ ችግራቸውንም በጋራ ያቃልላሉ::

ይችላል ::በውይይት የራሳቸውን ሙከራና የመፍትሔ እሳብ፤ የወደፊት እቅዳቸውና እቅማቸው፣ የስው ጉልበት፣ መሬት፣ ወዘተ ምን እንደሆነ፤ ዘመድ ወይም ሊረዳ የሚችል ጎረቤት እንዳለ፣ ግንኙነታቸውስ ምን እንደሚመስል እንረዳለን:: በመልካም ነገራቸውና ሙከራቸው ሁሉ ማመስገንና ማበረታታት ያስፈልጋል

5. ዕቅድ

በዲቁና እገልግሎት ውስጥ ከጥናት በተገኘ ውጤት መሠረት ከችግረኛው ጋር አንድ ላይ በመሆን ዕቅድ ማውጣት ለተግባራዊነቱ ይጠቅማል:: ዕቅድ የምናዘጋጀው ካለው ነገር ተነሥተን እንጂ በሌለው ነገር ላይ ተመሥርተን መሆን የለበትም:: በዕቅዱም ውስጥ መካተት ያለባቸው ነገሮች ይኖራሉ:: የጠለቀ ጥናት ከተደረገ በኋላ በማኅበረ ምእመናኑ የዲቁና ኮሚቴዎችና እባላት በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የአገልግሎቱ ዓላማና ግብ በአጭሩ በግልጽ ከተጠቀሰ በኋላ የሚጠበቀውን የእገልግሎት ውጤት በትክክል መለካት በሚቻልበት መለኪያ መግለጽ ያስፈልጋል:: እነዚህ የዕቅድ መመሪያዎች ሲሟሉ ብቻ ነው በማኅበረ ምእመናኑ ውሳኔ መሠረት ዕቅዱ ሥራ ላይ የሚውለው:: በከንውኑ ሂደት መጨረሻ ላይ ደግሞ ውጤቱን በመለካት የተሠራውን ሥራ መገምገም ይቻላል:: የከንዋኔ ግምገማ የሚያስፈልገው ለቀጣዩ ሥራ መሻሻልና አዲስ ራዕይ የሚያፈልቅ በመሆኑ በጥንቃቄ መደረግ ያለበት መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው::

ዕቅድ ለዕለት ተዕለት ኑሮአችንና ሕይወታችን የሚያስፈልግ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ተሰጥቶት በሚገባ ልንጠቀምበት የሚገባ መሣሪያ ነው:: ያለ ዕቅድ የሚመራ ሰው ወይም ድርጅት በውኃ ላይ ያለ መሪ የሚንሳፈፍ ጀልባ ነው:: ይህ ደግሞ ያለ እቅጣጫና ግብ የሚሠራ ሥራ ስለሚያስኝ ስእንጻሩ በግለሰብም ሆነ በቡድን ወይም በቤተ ክርስቲያን የዲቁና እገልግሎት ሲደራጅ በተቀነባበረና በተቀናጀ ሁኔታ በዕቅድ መገንባት ያለበት የእገልግሎት ዘርፍ ነው::

6. ማስተባበር

የዲቁና አገልግሎት የጥቂት ግለሰቦች ሥራ ብቻ ስላይደለ ሌሎች እንዲሳተፉበት ሁኔታውን በግልጥ በማስረዳት ማስተባበር ያስፈልጋል:: ይህም ለምእመን የበረከት መንገድ ይሆናል:: «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» የሚለውን የተለፋ ቃል በሕይወታቸው ተግባራዊ ይሆናል (ሐዋ.ሥ 20:35):: ማስተባበርን በሚመለከት ምሳሌ የሚሆኑ ብዙ ክፍሎች መጥቀስ ይቻላል::



ሆኖ ለትምህርታችን እንዲጠቅመን በአዲስ እበባ ካሉት ማኅበራነ ምእመናን መካከል በአንዷ ውስጥ በዚህ እገልግሎት የተሳተፉ እናቶችን ብቻ እንጠቅሳለን::

የዲያቆናት እስተባባሪ ኮሚቴዎች አንድ ወር ሙሉ ያለማንም የሰው እርዳታ በታይፎድ ሕመም ተኝቶ የነበረን ሰው የሚረዱ እናቶችን እስተባብረው ተራ በተራ ምሳ፣ እራትና ቁርስ እየወሰዱለት ቤቱን እያጸዱና ልብሱንም እያጠቡ ያስታምሙት ነበር:: ይህ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ድኖ እንደሄደና ከእናቶች እገልግሎት የተነሣ ራሱን ለዲቁና አልግሎት ሊሰጥ መቻሉን ከምስክርነቱ ተሰምቶአል:: እንዲያውም እስካሁን ክርስትና ምን እንደሆነ አይገባኝም ነበር:: አሁን ግን ሌሎችን መርዳት እንዳለብኝ እንዳውቅ ይህ የፍቅር እገልግሎት ዓይኔን ከፍቷል ብሎአል::

7. ክትትል

እንዴ ተረድቶአል ብሎ ችግረኛውን መርሳት እያስፈልግም:: አገልግሎቱ በሕይወቱ፣ በኑሮው፣ በዕለታዊ ነገሩና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያስከተለው ለውጥ መኖር አለመኖሩን መከታተል፣ ከፊት ይልቅ እዳዲስ ዘዴዎችን መጠቀም ችሎአልን? የተሰጠውን እርዳታ በምን ላይ አዋለ? እነዚህንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች መከታተል የዲቁና አገልግሎት ቡድን ኮሚቴ ሥራ ነው:: ብዙ ጊዜ ክትትል ከሌለ ሰዎች የተሰጣቸውን ጨርሰው ለማኞች ይሆናሉና::

8. ሪፖርት

ሪፖርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን የተሠራውን ነገር ሁሉ እንደ መታሰቢያ ያኖሩ ነበር:: የመታሰቢያ ድንጋይ ያኖሩና ለትውልድ ያስተላልፉ ነበር (ኢያሱ.4:6-7፣ዕዝ.8:21-22):: ኢያሱም ጾም አወጅኩ እግዚአብሔርን ለመንን እርሱም ተለመነን ይላል:: ሐዋርያትም የሠሩትን ሥራ ሪፖርት ለኢየሱስ እቅርበዋል(ሉቃ.10:17-19):: ሰብዓውም ተመልሰው የሆነውንና የሠሩትን ሁሉ ለጌታ ሪፖርት አደረጉ:: ጌታም ተቀበላቸው:: ስለዚህ የተከናወኑትን ተገባራት ሪፖሪት ማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው::

9. ግምገማ

ግምገማ በሁለት መልኩ ይታያል:: የመጀመሪያው ራሳችንን በራሳችን መምገም ሲሆን ሁለተኛው ሌሎች እኛን እንዲገመግሙን

ፈቃደኛ በመሆን፣ ደካማና ጠንካራ ጎናችንን የምናይበት ይሆናል (ማቴ 16:13-16):: ኢየሱስ ራሱን አስገመገመ:: የእግዚአብሔር ልጅ ራሱን ለግምገማ ካዘጋጀ እኛ አማኞችስ? ግምገማ የሥራችንን ምንነት እንድንገነዘብ ያደርጋል:: ካቀድነው እቅድ ምን ያህሉ ተሠራ?፣ ምን ያህሉስ ተፈጻሚ አልሆነም? ብለን እንድናየውና በቀጣዩ ጊዜ ለተ ግባራዊነቱ እንድንዘጋጅ ይረዳናል:: በዚህ ጊዜ ጠቅላላውን እንቅስቃሴ ማየት ይቻላል:: ግምገማ ዓመታዊ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ሥራችን የምናይበት ነው:: በግምገማ ወቀት ኮሚቴውና የአገልግሎት ቡድኑ ሊያጤናቸው የሚገቡ ነጥቦች:-

- ሥራውን የገቱ ችግሮች ካሉ ከነመፍትሔአቸው ማየት፣
- በትክክል ከተሠራ ለልቱን ማጠናከርና ማስፋፋት፣
- ሥልጠናና ትምህርት በተሰጠ ጊዜ ሰዎች (ምእመናን) መረዳት አለመረዳታቸውን፣
- ተገቢ ሰዎች መሠልጠን አለመሠልጠናቸውን፣
- ተገቢ ሥልጠና መሰጠት አለመሰጠቱን
- ዕቅዱ በዓመቱ ውስጥ ተፈጻሚ መሆን አለመሆኑን፣
- እርዳታ የተደረገላቸው ሰዎች ያላቸውን ለውጥ ማየት. . . ወዘተ ናቸው::

**10. ማመስገን**

እኛ ኢትዮጵያውያን ምስጋናን ማቅረብ ገና አልተለማመድንም እንጂ በዲቁና አገልግሎት በየትኛውም አንጻር የተሳተፉ ሰዎችን ላበ ረከቱት አስተዋጽኦ በግልም ሆነ በጉባኤ ማመስገን መልካም ነው:: በተለይ ሪፖርት በምናቀርብበት ጊዜ ሙሉ አባላት ባሉበት ማመስገን በአገልግሎቱ የተሳተፉትን ያበረታታል:: ገና ያልጀመሩትንም ተሳታፊ ዎች እንዲሆኑ ያነሣሣል::



## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የዲቁና አገልግሎት:-
   ሀ. ለምን?
   ለ. ማንን?
   ሐ. እንዴት? እንደሚያገለግል ዘርዝር::
2. የዲቁና አገልግሎት የማን ኃላፊነት ነው? የተገልጋዮቹ ኃላፊነትስ?
3. የተቀናጀና ያልተቀናጀ የዲቁና አገልግሎት ልዩነትና ተመሳሳይነት ግለጽ:: በማኅበረ ምዕመናንህ ወይም በአከባቢህ የተሻለ ዘዴ የቱ እንዴሆን አብራራ::
4. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ችግረኞች ተብለው የተጠቀሱ እነማናቸው? እነዚህ የዲቁና አገልግሎት ተገልጋዮች ወደ ራስ መቻል ለማድረስ ምን ምን ቢደረግ ይመረጣል?
5. እያንዳንዱ ምዕመን ዲያቆን ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ለምን? ይህንን ግንዛቤ ለማሳደግ ምን ማድረግ አለብን? እንዴት?
6. የዲቁና አገልግሎት በከተማና በገጠር እንዴት ባለው መልኩ ቢሰጥ ይበጃል ብለህ ታስባለህ? ባንተ ማኅበረ ምዕመናን ወይም አከባቢስ?
7. በዚህ ምዕራፍ ያገኘኸውን ዋና ዋና ፍሬ ጉዳዮችን በዝርዝር ጻፍና በማኅበረ ምዕመናንህና ኅብረተሰብህ ውስጥ እንዴት መተ ግበር እንዴሚቻል ግለጽ::

ይመስላል ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር ሠራተኛ እንደሆነ ሰውም ሠራተኛ ነው ማለት ነው::

### መ. <u>ሥራ ሰው ራሱን እንዲችል ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ነው:-</u>

ብዙውን ጊዜ በሥራ ራሳቸውን የማይደግፉ ሰዎች ልመናን፣ ሌብነትን፣ የሰውን መመኘትና በሌላ ሰው መደገፍን ይፈልጋሉ:: ይህ ሁሉ የሥራ ፈትነት ውጤት ነው:: እግዚአብሔር ከውድቀት በኋላ አዳምን ያዘዘው ሠርቶ እንዲኖር ነው (ዘፍ.3፣17-19):: ስለዚህ አላይ በተዘረዘሩትና በሌሎችም ምክንያቶች ሥራ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የታሰበ ነገር ነው::

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ሥራ በተብራራ መልኩ ለመገንዘብ ከተፈለገ በሙሴ በኩል የተሰጠውን ትእዛዛት ማየቱ ይጠቅማል:: አንድ ሰው ታዘዘ ማለት ሥራ እንዲሠራ ተነገረው ማለት ነው (ዘጸ 20:10-17):: በዚህ ክፍል 1ኛ/ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዝና እንዲሠራ 2ኛ/ ለወላጆቹ እንዲታዘዝና እንዲሠራ 3ኛ/ ከሌሎች ሰዎች ጋር ጤናማና ሰላማዊ ኑሮ እየኖረ አብሮ እንዲሠራ ታዞአል::

የነቢያት መጽሕፍት:-

በአብዛኛው የሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ስለመመለስ ይናገራሉ:: ጥቂት ክፍሎች ግን እግዚአብሔር ሠራተኛ እንደሆነ ይነግሩናል:: ከዚህ የምንረዳው ሰው የእግዚአብሔርን ፈለግ ተከትሎ መሥራት እንዳለበት ነው (ኢሳ. 29:16፣ 45፣9: 64፣8፣ ኤር. 18:4)::

የጥበብ መጻሕፍት:-

ለግሪኮች አእምሮው ሲሠራና ፈላስፋ ሲሆን ጠቢብ ሰው ነው ይባላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጥበብ መጻሕፍት የእስራኤልን የሥራ አመለካከት ያንፀባርቃሉ:: ለእነርሱ ጥበብ የአእምሮ ነገር ብቻ ሳይሆን የእጅ ሙያም ጭምር ነው(ኢሳ.40፣20፣2ዜና.2:12):: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሥራ ጠላቶች የሆኑት «ስንፍና» ወይም ሰነፍ የሚሉ ቃላት 37 ጊዜ ተጠቅሰዋል:: ከ37ቱ አራቱ ብቻ ከጥበብ መጻሕፍት ውጪ ሲገኙ የቀሩት በጥበብ መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ:: በተለይ በመጽሐፈ ምሳሌ «ሰነፍ እና ጠቢብ» የሚሉ ቃላት በተቃራኒ መልክ ይገኛሉ:: ይህም የሚያሳየው ሥራ ፈትነትን እንደሚያወግዝ ነው::



በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች በየመንገድ ዳርና በልዩ ልዩ ቦታ የሚለምኑ ሰዎች ሁሉም ችግረኞች ናቸው ለማለት ያስቸግራል:: አንዳንዶቹ ሥራ ላለመሥራት ፈልገው በስንፍና ልመናን የሕይወታቸው ክፍል ያደረጉ ናቸው:: ለምሳሌ እጅ እግራቸው ጤናማ ሆኖ እያለ የተለያየ ዘዴዎችን በመጠቀም ከሚለምኑ ሰዎች መካከል አንዱን የቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ አግኝቶት እንደዚህ ከምትለምን የቀን ሥራ እየሠራህ የምትውልበትን ሥፍራ ልውሰድህ ብሎ ጠየቀው «አሁን እኔ የቀን ሥራ ብሠራ የማገኘው አምስት ብር ብቻ ነው ነገር ግን በልመና በቀን እስከ ሃያ ብር አገኛለሁ» በማለት መልሶለታል:: ነገር ግን የትኛውም ለማኝ ኑሮውን በልመና ገንዘብ ሲያሻሽል ተይቶ አይታወቅም::

ይህ ማለት ሁሉም ለማኝ ችግር የሌለበት አታላይ ነው ማለት ሳይሆን የሚለምኑትን ጠጋ ብለን ከማነጋገርና መፍትሔ ለመፈለግ ከማሰብ መቆጠብ የለብንም::

### 3.1.2. ሥራ በአዲስ ኪዳን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ቆይታው ዘመን አገልግሎቱን ሳይጀምር በፊት የጉልበት ሠራተኛ ሆኖ ዮሴፍንና እናቱን ማርያምን እየታዘዛቸው በመሥራት ያገለግላቸው ነበር (ማር. 6:3)::

የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሠራተኞችም የሥራ አስተ ማሪዎችም ነበሩ:: ማንኛውም ሰው በምድር ላይ ሲኖር ለሕይወቱ መሠረታዊ ነገሮች /ምግብ፣ ልብስና መጠለያ/ ያስፈልጉታል:: እነርሱም ከሰማይ እንደ መና የሚወርዱ ነገሮች ሳይሆኑ በምድር ላይ የሥራ ውጤቶች ናቸው:: ስለዚህ የጌታ አገልጋዮች የሆኑት በመሉ ሠርተው የሚበሉ ነበሩ:: ሰው ሲሠራ እግዚአብሔር የደካሙን ውጤ ት በመባረክ ተስማሚ አየርና ዝናብ በመስጠት ፍሬያማ ያደርገዋል:: እግዚአብሔር ከሚሠራ ሰው ጋር እንደሚሆን በዚህ እናውቃለን::

ስለ ሥራ ሰፋ ባለ መልኩ ስናስብ፣ እግዚአብሔር የሸክላ ሠሪን ምሳሌ እንደያዘ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አናጺ እንደሆነ፣ ጳውሎስ ደግሞ ድንኳን ሰፊ እንደነበረ ከቃሉ እናያለን (ኤር.18:5-6፣ኢሳ.29:16፤ኢሳ.45:9-10፣ማቴ.13:55፣2ተሰ.3:7-8):: ሰው በማህበራዊና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ክርስቶስን እንዲመስል ተጠ ረቶአል:: ደቀ መዛሙርት በትምህርታቸው ትክክለኛውን የቤተሰብ አኗኗር በሚገባ ገልጸዋል(ቈላ.3:18-4:1):: ለሥራ መትጋት ለክርስቲያን ከሚገቡ ታላላቅ ምክሮች አንዱ መሆኑን ያወቀው ሐዋርያው ጳውሎስ (በሮሜ.12:11) «ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ»

በማለት ያስተምራል። ጳውሎስ ወንጌልን በሰበከባቸው ሥፍራዎች ሁሉ የቃላት ተስፋ ብቻ አልተናገረም። ነገር ግን ድንኳን እየሰፋ ከሚያገኘው ገቢ ችግረኞችን ይረዳ ነበር(1ቆሮ.9:12፣1ተሰ.2:9)። ሐዋርያው ጳውሎስ «እኛን ልትመስሉ ራሳችንን አንደ ምሳሌ እንስጣችሁ ዘንድ ነበር»በማለት የተሰሎንቄን ምእመናን ያደፋፍራቸው ነበር። በተጨማሪም «እኛ መንፈሳዊያን ነን» እያለ ሥራ ሳይሠሩ የሚዞሩትን ሰዎች በጸጥታ እየሠሩ የራሳቸውን እንጀራ ይበሉ ዘንድ በኢየሱስ ስም አዞአቿዋል፣ ደግሞም መክሮአቸዋል(2ተሰ.3:10-12)።

### 3.2. የሥራ ፈትነት ምክንያቶች

የሚከተሉት ነገሮች ለዘመናችን ሥራ ፈትነት ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ መገመት ይቻላል።

#### ሀ. ሥራን መሥራት ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር የሚጋጭ አድርጎ መገመትና ማመን፤

ለአንዲህ ዓይነት ሰዎች ክርስትና በቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ጣሪያ ውስጥ ብቻ ይመስላቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የምንማረው ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሆን፣ የምንኖረው ግን በኅብረተሰብ ውስጥ ነው። የማይተገበር የክርስትና ትምህርት ትርጉም የለሽ ነው። አንድ ሰው ሥራን ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር የሚጋጭ አድርጎ የሚያስብና የሚያምን ከሆነ «ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው አርዱ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ»(ሮሜ 12:13) የሚለውን አባባል እንዴት ሊተረጉምና ሊኖር ይችላል? ቅዱሳንን ለመርዳትና እንግዶችን ለመቀበል እኛ ከራሳችን የምንሰጠው ነገር መኖር አለበት። ያን ደግሞ የምናገኘው ሥራ ሠርተን ነው። በዚህ መልኩ ሥራ መሥራት ለዲቁና አገልግሎት እገዛ ያደርጋል። ስለዚህ ሥራ የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው።

#### ለ. በሌሎች ሥራ መደገፍ፤

መደጋገፍ የክርስትና አገልግሎት መንገድ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን። በመደጋገፍ ውስጥ አንዱ ሌላውን ይረዳል። አባቶች ልጆቻቸውን ለተወሰኑ ጊዜያት ይደግፋሉ። ያን የሚያደርጉት ልጆቻቸው የዕድሜ ልክ ጥገኞች እንዲሆኑ አይደለም። ራሳቸውን እስከሚችሉ ድረስ ነው። በክርስትና ሌሎችን የመደገፍ አገልግሎት የሚሰጠው ስንፍናን ለማስፋፋት ሳይሆን



መሥራት እየፈለጉ መሥራት የማይችሉትን ችግረኞች ራሳቸውን ወደሚችሉበት ለማድረስ ነው።

#### ሐ. ጸሎትንና ሥራን ሚዛናዊ አለማድረግ፤

ለእግዚአብሔር ክብር ካደረግናቸው ሥራም ሆነ ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት እኩል አስፈላጊዎች ናቸው። ድነት የሚገኘው ግን በእምነት ብቻ ነው። በሥራም በጸሎትም ጽድቅ የለም። የዳነ ሰው ሥራ ይሠራል፣ ይጸልያልም። ከዳንን በኋላ ሥራችንን ለእግዚአብሔር ክብር ከሠራን ከጸሎት በማያንስ መልኩ እግዚአብሔርን እናከብራለን፣ እርሱም ሥራችንን ይባርክልናል።

#### መ. የፈጠራ እጦት፤

አንድ ሰው ሁልጊዜ አንድ ሥራ ቢሠራ እያደር ሊሰለች ይችላል። ነገር ግን አዳዲስ ሥራ መፍጠር ለሥራ ያለንን ፍቅር በእጅጉ እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል። በአገራችን ብዙ ጊዜ ሥራ እጥ የሚል አባባል እንሰማለን። እንደ እውነቱ ከሆነ ሥራ ሠሪን እጥቷል እንጂ ለሰው ሥራ አልጠፋም። ብዙዎቻችን እንደሙያችን ልንሠራ አልቻልንም። ትምህርታችንንም ሥራን ለመፍጠር አልተጠቀምንበትም። በኢትዮጵያ ሰው ሥራ እንዳይፈጥር አንዳንድ እንቅፋቶች ይታያሉ። ከእነዚህም መካከል አንዳንድ ሥራዎችን መናቅ፣ ለምሳሌ በአብዛኛው ኅብረተሰብ መካከል የሸክላ ሥራ፣ ቆዳ የመፋቅ ሥራ፣ ጫማ መጥረግ ፣ ሥራ አይደለም። ከዚህ የተነሣ እነዚህን ነገሮች የሚሠሩ ሰዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ የተናቁና የተገለሉ ናቸው። ሸክላ ሠሪ ትልቅ ሥፍራ ሊሰጠው የሚገባ ሙያ ያለው ሰው ነው። የሸክላ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ለአገራችን ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ናቸውና ሊበረታቱ ይገባቸዋል። ሰው በዘመኑ ሆኖ ሥራ ለመሥራት የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይፈልጋል። አሮጊቶችና ሽማግሌዎች መሥራት የሚገባቸውንና አቅማቸው የሚፈቀደላቸው ሥራ መፍጠር የሥነ ልቦና እርካታ ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም የራሳቸውን ሥራ ሠርተው ያለ ማቋረጥ እንጀራቸውን እንዲበሉ ያደረጋቸዋል።

#### ሠ. በልመናና በዲቁና ያለው የተሳሳተ መረዳት፤

አንዳንዴ ሰዎች መለመንን የሕይወት ክፍላቸው አድርገው ይቀበሉታል። ይህ አመለካከት በባህልም ሆነ በሃይማኖት ደረጃ ራስን ከሰው የበታች እንደማድረግ ስለሚቈጠር መወገድ አለበት።

ረ. ሚዛናዊ ያልሆነ ማኅበራዊ ኑሮ፤

ጊዜ ውድ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው:: እያንዳንዱ ሰው በምድር ላይ እኩል ቀን (24 ሰዓት) ተሰጥቶታል:: ሰው በዚህ ጊዜ መሥራት ይገባዋል:: ምክንያቱም ጊዜ አንዴ ካለፈ ተመልሶ አይመጣም:: እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ብዙ ጊዜያችንን የምናሳልፈው በማኅበራዊ ኑሮ ነው:: በለቅሶ፣ በሠርግ፣ በሌሎችም ማኅበራዊ ጉዳዮች በምናሳልፋቸው ጊዜያት ሥራ እንፈታለን:: ይህ በመሠረቱ ክፉ ነው ማለት ሳይሆን ሚዛናዊ ቢሆን ይሻላል ለማለት ነው::

## 3.3. ሥራ ፈትነት የሚወገድባቸው መንገዶች

### ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

መጽሐፍ ቅዱስ ሥራ ፈትነትን ያወግዛል:: መሥራት የሚችል ማንም ሰው የራሱን ኑሮ በራሱ ጉልበትና ጥረት ሠርቶ መምራት አለበት:: ይህ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለሆነ ሰው ሁሉ መማር ይገባዋል::

### ለ. በተግባራዊ ክርስትና

እኛ ለሌሎች ምሳሌዎች መሆን ይገባናል:: ጳውሎስ ድንኳን ይሰፋ የነበረው ሌሎች የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተሉ ነው (2ተሰ 3:7-13):: ክርስትናችን በዕለታዊ ኑሮአችን ቢያንጸባርቅ ሰዎችን ከብዙ ስሕተት ይመልሳቸዋል::

### ሐ. ተግተው ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን በማበረታታት

ሥራን መናቅ ለስንፍና ትልቅ ምክንያት እንደመሆኑ ተግተው የሚሠሩ ሰዎች ሲበረታቱ ይገባቸዋል:: በሥራ የሚተጉትን ሰዎች ማክበር፣ ሙያቸውን ማድነቅና መቀበል ሰውን ለሥራ ያነሣሣልና::

### መ ድህነትን መንፈሳዊ አለማድረግ

መንፈሳዊ ሰዎች ድሆች ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን ድሀ መሆን ሰውን መንፈሳዊ አያደርገውም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለድሀ ያደረገው ልዩ ጥንቃቄ አለ:: በተለይ የሉቃስ ወንጌል ለድሀ የቆመ ወንጌል እንደሆነ ተጠንቶአል:: በሉቃ 4:16፣17:6-20 ኢየሱስ ወደ ድሆች ሲመጣ ድሆች ስለ ሆናችሁ ደስ ይበላችሁ አላለም:: ነገር ግን ከድህነት የሚያወጣ ወንጌል ተገልጧል በማለት ሰብኮአል:: በሥራ ፈትነታቸው ምክንያት ድሆችን «የእባቱ ቡሩካን ናችሁ» አይላቸውም ሊሠራ የማይወድ አይብላ ይላቸዋል እንጂ:: ስለዚህ ሥራ ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ ስጦታ እንደመሆኑ በምድር ላይ



ሲኖር ያስመሰለችት እየሠራ አደራውን መወጣት ያስፈልገዋል::

## 3.2. ዲቁናና የፈውስ አገልግሎት



ስለፈውስ ከመናገራችን በፊት ስለ ጤንነትና ስለ በሽታ ማሰብ ተገቢ ነው:: ጤንነት ምን ማለት ነው? ሙሉ በሙሉ ጤናማ የሆነ ሰው በዚህ ምድር ይገኝ ይሆን? ጤንነት ማለት ከአካል ወይም ከአእምሮ በሽታ ነፃ መሆን ብቻ አይደለም:: ጤንነት ማለት ሰው ከእግዚአብሔር፣ ከባልንጀራዎቹና ከራሱ ጋር በስምምነትና በሰላም ሲኖር ነው:: ሰላማችንን የሚያናጉ ብዙ ነገሮች አሉ:: ለምሳሌ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ልዩ ልዩ አደጋ፣ ተላላፊ በሽታዎችና ደዌ፣ ማኅበራዊና የትዳር ችግር፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ዓለም የሚያጋጥም አጋንንት አሠራር ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው:: እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ከበሽታቸው ተፈውሰው ጤናማዎችና ደስተኞች እንዲሆኑ ይፈልጋል:: ስለዚህም በበሽታና በኀዘን እንዲኖሩ የሚያደርጉ ነገሮችን በሙሉ ለማስወገድ አንድያ ልጁን ኢየሱስን ልኮአል::

በምድር ሳለን ግን መከራ አለብን:: ከባድ በሽታና አደጋ፣ አካል ጉዳተኝነት ወይም ሌላ መከራ ሲያጋጥሙን የሚያስጨንቁ ጥያቄዎች ወደ አእምሮአችን ሊመጡ ይችላሉ::

ይህ ችግር የደረሰብኝ ከእግዘአብሔር ቍጣ የተነሣ ነውን? እግዚአብሔር የሚወደኝ ከሆነ ይህ ነገር ለምን ሆነብኝ? የአእምሮ ሰላምን እንዴት አገኛለሁ? የሚሉና የመሳሰሉትም ይሆናሉ::

በታመሙት ላይ የፍርድ ቃል እንዳንናገር «እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለደረሰባቸው ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስሉአችኋልን?» በማለት ጲላጦስ ደማቸውን

ከመሥዋዕታቸው ጋር ስላደባለቀው የገሊላ ሰዎች ጌታ የተናገረውን ቃል እናገኛለን (ሉቃ. 13:1-5)። እንዲያውም ሁላቸውም ንስሐ ካልገቡ ከጥፋት እንደማያመልጡ አስጠነቀቃቸው። እዚህ ላይ ማንም ከማንም የተሻለ ጻድቅ አይደለም ማለቱን እንመለከታለን።

መጽሐፍ ቅዱስ በሽታንና መከራን በተለያየ መልኩ ያየዋል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ መከራ ሰውን ከክርስቶስ የመስቀል ሥቃይ ጋር እንደሚያገናኝ ይናገራል(ፊልጵ.3:10-11)። ያዕቆብ ደግሞ በፈተና መጽናት በረከት ነው ይላል(ያዕ.1:2-3፣2ቆሮ.12:7-9፣ዮሐ.9:1-3፣ሮሜ.5፣3-5)። እነዚህን ጥቅሶች ስናነብ ካወቅንበት መከራ ወደ ክርስቶስ የሚያስጠጋንና ለችግራችን መፍትሔን ከአምላካችን ብቻ ማግኘት እንደምንችል ይነግሩናል። ስለዚህ መከራ አንዳንድ ጊዜ ምሥጢራዊ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። በጨለማ የሕይወት ብርሃን እናገኛለን። ጊዜያዊ ችግር ዘለቄታ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ያስጠጋናል እንድንታመን ያደርጋል።

መልካም ለዎች እንኳ መከራ ያጋጥማቸዋል። በዚህ ዓይነት እይታ ውስጥ እግዚአብሔር ተፈጥሮን በሙሉ በእኩል ዓይን ያያል። በሌላው ላይ የሚደርስ መከራ በማንም ሰው ማለትም በኃጢአተኛም በጻድቅም ላይ ሊደርስ ይችላል የሚል ነው (ማቴ. 5:45)። የጌታ ደቀ መዛሙርት እውር ሆኖ ስለተወለደው ሰው በማን ኃጢአት ምክንያት እውር እንደሆነ ኢየሱስን በጠየቁት ጊዜ «የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም» ብሎ መለሰላቸው (ዮሐ.9:2-3) እግዚአብሔር ፍቅሩን የሚገልጽባቸው ወገኖች መከራ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ለምሳሌ ኢዮብን ስንመለከት ትዕግሥስት ያስተምረናል። ሐዋርያው ጳውሎስም የሥጋ መውጊያ ተሰጠኝ ይላል (2ቆሮ.12:8-10)።

መከራ፣ በሽታና አካል ጉዳተኝነት ከእግዚአብሔር ተግሣጽ ወይም ቊጣ የተነሣ ሊደርስ እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ለምሳሌ ማርያም በሙሴ ባጉረመረመች ጊዜ (ዘኁ.12:1-15) ንጉሡ ዖዚያን ወደ መቅደሰ ገብቶ መሠዊያ ላይ ባጠነ ጊዜ (2 ዜና. 26:16-21)፣ የእግዚአብሔር ሰው የኤልሳዕ ሎሌ ግያዝ ያልተፈቀደለትን ስጦታ ከወሰደ በኋላ መውሰዱን ክዶ የንዕማን ለምጽ በርሱና በዘሮቹ ላይ በደረሰ ጊዜ (2ነገ. 5:20 - 27)፤ ሐናንያና ሰጲራ መንፈስ ቅዱስን በዋሹ ጊዜ (ሐዋ. 5:1 - 11) የእግዚአብሔር ፍርድ ተገልጾባቸዋል።

በሰዎች ላይ ስለሚደርስ ችግር ጠቢቡ ሰሎሞን «ልጄ፣ ሆይ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ በገሠጸህም ጊዜ አትመረር



እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጸልና አባት የሚወደውን ልጅ እንደሚገስጽ» (ምሳ.3:11-12) በማለት መከራን እንደ እግዚአብሔር ተግሣጽ እንድንቀበለው ይነግረናል። በዕብ.12:5-11 ተመሳሳይ ሐሳብ እናገኛለን።

መከራ በሰው የሕይወት ዘመን የሚደርስ ነገር ሲሆን እግዚአብሔር ደግሞ ከደካሞችና ከበሽተኞች ጎን ይቆማል። እርሱ ብቻ እውነተኛ የሆነ የነፍስና የሥጋ ፈዋሽ ነው። በኢሳይያስ 53:4-9 ያለውን የትንቢት ቃል ስንመለከት እግዚአብሔር ደዌያችንን የሚቀበልና ሕመማችንን የሚሸከምልን ስለ ጭንቃችንም ተጨንቆና ቈስሎ በቊስሉቹ የሚፈውሰንን መሲሕ እንደሚልክልን ይናገራል።

ኢየሱስ በትንቢት መጻሐፍት እንደተፃፈለት የሕዝብን ሁሉ ደዌ ሊፈውስ ወደ ዓለም መጥቷል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ታላላቅ የሆኑ የፈውስ ሥራዎችን እየሠራ ነው። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው»(ዕብ 13:8) የሚለው ቃል ስንመስከት የእግዚአብሔርን እውነተኛ ባሕርይ እናያለን። እግዚአብሔር አይለወጥም። ትላንትና የሰራውን ዛሬም ይሠራል። ዛሬ መሥራት የቻለ ነገም ሆነ እስከ ዘላለም ይሠራል። እግዚአብሔር ከጥንት እስከ ዘላለም ማንነቱ የማይለወጥ ብርቱና ታላቅ አምላክ ነው። ለመፈወስ እጁን ሲዘረጋ የሚቋቋመው የደዌ ዓይነት አይኖርም። እርሱ የለዎችን ሁለንተና ይፈውሳል። ይህንን አገልግሎት ለተከታዮቹም አስረክቧል (ማቴ. 10: 1፣ 28:19-20፣ ማር. 6:7-13፣ 2ቆሮ. 5:19-20)። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ፈውስ በተለያየ ዓይነት ይፈጸማል። ከእነዚህም:-

1. <u>በእግዚአብሔር ቃል</u>
   «በተጨነቁ ጊዜም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ከመከራቸውም አዳናቸው ቃሉን ላከ ፈወላቸውም ከጥፋታቸውም አዳናቸው» (መዝ. 107፣19-20)። ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል የመዳንን መንገድ አሳይቷቸው ከእርሱ ጋር ታርቀው ያለ ምንም ሌላ ዘዴ ከበሽታቸው ተፈውሰዋል።
2. <u>በሕክምና አገልግሎት</u>
   እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የመመራመርና የማጥናት ልዩ ልዩ የሕክምና ዘዴዎችንና የመድኃኒት ፈጠራ ችሎታ ሰጥቶአዋል። በመሆኑም እኛ ዘመናዊ ሕክምናን

እንደ እግዚአብሔር መልካም ሰጦታ አድርገን እንቀበላለን።

3. <u>በቅዱሳት ምሥጢራት</u>
   ከጨለማ ዓለም ክርስቶስን ወደ ማወቅ ሲመጡና ሲጠመቁ ከሥጋ ደዌና ከአጋንንት እስራት የተፈወሱ ጥቂቶች አይደሉም። በተመሳሳይ በቅዱስ ቊርባን የኢየሱስን ሥጋና ደም ተቀብለው ብዙ ሕመምተኞች ሲፈወሱ እናያለን።
4. <u>በምክር አገልግሎት</u>
   በምክር አገልግሎትም ሰዎች በመጀመሪያ ደረጃ ከእግዚአብሔር፣ ሁለተኛ ከባልንጀራቸውና ከራሳቸው ጋር ታርቀው ከብዙ ከባድ በሽታ ይፈወሳሉ። ጭንቀትና መከራ ራሱ በሽታ ሲሆን ከጭንቀት የተነሣ ደግሞ ብዙ አካላዊ በሽታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ።
5. <u>በፀሎት አገልግሎት</u>
   እኛ ተከታዮቹ የሆንን ክርስቲያኖች በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት በቃሉ ግልጽ ትእዛዝ ለሕሙማንና በአጋንንት ለታሰሩት በኢየሱስ ስም እንጸልያለን፤ እርሱም ይፈውሳቸዋል። እግዚአብሔር የታመሙ ሰ ዎችን ጸሎት ይሰማል።

በእምስቱም ዓይነት አገልግሎት ፈዋሹ እግዚአብሔር ነው። ክርስቲያን አገልጋዮች፣ ወንጌላውያንና ቄሶች፣ ሐኪሞች ወይም አማካሪዎች ብንሆን ተቀጥረንም ሆነ በፈቃደኝነት የምናገለግል የጌታ ረድኤት ያስፈልገናል። ክርስቲያን ሐኪም ሥራውን በጸሎት ይጀምራል። ሰው በተማረውና በለመደው እውቀትና ሙያው ቀኑን በሙሉ ቢሠራም ከፈጣሪ ምክርና ምሪትን ይጠይቃል። የእግዚአብሔ ር ፈዋሽ ኃይል ሲጨመር ቀዶ ጥገናና መድኃኒት ውጤታማ ይሆናል።

የተለያየ ውስጣዊ ወይም አካላዊ ሕመም ያለበት ሰው ከሁሉም በላይ ፍቅርና መጽናናትን ይፈልጋል። የቃል እውቀትና የስብከት ዘዴ፣ የሕክምና ሙያና የምክር አገልግሎት እውቀት ያስፈልገናል። ከዚህም በላይ በአገልግሎታችን ከጌታ የምንቀበለው የፍቅር ሙላት ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር በሚያውቀው በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሰው ሁሉ በዚህ ምድር ከበሽታው ወይም ከጎደሎነቱ ነፃ ላይሆን ይችላል። ሐዋርያው ጳውሎስም የሥጋ መውጊያ ከእርሱ እንዲለይ በፀለየ ጊዜ «ጸጋዬ ይበቃሃል ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና»(2ቆሮ.12:9)



የሚል መልስ አገኘ። ብዙ ቅዱሳን የተለያየ የአካል ጉዳተኝነት ኖሮአቸውም ጌታን ያገለግላሉ። እኛ አገልጋዮች በሰዎች ሕመምና በቊስላቸው ላይ ተጨማሪ ቊስል እንዳንጨምር መጠንቀቅ ይኖርብናል። ጌታ ያሸከማቸውን ሸክም ወይም መስቀል እስኪለማመዱ ድረስ በአጠገባቸው በዝምታ በአክብሮትና በፍቅር መቆየት ይሸለናል። ላንችኩል እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ላናበላሽ ፈዋሽና አፍቃሪ በሆነው አምላክ እንታመን። ምናልባት ከዚህ ዓለም የሚጠራበት ጊዜ ደርሶ እንደሆነ መገንዘብ፤ ከአምላኩ ጋር እንዲገናኝ ማዘጋጀትና ምድራዊ ነገሮቹንም እንዲያስተካክል መርዳት መቻል አለብን።

በፀሎት የምናገለግለው ሰውም ደካማ ሥጋና ደም ያለው ሰብዓዊ ፍጡር መሆኑን አንርሳ። አንዳንድ ጊዜ አገልግሎቱ ብዙ ቀናት እንኳ ሊወስድ ይችላል። የታመመው ሰው እንዲበላና እንዲታጠብ፣ እረፍት እንዲለማው ብርድም እንዳይጎዳው ለማድረግ ኃላፊነት መውሰድ አለብን። በአንዳንድ ቦታ ከማስተዋልና ከልምምድ ማነስ የተነሣ በታማሚው ጆሮ ላይ በኃይል መጮህ ወይም አንገቱን በጉልበት መያዝ የመሳሰሉ መደረግ የሌለበት ነገር ነው። ጋኔንም ቢሆን ወይም ሌላ በሽታ የምናሸንፈው በድምፃችን ብዛት ሳይሆን በመስቀሉ ላይ ድል በሰጠን በኢየሱስ ስም ብቻ ነው። የሚሰቃየውን ጠላት ስንጠላው ሕመምተኛውን ግን በፍቅርና በአክብሮት መያዝ ያስፈልጋል። የታመመው ሰው መፈወሱ ሳይረጋገጥ ተፈውሶአል ብሎ ማረጋገጫ አለመስጠትና መድኃኒት ከመጠቀም አለመከልከል፣ እንዲሁም የእእምሮ ሕመምንና ጭንቀትን ወይም የመንፈስ መታወክን ከአጋንንት ለይተን ማወቅ አለብን። እንዲፈወስ በመጸለይ ምክር መስጠት እንጅ የእምሮ ሕመም ወይም የመንፈስ ጭንቀት ካለበት ሰው አጋንንትን ማውጣት መሞከር ፍጹም ስሕተት ነው፡

### 3.3. ዲቁናና የማማከር አገልግሎት

ሰዎችን ከመንፈሳዊና ከማኅበራዊ ችግሮቻቸው ማላቀቅ ከዲቁና አገልግሎት አንዱ ክፍል እንደሆነ መገንዘብ መልካም ነው። በእብያተ ክርስቲያናት ለምክር አገልግሎት በቂ ትኩረት ባይሰጥም ብዙ ማኅ በራኑ ምእመናን ግን አገልጋዮችን አሠልጥነው ይመድባሉ። እነዚህ ሠልጣኞች እንደ አንድ የአገልግሎት ቡድን ሆነው በመንፈሳዊና በትዳር ችግሮቻቸው ምእመናንን ያገለግላሉ። ስለ ምክር አገልግሎት ከሌሎች መጸሕፍት ሰፊ ትምህርት ማግኘት ይቻላል። የዲቁና አገልግሎትና የምክር አገልግሎት ብዙ ግንኙነት አላቸው። ይህን በሚመለከት በዚህ መጽሐፍ ባጭሩ እንመለከታለን። ለሰዎች ችግር እውነተኛ መፍትሔ ሰጪ እግዚአብሔር ነው። ቢሆንም እግዚአብሔር

ደግሞ አንዳችን ለአንዳችን መካሪዎችና ረዳቶች አድርጎ በምድር አስቀምጦናል:: እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን (1ቆሮ. 12:4-17፣ 1ጴጥ. 4:10-11) በተሰጠን ጸጋ መጠን ተግተን ልናገለግል ታዘናል:: «የሚመክር ቢሆን በመምከሩ ይትጋ» በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ትእዛዛዊ የሆነ አገልግሎት ይሰጠናል(ሮሜ.12:8)::

ኢየሱስ እውነተኛ መካሪ ነው:: ክርስቲያኖችም የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል የምክር አገልግሎት መስጠት ይገባቸዋል:: የዮሐንስን ወንጌል በተለይ አራተኛውን ምዕራፍ ስናነብ የአንዲት ሳምራዊት ሴት ታሪክ እናገኛለን:: ይህች ሴት ከአይሁድ ወገን ውጭ የሆነች ናት:: መንፈሳዊ ኑሮዋ የተበላሸና ከኅብረተሰቡ ጋር መልካም ግንኙነት የሌላት ብዙ ባሎች ያሉአት ሴት ነበረች:: ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ከተማ ልኮ ለብቻው አነጋገራት:: ራሱን ዝቅ አድርጎ በትሕትና ውሃ እንድትሰጠው ለመናት:: እርስዋ ግን የባህል ተጽዕኖ ስለነበረባት በራስዋ መቅጃ ለመስጠት ተጸይፋ መቅጃ የለህም? አለችው:: ጌታ ግን በትዕግሥት ያዳምጣት ነበር:: ከዚህ የተነሣ ቀስ በቀስ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት አመጣት:: የምክር አገልግሎት በማስተዋልና በፍቅር ማድመጥን ይጠይቃል:: የምንመክራቸው ሰዎች የእኛን የአፍ ንግግር ብቻ ሳይሆን ስሜታችንን፣ አቀራረባችንና የምናሳየውን ፍቅር ሁሉ ይመለከታሉ:: ችግራቸውን ሲነግሩን በፍቅርና በሃዘኔታ ከቀረብናቸው ምሥጢራቸውን ጭምር ሊገልጡልን ይችላሉ:: ስለዚህ ቶሎ ብለን ምክር ለመስጠት አለመነሣትና በእርጋታ ችግራቸውን መ ረዳት ለመፍትሔ ጠቃሚ መንገድ ነው::

ብዙ ሰዎች ችግራቸውን የሚያካፍሉት ሰው አጥተው በጨለማ ውስጥ ይኖራሉ:: እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ከገንዘባችን ይልቅ ምክራችንን ይፈልጋሉ:: የሰዎች ችግር አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላል:: የጋብቻ ችግር፣ የኑሮ ችግር፣ የሥራ ማጣት ችግር፣ ከቤተ ሰብ ተለይቶ የመኖር ችግር፣ ልጅ ያለመውለድ ችግር፣ ራስን ክሰው በታች አድርጎ የመቊጠር ችግር፣ የወሲባዊ ፈተና ችግር፣ የኤድስ ቫይረስ ተሸካሚ የመሆንና የሞት ፍርሃት ችግር፣ የተለያየ የመንፈሳዊ ሕይወት ችግር፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል::

የምንረዳቸው ሰዎች ብዘውን ጊዜ ውስጣቸው የቈሰለ፣ ተስፋ የቈረጡ፣ ራሳቸውን የሚንቁ፣ በዙሪያቸው ባሉት ሰዎች ላይ በምክንያት ይሁን ያለምክንያት ያዘኑባቸው፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ክርክር ያላቸው ሰዎች ናቸው:: የችግራቸውን መነሻ ለማጥናትና



በጋራ የመፍትሔ ሐሳብና እቅድ ለመፈለግ በምንቀርባቸው ጊዜ የምክር አገልግሎት ትዕግሥትና ጥንቃቄ ይፈልጋል::

እንደ ግለሰቡ ችግርና ሁኔታ የምክር አገልግሎት አሰጣጥም ይለያያል:: ጥቂት መሠረታዊ መመሪያዎችን በማንኛውም ዓይነት ምክር ጊዜ ማስታወስ ተገቢ ነው::

1. <u>የቦታና የጊዜ ምቹነት</u>

   በግለሰቡ ጉዳይ ትርፍ ሰው መግባት የማይችልበት ውጫዊ ድምፅ የማይሰማበት፣በስልክም ሆነ በሌላ ነገር የማንረበሽበት ቦታና ለተረጂ ምቹ የሆነ የተወሰነ ጊዜና ሰዓት መምረጥ አለብን::

2. <u>ጾታ</u>

   ቢቻል አማካሪና ተረጂ ተመሳሳይ ፆታ ቢሆኑ ይመረጣል:: በተለይም ወሲባዊ ችግር ሲኖር ሴት ከሴት ወንድ ከወንድ ጋር ቢወያዩ ነፃነት ይሰጣል::

3. <u>ምሥጢር ጠባቂነት</u>

   ብዙ ጊዜ የምክር አገልግሎት በዚህ ጉዳይ ላይ የተሟላ አይደለም:: ምሥጢራቸው ወደ ሰው ይደርሳል ብለው በመፍራት ምንም ከባድ ችግር ውስጥ ቢኖርባቸውም እንኳን ላይ ላዩን እንጂ ዋና ችግራቸውን ለመንገር አይደፍሩም:: አገልግሎቱ ውጤታማ እንዲሆን ከፈለግን መጀመሪያ በረጂና በተረጂ መካከል መተማመንን መፍጠር መቻል አለብን:: በምክክር ጊዜ የሰማነውን በፍጹም ለማንም መናገር የለብንም::

4. <u>ቋንቋ</u>

   ቢቻል ሰው በራሱ ቋንቋ መናገር መቻል አለበት:: ይህ ብቻ ሳይሆን ከባሕላዊና ከአካባቢ ልምድ የተነሣ ስለ አንዳንድ ነገር መናገር አሳፋሪ ሊሆን ይችላል:: እርሱንም ቀስ ብለን በጥንቃቄ ማስረዳት እንችላለን::

5. <u>ማዳመጥ</u>

   ሰው የራሱን ችግር በነፃነት እንዲናገር ጊዜ መስጠትና በየመሐሉ አንዳንድ ጥያቄ መጠየቅ ማዳመጣችንን ለመግለጽ፣ ለእኛም ግልጽ እንዲሆንልን ይረዳል:: ማዳመጥ ስንል በጆሮ ብቻ ሳይሆን ችግረኛው በአካሉ የሚገልጸውን

ሁኔታ ማለት፣ (ፍርሃትን፣ መጨነቅን፣ ተስፋ መቁረጥን) በዓይናችን ማየት እንችላለን::

6. <u>የስሜት አገላለጽ</u>

አማካሪው አክብሮት፣ ፍቅርና ተቀባይነትን አሳይቶ የተ ረጂውን ማንኛውም ስሜት ቊጣውንም፣ ማልቀሱንም ያለ ክርክር መቀበል አለበት:: ከውስጡም እንዲወጣለት ጊዜ መስጠት ይኖርበታል::

7. <u>ሐቀኛነት</u>

ውሸት የተቀላቀለበት ንግግር፣ መሠረት የሌለው ተስፋ መናገር ተገቢ አይደለም::

8. <u>ማስተማርና ጥቆማ መስጠት</u>

አንድ ሰው ስሜቱና ሐሳቡ ከተረጋጋ በኋላ አዲስ ነገርን ለመቀበል ይችላል:: ከትምህርቱ ወይም ከተሰጠው አማራጭና ሐሳብ ውስጥ ራሱ መፍትሔ ሐሳቦችን ሊያገኝ ይችላል::

9. <u>አለመፍረድ</u>

ተረጂው የማያዋጣውን መንገድ ወይም መፍትሔ ቢመርጥ እንኳን በጥያቄና በተለያየ አቅጣጫ ነገሩን እንዲመለከት ለመርዳት እንጂ፣ አይሆንም፣ ጥሩ አይደለም በማለት መዝጋት የለብንም::

10. <u>ክትትል</u>

ሰው በአንድ የምክክር ጊዜ ለችግሩ መፍትሔ ላያገኝ ይችላል:: በመሆኑም ለተረጂው በሚመች ሰዓት ጊዜ ሳይሰጥ አዲስ ቀጠሮ በመስጠት የሁኔታና የባሕርይ ለውጥ እንዳለ ለማየትና የጀመረውን እንቅስቃሴ ለማበረታታት ይረዳል:: ለሚቀጥለውም ቀጠሮ የቤት ሥራ ለመስጠት ይቻላል::

አንዳንድ ጊዜ ክትትል ለረጅም ጊዜ አስፈላጊ ቢሆንም እኛ የሰውን ኑሮ ልንኖር፣ ላልተወሰነ ጊዜ ልንሸከመው አንችልም:: ደግሞም ጥገኝነት እንዳንፈጥር በጣም መጠንቀቅ አለብን:: ከመጀመሪያ ጀምሮ ዓላማችን ተረጂው ራሱን እንዲችልና ሌሎችን ለመርዳት እንዲበቃ ነው::

በአጠቃላይ ችግረኞችን ለመርዳት በሚሰጠው አገልግሎት ምክር ሰጪው መፍትሔ አቅራቢ መሆን የለበትም:: ትልቁን ሥፍራ ሊወስዱ የሚገባቸው ራሳቸው ችግረኞቹ ናቸው:: ምክር ሰጪ ጠቋሚ



መንገድ መሪና አቅጣጫ የሚያሳይ ሆኖ ከቀረበ ወደፊት ከችግራቸው እንዴት እንደሚላቀቁ ራሳቸው ያውቃሉ::

የደረሰባቸው መከራ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን በመከራ ማለፍ ወደ ድል መገስገሻ እንጂ መጥፊያ አለመሆኑን ማሳየት አስፈላጊ ነው:: «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው:: ከተ ፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበላልና»በማለት ሐዋርያ ያዕቆብ ያሳስበናል(ያዕ. 1:12-13)::

አንዳንድ ሰዎች ችግራቸው ትንሽ ሆ ኖ እያለ አውግዘፈው ሊናገሩ ይችላሉ:: ሌሎች ግን ትልቅ ችግር እያለባቸውም የሚገልጡበትን መንገድ አያውቁም:: በአፋቸው የማይጮኹትን እንደእነዚህ ዓይነቶቹን ከሁኔታቸው መረዳት አለብን::

የማማከር አገልግሎት አስቸጋሪ ነው:: እርሱን ለማከናወን የመንፈስ ቅዱስ ረድኤትና ምሪት ያስፈልጋል:: የሰውን ውስጣዊ ምሥጢር የሚያውቀውን ጌታ በጸሎት መለመን አስፈላጊ ነው:: ይህንን ስንል ግን ሰዎችን ለመርዳት ጸሎትና መንፈሳዊ ልምዶችን አቋራጭ መንገድ አድርገን መጠቀም አይገባንም:: የእርስ በርስ ችግራችንን እንድንሸካከም ቃሉ ያዘናል:: ምንም መንፈሳውያን ብንሆን ሰለው ሰው ያስፈልገዋል:: ጌታ ኢየሱስም ሰዎችን ሲቀርብ ችግራቸውንና ብሶታቸውን ራሳቸው እንዲናገሩ ፈቀደላቸው:: በመስቀል ተሰቅሎ እያለ እንኳ እናቱን ለዮሐንስ ፣ዮሐንስን ደግሞ ለእናቱ አደራ ሰጠ (ዮሐ. 19:26-27)::

### 3.4. ዲቁናና የአካል ጉዳተኞች እንክብካቤ



«ድሆች ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ » ሉቃ 14፡ 16-24
በቤተ ክርስቲያን መታቀፍ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች አንዳንዶቹ የአካል ጉዳተኞች ይሆናሉ። ለምሳሌ፡- መስማትና ማየት የተሳናቸው፣ ሽባዎች፣ የአእምሮ እድገት ዘገምተኞች እንዲሁም ሌሎች ሊሆኑ ይችላሉ። አካል ጉዳተኛ ማለት እንደማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ ነው (ዘፍ. 1፣26-27= 31)። የአካል ጉዳተኛ በሰውነቱ ላይ ችግር የደረሰበት ሰው እንጂ ከሌላው ሰው አንሶ የተ ፈጠረ አይደለም። እግዚአብሔር አይሳሳትም። ጎደሎነትን መቀበል ቢከብድብን እንኳን እግዚአብሔር ባደረገው ወይም በፈቀደው ሁኔታ ሁሉ የተሰወረ ዓላማ አለበት። በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ከቶ ማፈር አይገባም።
የአካል ጉዳተኝነት በሁለት መልክ ሊከሰት ይችላል።

1. ከውጫዊ ሁኔታ ገና በእናት ማኅፀን እያሉ በመድኃኒት፣ በአልኮል አንዳንዴም በእርግዝና ወቅት እናትየዋን ከሚያጋጥማት በሽታና ችግር እንዲሁም በአወላለድ ጉዳት ወይም በኋላ ከሚያጋጥም አደጋና በሽታ፣
2. ከዘር የሚተላለፍ (በአባት ወይም በእናት በኩል ተመሳሳይ ችግር ሲኖር) ነው።

እላይ እንደተመለከትነው የአካል ጉዳተኝነት የሚመጣው በእግዚአብሔር ቍጣ አይደለም። ስለዚህ የአካል ጉዳተኞችን እግዚአብሔር እንደፈረደባቸው አድርገን ማየት የለብንም። ለማንኛ ውም ሰው የሚያስፈልጉ ነገሮች፤ ልብስ፣ ምግብ፣ መጠለያ፤ ፍቅር፣ መሥራትና ማግኘት . . . ወዘተ ለእነርሱም ያስፈልጋቸዋል። እኛ በጤናማ የአካል ክፍላችን ተንቀሳቅሰን ስንሠራ እነርሱም ባልተጎዳው የአካል ክፍላቸው መሥራትና ማሰብ ይችላሉ። ለምሳሌ የእግር ችግር ያለባቸው ተቀምጠው በእጃቸው ይሠራሉ፣ የእጅ ችግር ያለባቸው ተቀምጠው በአእምሮ በማሰብ ምክርና ትምህርት ሌላም ነገር ሊያበረክቱ ይችላሉ። መስማት የተሳናቸው በምልክት ቋንቋ ስለሚማሩ ማንኛውንም ሥራ ይሠራሉ። ማየት የተሳናቸው በብሬል ይጽፋሉ፣ ያስተምራሉ፣ በእጃቸውም ይሠራሉ። ለምሳሌ በዓለም አቀፍ የታወቀች ሄሌን ኬለር የተባለች ማየትና መስማት የማትችል አሜሪካዊት ሴት በዘመኗ (1880-1968) ለዓለም የአካል ጉዳተኞች እጅግ ብዙ አስተዋጽኦ አበርክታለች። ዛሬ ደግሞ ከ17 ዕድሜዋ ጀምራ ከአንገቷ በታች ሽባ የሆነች በአፏ የምትጽፍ፤ እውቅ ሠዓሊ የሆነች ከረዳት ቡድንዋ ጋር በመላው ዓለም እየዞረች ለአካል ጉዳተኞች



መንፈሳዊ ሕይወትንና ኑሮ የሆነች ጃኒ ኤሪክሰን የምትባል ባለ ትዳር የተስፋ መልክተኛ ነች።

የአካል ጉዳተኞች ከሕፃንነታቸው አንሥቶ የራሳቸውን ኑሮ መኖር ይፈልጋሉ። እነዚህ ወገኖቻችን አንዳንዴ ወደአሰቡበት ግብ መድረስ ሊከብዳቸው ይችላል። ይሁን እንጅ ሰው በተለያየ ድጋፍ ወደ ደረሰበት የእውቀት ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ ለቤተሰቦቻቸው ሥነ ልቦናዊና መንፈሳዊ እገዛ ያስፈልጋቸዋል። የእነርሱ ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ፍላጎት መረዳት አለባቸው እንጂ የራሳቸውን መመሪያ ብቻ እንዲከተሉ ማድ ረግ የለባቸውም። «አትችልም» የሚል ቃል መጠቀም ተገቢ አይደለም። ወደ ሚፈልጉት ደረጃ ለማድረስ ግን ማነሣሣት አለባቸው። እንዲሁም በራስ መተማመን ወደ ራስ ውሳኔ እንደሚያደርሳቸው አውቀው መርዳት አስፈላጊ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ዕለታዊ ኑሮአቸውን ለማመቻቸት እንደ ምርኩዝ፤ ተሽከርካሪ ወንበር፤ እንዲሁም ለመጸዳጃ የሚውል ክፍት ወንበርና ባልዲ፤ የመሳሰሉ ለተጎዳው የአካል ክፍላቸው የሚረዱ ጠቃሚ ዕቃዎችን ማግኛ መንገድ መፈለግ ይገባል። እነዚህንም መሣሪያዎች ለማግኘት ወደ ትልልቅ ከተማዎች ብቻ መሄድ ሳይሆን በኣከባቢው የሚገኙትን የኀብረተሰብ ክፍሎች በማስተባበር መሥራትም ይቻላል። የአካል ጉዳተኞች ወደ ቤተ ክርስቲያን ወይም እንደ ባንክ ወዳሉ ሕዝባዊ የአገልግሎት ቦታዎች ቤት በተሽከርካሪ ወንበር መግባት የሚችሉበትን መግቢያ መሥራት ይቻላል።

የአካል ጉዳተኞች እንደ አቅማቸው በማንኛወም ዓይነት አገልግሎት ሊመደቡ ይችላሉ። የጸጋ ስጦታ ለማንኛም ሰው ነጻ ስለሆነ በአካላዊ አቋማችን ተለክቶ የሚሰጥ አይደለም። በሰማይ ደግሞ የአካል ጉዳተኝነት የለም። በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተ ፈጠርን ሁላችን አንዱን ሰማያዊ አካል እንለብሳለን። እንዲሁም በትምህርት ቤት ገለልተኝነት እንዳይሰማቸውና ያለችግር እንዲማሩ መምህራንና ተማሪዎች በአስፈላጊ ነገሮች እንዲተባበሩ ማስተማርና ማነሣሣት ይገባል።

### 3.6. የእእምሮ እድገት ዘገምተኞች

የአእምሮ እድገት ዘገምተኝነት ደረጃ አለው። አንዳንዶች በአካል አድገው ዕለታዊ ተግባራቸውን ማለት እንደ መብላት፣ መልበስ፣ መጸዳዳት ያሉትን ነገሮች ራሳቸው አውቀው መፈጸም ይችላሉ። በሌላ ሰው መሪነት የጉልበት ሥራ ለመሥራት የሚችሉ ይሆናሉ።

በአእምሮና በማስተዋል ግን ዕድሜ ልካቸውን እንደ ሕፃናት ሆነው ይቀራሉ።

የአእምሮ እድገት ዘገምተኝነት በጣም ከፍተኛ ከሆነ ዕለታዊ ተግባራቸውን መፈጸም፣ መናገርና በእልጋቸው ላይ መገላበጥ እንኳ አይችሉም። እነዚህን ማድረግ ባይችሉም ለእግዚአብሔር አምላክ ውድ ልጆቹ ናቸው። የወገኖችንም ፍቅርና ድጋፍ ይፈልጋሉ። የአእምሮ እድገት ዘገምተኞች የማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ የሕክምናና የጸሎት እገዛ ያስፈልጋቸዋል። በተለይ የዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ቤተሰቦች ስለ ልጆቻቸው እጅግ ይጨነቃሉ። እንዲድኑ በማሰብ ወደ ሆስፒታልና ባለመድኃኒቶች ዘንድ ያመላልሱአቸዋል። መድኃኒት ይገኝበታል ወደ ተባለ ሥፍራ ሁሉ ማለት እስከ ጠንቋይ ቤት ድረስ ይወስዱአቸዋል። ይህም በገንዘባቸውና በንብረታቸው ላይ ጉዳት ከማስከተሉም በላይ የአእምሮ ጭንቀትን ይፈጥራል። ከዚህ የተነሣ ጤናማ የቤተሰብ ኑሮ ይቃወሳል። እነዚህ ቤተሰቦች በቂ ድጋፍና እገዛ ቢያገኙ አመለካከታቸው ተቀይሮ ችግሩን እንደ እርግማን ሳይሆን እንደ በረከት ሊቈጥሩት ይችላሉ።

### 3.7. ዲቁናና ኤድስ



ስለኤድስ ስንለማ የራሳችንም ሆነ የኅብረተሰባችን አመለካከት ከበሽታው ሁኔታ የተለየ ነው። በተለይም ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ከኃጢአትና ከእግዚአብሔር ቍጣ ጋር ያያይዘዋል። ለመሆኑ ኤድስ የእግዚአብሔር ቍጣ በሰዎች ላይ የመገለጥ ምልክት ነው? ወይስ ሌላ ከሌሎች በሽታዎች በተለየ መልኩ አስደንጋጭ የሆነው ለምንድን ነው? ዲቁናንና ኤድስን ምን ያገናኛቸዋል? በእነዚህ ጥያቄዎች መሠረት ስለ ኤድስ በአጭሩ እንደሚከተለው እናያለን።

እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በልዩ ልዩ ደዌ እንደሚቀጣ በብሉይ ኪዳን ተጽፎ እናገኛለን (ዘሌዋ. 26:14-33፤ዘዳግ.28:15-46)። የአይሁድ ሕዝብ ከዚህ ቃል የተነሣ በሰዎች ላይ የሚደርሰው በሽታም



ሆነ መቅሠፍት የእግዚአብሔር ቍጣ እንደሆነ ማየት ባሕላቸው ነው። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጌታችን ያስተማራቸውን ትምህርቶች ስንመለከት በማቴዎስ 5፡ 46 «እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናብን ያዘንባልና» ይላል። እንዲሁም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር ስለነበረ ሰው «ይህ ሰው ዕውር ሆ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ? ብለው ደቀ መዛሙርቱን በጠየቁት ጊዜ . . . እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም በማለት መልሶላቸዋል። እንዲህ ከሆነ የኤድስ በሽተኞችን ከሌሎች ለይተን እንደ ኃጢአተኞች መቁጠር እንዴት ይቻላል?

ኤድስ ወንዶችን፣ ሴቶችን፣ ያገቡትንና ያላገቡትን፣ ሕፃናትንና አዛውንትን፣ በአጠቃላይ የሰውን ዘር በሙሉ ሊያጠቃ የሚችል ፈጽሞ ከሰው ዘንድ ፈውስ ያልተገኘለት በሽታ ነው።

በሽታው የሚተላለፍባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው።

1. ልቅ በሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣
2. ደምን በመለገሥ፣
3. ንጽሕናው ባልተጠበቀ መርፌና ሌሎችንም ስለታም ነገሮች በጋራ በመጠቀም፣
4. ከእናት ማኅፀንና ጡት ወደ ልጆች ሊተላለፍ ይችላል።

ይህ የሚሆነው የቫይረሱ ተሸካሚ የሆነ ሰው አላይ በተጠቀሱት መንገዶች ወደ ጤነኛ ሰው ሊያስተላልፍ ሲችል ብቻ ነው እንጂ በምግብና በውሃ እንዲሁም በትንፋሽ ወይም በሌላ መንገድ አይተ ላለፍም። የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ አደገኛነት በሰዎች ደም ውስጥ ራሱን ሳይገልጥ ለብዙ ዓመታት ሊቆይ የሚችል ስለሆነና ከደም ምርመራ በስተቀር የቫይረሱ ተሸካሚዎች መሆናቸውን ማወቅ ስለማይቻል ነው።

ኤድስ በብዛት ልቅ በሆነ ግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሚተላለፍ የሚታወቅ ስለሆነ ከኃጢአት ጋር ይገናኛል። ሰዎች ኤድስ የሚተ ላለፍባቸውን መንገዶች እያወቁ የአልኮል ሱስና ልቅ የሆነ ወሲባዊ ልምድ ከታሠሩ ከእንዲህ ዓይነት እስራታቸው ያለመንፈስ ቅዱስ ረድኤት በቀላሉ ነፃ ሊወጡ አይችሉም። በመፍረድና በመጸየፍ ማንንም ለመርዳት አንችልም። አንድ ጊዜ ጻፎችና ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘችን ሴት በድንጋይ እንድትወገር ወደ ኢየሱስ ሲያመጡ ኢየሱስ የሰጣቸውን መልስ እናስታውሳለን። «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት» ባለ ጊዜ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና አንድ በአንድ ትተዋት ወጡ። ኢየሱስም

ሰሴቲቱ፣ «እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢያት አትሥሪ» አላት (ዮሐ 8.1-11)። ጌታ ኢየሱስ ኃጢአትን ይጠላል ኃጢያተኞችን ግን ይወዳል። በገዛ ራሱ ሕይወቱን ያበላሸውንና የጠፋውን አንኳ ጌታ ኢየሱስ በፍቅሩ ይፈልገዋል።

የእግዚአብሔር ሕግ የሕይወት ሕግ ነው። «አታመንዝር» የሚለው ትዕዛዝ ዓላማ ሰዎችን ከብዙ ዋይታና ለቅሶ ለመጠበቅና ወንድና ሴት አንድ ለአንድ ሆነው በተቀደሰ ትዳር ፣በፍቅር፣ በደስታና በጤና እንዲኖሩ ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ በፍጹም ግልጽነት የምንሰብከው ሰው ሁሉ ወደ ጌታ ኢየሱስ እንዲመጣና አዲስ ፍጥረት እንዲሆን ነው። ሕግ ወደ ክርስቶስ ይመራናል እንጂ ሕይወትን የመስጠት ኃይል የለውም። ከክርስቶስ ጋር እንድንሰቀል፣ ከእርሱም ጋር ደግሞ በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ተጠርተናል (ሮሜ 6:1-4)።

በመሆኑም ሕያው የሆነውን የእግዚአብሐር ቃል በመስበክ በመንፈስ ቅዱስ እገዛና ኃይል ሰዎች በአዲስ ሕይወት እንዲመላለሱ ወደ ኃይሉ ምንጭ መምራታችን ከሁሉም የሚበልጥ የኤድስ መከላከያ አገልግሎት ነው። ይሁን እንጂ ጌታን ወደ ማወቅ ሳይመጡ በፊት ወይም በድካማቸው በኃጢአት ወድቀው በኤድስ ቢታመሙ እንኳ እግዚአብሔር እኛን ከብዙ ኃጢአታችንና ድካማችን እንደማረን ለኤድስ ሕሙማንም በእግዚአብሔር ምሕረትና ይቅርታ፣ አዲስ ዕድልን ማቅ ረብ አለብን። አንተስ/አንቺስ ከኤድስ ሕሙማን በምን ትበልጣለህ/ ትበልጫለሽ/? እግዚአብሔር ባይጠብቀን ኖሮ ሁላችን በጠፋን ነበር።

መጀመሪያ ኃላፊነታችን ሰዎች ከዚህ ከክፉ በሽታ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ማስተማር ቢሆንም፣ በኅብረተሰባችን በየመንደሩና በየከተ ማው ብቻቸውን ተደብቀው የሚያለቅሱ፣ ከዘመድና ከጎረቤት ገለልተኛ የሆኑ ወገኖቻችንን መድረስ ትልቅ ኃላፊነት ነው። እንዲሁም የኤድስ ችግር ከሌላ ችግር ጉልቶ ስለሚታይ በዲቁና አገልግሎታችን ልዩ ትኩረት መስጠት አለብን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ወደ ኃጢአተኞችና ወደታመሙት ሲሄድ ፈሪሳውያን አንጎራጎሩበት። ኢየሱስም ሰምቶ «ሕመምተኞች እንጂ ባለጤናዎች ባለመድኃኒት አያስፈልጋቸውም ነገር ግን ሄዳችሁ ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ተማሩ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና» (ማቴ. 9:12-13) አላቸው።



የኤድስ ሕሙማንና ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናት ከእኛ ይልቅ ኃጢአተኞች አይደሉም። እንዲሁም በልበ ጠንካራነታችን የተቸገረውን ወደ ሞት የደረሰውን ልብስና የዕለት እንጀራ መጠለያም ያጣውን አለመርዳታችን ኃጢአት ሆኖ ይቈጠርብናል(ያዕ.4:17፣1:27፣1ዮሐ. 3:14-18)።

ሰዎች በኤድስ በሽታ የሚያዙት ሳያውቁ ጥንቃቄ በማያደርጉ በሌሎች ሰዎች አማካይነት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ወጣቶች ሳይመ ረመሩ ትዳር ቢመሠረቱ በኤዲስ ሊያዙ ይችላሉ። ንጽሕና የጎደለው መርፌ በመወጋት ወይም ወደጌታ ሳይመጡ በፊት በወጣትነታቸው ተሳስተው ወይም ተደፍረው ቫይረሱ ይዞአቸው ይሆናል። ስለዚህ ክርስቲያን አገልጋይ ሆይ፣ በምንም ዓይነት ሁኔታ በማንም ላይ መፍረድ አያስፈልግህም።

ከHIV/AIDS ጋር የሚኖሩትን እንዴት መርዳት ይቻላል?

1. በመጀመሪያ ደረጃ ፍቅርና አክብሮትን አሳይ። በቤቱ የሚያስፈልገው ነገር እንዳለ ጠይቀው። ኢየሱስም ዕውሩ በርጤሜዎስን፣ «ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? አለው»(ማር. 10:51)። ምንናልባት ሉቅ ወይም ገበያ የሚሄድለት ሰው የለውም ወይም የማገዶ እንጨት ወይም ውሃ አጥቶ ይሆናል። ምናልባት ወደ ዘመዶቹ መልእክት መላክ ይፈልጋል። ትልቁ ነገር ጊዜህንና ራስህን ፍቅርህንም መስጠት ነው። ሰላምታ መለዋወጥ፣ መተቃቀፍ፣ አብሮ ቡና መጠጣትና መጫወት ወዘተ... የፍቅር መግለጫዎች ናቸው።

2. የእርስ በርስ መተማመን ከተፈጠረ ያለምንም ችግር ወደ ምክር አገልግሎት መሻገር ይቻላል፡ በምክር አገልግሎት መሠረታዊ ዕውቀት ቢኖርህ ይመረጣል። ጌታ የሕመምተኛውን ልብ ካዘጋጀ ወደ መንፈሣዊ ምክክርና ጸሎት መሻገር ትችል ይሆናል። በዚህም የመንፈስ ቅዱስ ምሪት አስፈላጊ ነው። ጌታ እንዲፈውሰውም መጸለይ ተገቢ ነው። ነገር ግን ያለ ማረጋገጫ ተፈውሰሃል ማለት ትክክል አይደለም። እግዚአብሔር አይዋሽም ሰው ግን በአገልግሎቱ ሳይቀር ጎደሎነት ይርበታልና ሊሳሳትም ይችላል። እግዚአብሔር የህንን በሽተኛ ወደ ቤቱም የሚጠራበት ጊዜ ከደረሰም ለሰማያዊ ሠርግና ከንጉሡ ጋር ለመገናኘት እንዲዘጋጅ ማድረግ እንጂ ስለ ሞት በመናገር ፍርሃት እንዲሰማው ማድረግ አያስፈልግም። ማንም ሰው ይሞታል ሞትን ግን አይወድም። በተለይም አዳጊ ሕፃናት በቤቱ እያሉ ለእነርሱ ብሎ እንኳ ዕድሜው እንዲረዝም ይፈልጋል። እግዚአብሔር ንጉሥ ሕዝቅያስን «ትሞታለህ. . .ቤትህን አስተካክል»

አለው (2ነገሥ. 20:1)። ሕዝቅያስም እግዚአብሔርም ዕድሜን ጨመረለት። ነገር ግን ለመልካም ሳይሆን ለመሰናከል ሆነበት።

ወደ ጌታ ለመሄድ በቅድሚያ ራሳችንን ማዘጋጀት ትልቅ ዕድል ነው እንጂ ሞትን መጋበዝ አይደለም። ሁላችንም አንድ ቀን እንሞታለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በፊል. 1:21 «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፣ ሞትም ጥቅም ነውና» አለ። በሌላ ትርጉም ደግሞ «ሞትም ማትረፍ ነው አለ»። ከሞት ጋር የተስማማ ሰው ከሕይወትም ጋር ይስማማል። በሕክምና ዓለም አንድ የምናውቀው እውነት ወይም ሕግ አለ። በተመሳሳይ አካላዊ ሁኔታ ካሉት ሁለት በሽተኞች አንዱ በጭንቀትና በፍርሃት ሲሞት ሌላው ግን ከራሱና ከባለጋራው ከፈጣሪም ጋር ተስማምቶ ሰላም ያገኘ ሰው ብዙውን ጊዜ ዕድሜው ሲረዝም እናያለን። የታመመን ሰው ለሞት ማዘጋጀት ለቀሩት ቤተሰቦች በጣም ትልቅ ጠቀሜታ አለው። የንብረታቸውን ወይም የትዳራቸውን ሕጋዊነት፣ ወዘተ የማስተካከልን ነገር ሕመምተኛው መንቀሳቀስ ወደማይችልበት ወደ መጨረሻው ሰዓት ማቆየት ጥሩ አይደለም። በዚህ ሁሉ አንድ ሕመምተኛ ልባዊ ጥበብ ያለው ምክር ሰጪ ያስፈልገዋል። የተዘጋጀው ሰው ሳይሞት ቀርቶ ዕድሜው ሲጨመርለት እያንዳንዱን ቀን እንደ አዲስ ስጦታ ይቀበላል።

3. ሕመምተኛው እየደከመ ሲሄድ ብዙ ዓይነት የሕክምና እርዳታና እንክብካቤ ያስፈልገዋል። በአካባቢህ ወዳለው የኤች አይ ቪ / አድስ ተቋም ሄደህ ተጨማሪ ትምህርትና ምክር መፈለግ ጠቃሚ ይሆናል። አትፍራ፣ በሚሰጥህን መመሪያ መሠረት ጥንቃቄ እያደረግህ እስከመጨረሻ ከሕመምተኛው አትራቅ፣ ዋጋህ ትልቅ ነው፣ በስውር ያደረግኸውን የፍቅር አገልግሎት በሰውር የሚያይ አባትህ ዋጋህን በግልጽ ይከፍላል (ማቴ 6:4) ።

4. በአፍሪካ አገሮች ከኤድስ የተነሣ ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናት ቊጥር እጅግ በዝቷል። እነርሱን ለመርዳት የተዘጋጁ ድርጅቶች አልፎ አልፎ ቢታዩም በገንዘባቸው ሙሉ መፍትሔ ልናገኝ አንችልም። የክርስቶስ ቃል በማቴ. 18:5፣ ማር. 9:37፣ ሉቃ. 9:48 ልቦናችንንና ቤታችን እንድንከፍት ይጋብዘናል «እንደዚህ ያለውን ሕፃን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል የሚያሰናክል ግን ከባድ ፍርድ ይጠብቀዋል» (ያዕ 1:27)። ደግሞ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆች በችግራቸው መርዳትን ከአምልኮ ጋር ያገናኛል። ምንናልባት በእምነት ሳንጠራጠር እንደነዚህ አይነት ያሉ ሕፃናትን ወደ ቤታችን ብንቀበል፣ ሰማያዊ አባታችን የዕለት እንጀራ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ይሰጠናል።



በእምነት ለሚታዘዙ እግዚአብሔር ልዩ በረከትን እንዳዘዘላቸው ብዙ ምስክርነቶች አሉ።

5. ከኤድስ የተነሣ የልጆች ወላጆችን ማጣት ብቻ ሳይሆን ወጣት ልጆቻቸውን ያጡ ወላጆችም ብዙዎች ናቸው። እነዚህ ወላጆች ተቸግረውም ቢሆን ልጆቻቸውን አሳድገው፣ በማስተማር «በስተእርጅናችን በተራቸው እኛን ይደግፉናል» በማለት ተስፋ ቢያደርጉም የሚጦራቸውን አጥተው ብቻቸውን ናቸው። ስለዚህ የእኛን ድጋፍና ፍቅር ይፈልጋሉ።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥራ ክቡረነት ከሚያስተምሩት ነጥቦች ጥቅቶቹን ጻፍ። በዲቁና አገልግሎት ውስጥ ሥራ ለአገልጋዩም ሆነ ለተገልጋዩ የሚሰጠው ውጤት ምንድነው?
2. የስንፍናና ሥራ ፈትነት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የዲቁና ተገልጋዮችንስ እንዴት ከስንፍናና ሥራ ፈትነት ማዳን እንችላለን?
3. በዲቁና አገልግሎት አገላለጽ የፈውስ አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው? ፈውስ ከዲቁና አገልግሎት ጋር ያለውን ተያያዥነት ግለጽ።
4. በዲቁና አገልግሎት ዕይታ የማማከር አገልግሎት ምን እንዴሆነና እንዴትስ መተግበር እንዳለበት አብራራ።
5. የድቁና አገልግሎት በተለያዩ መንፈሳዊና አካላዊ ጉዳት ወይም በሽታዎች የተጠቁትን ሰዎች እንዴት ማገልገል ይቻላል?
6. የማኅበረ ምዕመናን ዲቁና አገልግሎት ሰዎች በHIV/AIDS እንዳይጠቁ ምን አስተዋጽኦ አለው? ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ሰዎችስ?
7. ባጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ዲቁና አገልግሎት በአከባቢህ በመንፈስ፤ በአከል፤ በኢኮኖሚ፤ በማኅበራዊና በፖለቲካ ጤናማ ኅብረተሰብን ለማፍራት ምን ምን መደረግ እንዳለበት አስተያየትህን ጻፍና ለጓደኞችህ ወይም ለማኅበረ ምዕመናንህ ሐሳብ አቅርብ።

# ክፍል አራት

## 4. የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት በኅብረተሰብ መካከል

ቤተ ክርስቲያን በዓለም የምትገኝ የኅብረተሰብ ክፍል ናት። የኅብረተሰቡ ደስታና ኀዘን፣ ማጣትና ማግኘት፣ ሰላምና ነጻነት...ወዘተ ቤተ ክርስቲያንንም ይመለከታሉ። እርስዋ ራስዋ በእነዚህ ነገሮች ውስጥ ታልፋለች። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰቡ መሐል እንደ ኩሬ ውሃ በተወሰነ ሥፍራ የምትቀመጥ አይደለችም። ይልቁንም እንደ ወንዝ ውኃ እየንተንቀሳቀሰች የኅብረተሰብን ችግር ለመካፈልና መፍትሔ ለማምጣት እግዚአብሔር በዓለም የፈጠራት የእርሱ ወኪል (አምባሳደር) ናት። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን በዚህች ዓለም ሳለች የዚህ ዓይነቱ መስኮታዊ ኃላፊነት ተሰጥቶአታል። በዓለም ካሉት ሌሎች መንፈሳዊና ሰብአዊ ድርጅቶች ይልቅ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መስኮታዊ ስልጣንና ኃላፊነት ከአምላኳ የተቀበለችና ለዓለም ሕዝቦች እኩልነት፤ ነጻነት፣ ፍትሕና ሰላም ለማስፋፋትና ለመገንባት የተመሠረች አካል ናት። ይህንን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊው ዕይታና ትምህርት ምን እንደሚመስል እንመለከታለን።

### 4.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕይታ

የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከጴንጤቆስጤ ዕለት በኋላ በሐዋርያት ትምህርት መሠረት እንደተመሠረተች(የሐዋ.ምዕ.2) የዲቁና አገልግሎተዋን ጀመረች(የሐዋ.6፣1-7)። የጥንት ቤተ ክርስቲያን የዲቁና አገልግሎት(ምዕ.6፣7) የእግዚአብሔር ቃል መስፋፋት፤ የደቀ መዛሙርት በቍጥር መብዛትና ለሃይማኖት የመታዘዝ በሀሪይ ውጤት አስገኘ። በዚህ መሠረት የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናዊት ቤተ ክርስቲያን መሆን ይኖርባታል። በአሁኑ ጊዜ ይህን የሥነ-መለኮት ግንዛቤ ያገኙ የምዕራቡ ክፍለ ዓለም ሉተራን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዲያቆናዊት ቤተ ክርስቲያንን ለማጠናከር ዘርፈ- ብዙ አገልግሎቶችን ያቀፈ የዲቁና መምሪያዎች አዘጋጅተው በከፍተኛ ሁኔታ አገልግሎቱን በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን ክልል ወጣ ብለው የኅብረተሰቡን እስተ ዳደራዊ፣ ኢኮሚያዊና መንፈሳዊ ኑሮ ለማሻሻል ትምህርት ቤቶችንና ሆስፒታሎችን፣ ሌሎችንም ሥራዎች በመሥራትና መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር አስፈላጊውን ግንኙነት በማድረግ ሕዝብን ያገለግላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን



አብያተ ክርስቲያናት ስለ ዲቁና አገልግሎት መረዳትና የሚያስገኘ ውንም ውጤት ለኅብረተሰብ ማስጨበጥ ይገባቸዋል ።

በመሆኑም ስለ ጤና፤ ትምህርት፤ ልማት፤ ፍትህ፤ ሰላም፤ ዕርቅ፤ እኩልነት የእግዚአብሔር ሐሳብና ተግባር ምን እንደሆነ በትክክል ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ማጥናት ይጠቅማል። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በዚህች ዓለም ላይ የእግዚአብሔርን ሐሳብና ባሕርይ እንዴት መግለጥና መተግበር እንዳለባት የሚያሳውቃት ብቸኛ መመሪያ ሆኖ ስለሚያገለግል ነው። በዚህ መሠረት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዲቁና የዓለም ኅብረተሰብን ሰላም፣ ፍትሕና ዕርቅ እንዴት ይመለከታል? ለተግባራዊነቱስ እንዴት ይሠራል? የሚሉትን ጥያቄዎች መሠረት አድርገን እንደሚከተለው ባጭሩ እንመለከታለን።

#### ሀ. ሰላም

ሰላም ለሚለው ቃል ቀጥተኛና ጥሬ ትርጉም ለመስጠት ያስቸግራል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ግለሰብና ኅብረተሰብ እንደየባህሉና እንደየሥረ-መሠረቱ ይረዳዋል። ለምሳሌ:- አይሁዳውያን «ሻሎም» የሚሉትን ቃል እኛ ሰላም እንለዋለን። እንዲህ ሲባል ግን በእነርሱ መረዳት ሙሉ በሙሉ ትርጉሙን እንጠቀምበታለን ማለት ላይሆን ይችላል። «ሻሎም» የሚለው ቃል በእነርሱ መረዳት «የተረጋጋ፣ ጠብና ጦርነት የሌለበት ሁኔታ» ብቻ ሳይሆን «መንፈሳዊና አካላዊ ወይም ሁለንተናዊ ደኅንነት እና ሁለመናዊ ድነት» የሚለውን ጠንካራ መልእክት የያዘ ቃል ነው። እስራኤላውያን ከአሮን ቡራኬ ስለ ሰላም በመንፈሳዊ መልኩ ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ አንድነት መፍጠር ሲሆን በምድራዊ ኑሮአቸው ደግሞ ስለ ግለሰብ አእምሮአዊ፣ መንፈሳዊ፣ አካላዊና ሥጋዊ ማንነት፣ እንዲሁም ስለኅብረተሰብ የርስበርስ መልካም ግንኙነትና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው ጤናማ ኑሮ ጋር ጭምር በማያያዝ ይረዱታል(ዘኍል. 6፣26)።

በአጠቃላይ ሰላም የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር፤ ከርስ በርሳቸው ጋር፤ ከራሳቸው ጋርና ከተፈጥሮ ጋር በስምምነትና በአንድነት በምሉአት አብሮ መኖርን ያመላክታል (ሮሜ. 5፡1፤ቈላ.1፣20፤ኤፌ.ምዕ.2)። ሰላም የንግግር መክፈቻ ቃልም ነው(ዮሐ.20፣19)። እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ሰው በክርስቶስ አምኖ ከኃጢአት ነጽቶ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቅ ነው(ሮሜ.1ኤፌ.2፣14-17)። ሰላም የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፣22)። አማኞች ከሌሎች

ሰዎችና ከራሳቸው ጋር በሰላም እንዲሩ ታዝዘዋል (ሮሜ 12፣18፤1ጴ ጥ3፣11)። በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በኅብረተሰብ መካከል በዲቁና አገልግሎትዋ እውነተኛውን የክርስቶስ ሰላም ለማምጣት በተ ቀናጀና በተደራጀ መልኩ እንዲንቀሳቀሱና በአከባቢያቸው ሰላም ያጡትን ችግረኞች እንዲረዱ የማድረግ ኃላፊነት አለባት።

*ለ. ፍትህ*

ፍትህ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (2ሳሙ.15፣4፤መዝ.82፣:3) በዕብራይስጥ ቋንቋ «ጻደቅ» ወይም «ዮሽር» (ዘዳ.9:5) በሚሉት ቃላት ይገለጻል። እንደ ቃሉ ቀደም ተከተ ል «ጽድቅ» ወይም «የልብ ቅንነት፣ቀጥተኛነት (ቀጥ ያለ ነገር)» የሚለውን ትርጉም ያዘለ ሆኖ በአጠቃላይ በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ትክክለኛና እውነተኛ የሆነ ቅን ፍርድ መስጠት(ማወጅ) ማለት ነው። በትክክለኛ በሆነ ሁኔታ በእኩልነት ነገሮችን በሚዛን መመልከትና ያለ አድልኦ መፍረድ ወይም መቁረጥ ማለት ነው።

እላይ በተሰጠው ትርጉም መሠረት ፍትሕን በምን ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ነው መለማመድና ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር በባሕርይውና በተግባሩ ጻድቅና ቅን አምላክ በመሆኑ ሰው በኃጢአት በወደቀ ጊዜ በሰውና በኃጢአት መከከል ቅን ፍርድን ሰጠ። በመቀጠልም የእስራኤል ሕዝቦች በምድረ በዳ ሲጓዙም ሆነ በከነዓን ምድር በነበሩበት ጊዜ እግዚአብሔር በሁለንተናዊ ኑሮአቸው (በማህበራዊ፤ በኢኮሚያዊ፤ በመንፈሳዊ፤ በፖለቲካዊ በአስተዳደር ... ወዘተ) መስከ ሁሉ ቅን ፍርድ እየሰጠ ሰመራቸው ነበር። የእግዚአብሔር አመራር ፍትሓዊ ነው። እርሱ ጻድቅ በመሆኑ በምንም ነገር የማይደለል ቅን ፈራጅ ነውና። እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው (መዝ.7፣11)። ሰዎች በተለያየ ምክንያት በመካከላቸው (በኢኮኖሚ፣ በሥልጣን፣ በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለምና በሃይማኖት)፣ የመበላለጥ ደረጃ ዎችን ይዘረጋሉ። ከዚህም የተነሣ በኅብረተሰብ መካከል ኢ-ፍትሓዊ ግንኙነቶች ይከሰታሉ።

እግዚአብሔር ትክክለኛ ፍትሕ በዓለም ላይ እንዲሰፍን ይፈልጋል (አሞጽ 4፣1-2፣5፣10-24፣8፣4-10)። ቤተ ክርስቲያን ሕያው የክርስቶስ አካልና አምባሳደር እንደመሆንዋ መጠን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በኩል በዓለም ላይ ፍትሕ እንዲኖር ይፈልጋል። ይህም የሚሆነው አማኞች የእግዚአብሔርን እውነተኛ



ባህርይ በቃልም ሆነ በተግባር መግለጥ ሲችሉ ነው። ይህ እንዴት ይቻላል? ምእመናን በሙሉ የዲቁና አገልግሎትን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በተቀናጀና በተደራጀ ሁኔታ መተግበር የቻሉ እንደሆነ ብቻ ነው።

በዲቁና አገልግሎት አማካይነት እንዴት የፍትሕ አገልግሎት ይሰጣል? ብሎ ማሰብ ይቻላል። በመሠረቱ የዲቁና አገልግሎት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ተግባር እና ችግረኞችን የመርዳት አገልግሎት በመሆኑ በማንኛውም የኅብረተሰብ ግንኙነቶች ውስጥ መስሎቻቸውን ሰዎችን በማይጎዳ ሁኔታ አብረው እንዲኖሩና እንዲሠሩ የማበ ረታታትና ለተጎዳው አካል ደግሞ ቅን ፍርድ መፈለግን እንዲሁም መሟገትን (Advocacy) ጭምር የሚያጠቃልል ነው። የዚህ ዓይነቱን የዲቁና አገልግሎት «የነቢይነት ዲቁና አገልግሎት» (Prophetic Diakonia) ብለን እንጠራዋለን።

የነቢይነት ዲቁና በቃል፤ በጽሑፍ እና በአካል ቆሞ በሕግ ፊት ለተጎዱ ወገኖች ድምፅን ማሰማት ብቻ ላይሆን እያንዳንዱ ክርስቲያን በዕለታዊ የኑሮው እንቅስቃሴ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚጎዱትን ሰዎች በብቁ ተሳትፎ በክርስቶስ ፍቅር በተግባር ማገልገል ማለት ነው። ለምሳሌ፦ በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ በቂ ተሳትፎ የሌላቸውን፣ የተረሱትን፣ ድሆችን፣ ባልቴቶችን፣ ወላጅ-አልባ ሕፃናትንና አረጋውያንን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ማገልገል ነው።

እንዲሁም አንዳንዶች ከፖለቲካ አመለካከት የተነሣ ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሲታሰሩ፤ ሲሞቱና ሲቸገሩ ይታይ ይሆናል። በማንኛ ውም አቅጣጫ ስለሚጎዱ ሰዎች ፍትሕ እንዲረጋገጥላቸው ከመንግሥትም ሆነ ከሚመለከተው አካል ጋር መልካም ግንኙነትን በመፍጠር መፍትሔን ማምጣት ያስፈልጋል። በሌላ መልኩ ሲታይ የድሆች ጉልበት ያለ ልክ በሀብታሞች ሲበዘበዝ ይችላል። ከሥራ ጋር የማይመጣጠን ደመወዝ፣ የሥነ-ልቦናዊ ተጽዕኖ ማሳደር፣ የኑሮ አለመረጋጋት (የገበያ አለመጣጣም)፣ የድሆች በነፃ ገበያ ትርፋማ መሆን አለመቻልና የሀብታሞችን ጥያቄና ፍላጎት ብቻ መጠበቅ፣ የድሆች ንጹህ አየርና አከባቢን መምረጥ አለመቻል፤ የገንዘብ አቅም ማነስ የመሳሰሉ ኢ-ፍትሐዊ አሠራሮች ናቸው። ከገደብ-የለሽ የኢኮኖሚ ነጻነት ግብይት እምባገነናዊነት ሥርዓትን በመስፈን ድሆችን የሚጎዳ ከሆነ መመልከት ጠቃሚ ነው። በመሆኑም ክርስቲያኖች በሀገራቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድርግ ማንኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል በማይጎዳ

ሁኔታ ፍትሕ በሰፈነበት ሁኔታ መልካም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋቸዋል።

ስለዚህም ነው የዲቁና አገልግሎት ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ የመሆንና ተስፋ ለሌላቸው ተስፋ የመሆን አገልግሎት ነው የምንለው። ይህ ደግሞ በትክክል ሥራ ላይ መዋል የሚችለው እያንዳንዱ ክርስቲያን በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በዕለታዊ ኑሮው ውስጥ ለተጎዱ ሰዎች መሟገትና ጠበቃ መሆን ሲችል ነው። ፍትሕ እንዳይጓደል መጸለይ ብቻ ሳይሆን በተግባር እንድንገልጠው እግዚአብሔር ይፈልጋል። ፍትሕና ጽድቅ የሞላባት «መንግሥትህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» ስንል ጸሎታችንና ተግባራችን የተጣጣመ መሆን ያስፈልጋል። ተግባራዊ ኑሮ ከቃል የበለጠ ስብከት ነው። ይህ ካልሆነ ግን የተግባር ሳይሆን የቃልና የልፍለፋ ሰዎች ብቻ ሆነን እንቀራለን። ይህ ደግሞ ክርስትና ሳይሆን በክርስትና ስም የማምለጫ ኑሮን መኖር ማለት ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን የጽድቅ መንግሥት ባሕርይን በቃል ለዓለም ሕዝቦች መግለጥ ብቻ ሳይሆን እንዲለማመዱትም ማድረግ መለኮታዊ ኃላፊነታቸው ነው። ከዚህ የተነሣ ነው በማንኛውም ኅብረተሰብ ዘንድ የነቢይነት ዲቁና ዓለም አቀፋዊና የጊዜው አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የመንፈሳዊ፣ የባሕሳዊና የሥነ-ልቦናዊ ኢ-ፍትሐዊነትንና ጭቆናን የሚያወግዝ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘርፍ ነው የምንለው።

### ሐ. ዕርቅ

ዕርቅ የሚለው ፅንሰ-ሐሳብ በተለያዩ ግለሰቦችና ኅብረተሰቦች ዘንድ እንደየሁኔታው በተለያየ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። በመሠረቱ ዕርቅ በሁለት ወገኖች መካከል መልካም ግንኙነትን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ከመካከላቸው ጠላትነትን የማስወገድ ተግባር ሂደትም ነው። በሌላ አባባል ተለያይተው ያሉትን ሁለት ወገኖች የሚያቀራርብ መልካም ድልድይ መገንባት ማለት ነው። ሰው በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ በጠላትነት ሲኖር ሳለ (ኤፌ.2፣3) ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው ሁለቱን ወገን አስታረቀ (2ጢሞ.2፣5)። በሰዎች መካከል ዕርቅን አመጣ (ኤፌ.2:12-14). «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር... በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ (2ኛ ቆሮ.5፣19)።



እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ለዕርቅ፣ ለሰላም፣ ለፍትሕ፣ ለኅብረተሰብ አኩልነትና ነጻነት የሚጠቅም መልእክት ከእግዚአብሔር ተቀብላለች። ይህንንም መልእክት ለማስተላለፍና ድምፅዋንም ከፍ አድርጋ ለማሰማት በእግዚአብሔር ተጠርታለች። ለዚህም መመሪያና ሕይወትዋ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መጠቀም ያስፈልጋታል። «በኃይልህ ጩኽ አትቈጥብ ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ ለሕዝቤም መተላለፋቸውን ንገር» (ኢሳ.58:1)። በዘመናት ሁሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ግፍንና ኃጢአትን አይተው በዝምታ አልፈው አያውቁም። ዛሬም ያለችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ዕርቅና ሰላም ሲጎድል አይታ ማለፍ የለባትም። ለመፍትሔ መጮህ ያስፈልጋታል።

እያንዳንዳችንም ክርስቶስ ያፈረሰውን የጥል ግድግዳ መልሰን መገንባት አይገባንም (ኤፌ 2:19)። ክርስቶስ ያፈረሰውን ነገር አፍርሰን እርሱ በደሙ የገነባውን ሰላም ወዳዶች ሁነን መገንባትና ለዚህ የሚያስፈልግ ሁኔታዎችን እያመቻችን መሥራት የእኛ የክርስቲያኖች ኃላፊነት ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል፣ በሰዎችና በሰዎች መካከል፤ በሰዎችና በተፈጥሮ መካከል በግለሰብ ደረጃም ሰዎች ሰላም እንዲኖራቸው የዕርቅ ሥራ ትሠራለች።

እንዴት? ለሚለው ጥያቄ በቀላሉ መልስ ከመስጠታችን በፊት ከቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ልምድ ሐሳብ መስጠት መልካም ነው። ባሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ካሉዋት የአገልግሎት ዘርፎች መካከል ዲቁና አንዱ ነው። ዲቁና ደግሞ የሁሉም ምእመናን ኃላፊነት በመሆኑ በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ እንደ አንድ ክርስቲያን የዕርቅ አገልግሎት መወጣት ይኖርበታል። ከክርስቲያን የሚጠበቀው ኃላፊነት የማስታረቅ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን፣ ለሰዎች ሁሉ ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ የመስጠት፣ የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታንም ይጨምራል። ጌታ ኢየሱስ «በእኔ ያመነ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፣ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» (ዮሐ.14:12) ያለውን ቃል በትክክል መገንዘብ እያንዳንዱ ምእመን የዕርቅን ሥራ እየሠራ በኅብረተሰብ ውስጥ በተለያየ ምክንያት የሚከሰቱትን ግጭቶች እንዲያስወግድና ሰላምን እንዲያሰፍን ለኅብረተሰቡም ሁለንተናዊ ለውጥ እንዲያመጣ መሥራት ይገባል።

### 4.2 ሰብአዊ መብቶች

ሰብአዊ መብቶች ስንል ምን ማለታችን ነው? እግዚአብሔር በዘፍ.1፣27 ሰውን በመልኩና በምሳሌው ወንድና ሴት አድርጎ

እንደፈጠረ የራሱን ክብርና ሞገስ እንዳካፈለውና ፣ በፍጥረት ሁሉ ላይ የበላይነትና የማስተዳደር ሥልጣን እንደሰጠው እናያለን:: ሰው ሰብአዊ መብቱን ከማንም ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር ነው ያገኘው አንዱና ዋነኛው መብት የሰው በሕይወት መኖር ነው:: አንድ ሰው በእግዚአብሔር አመነ አላመነ ሕይወት ያገኘው ከሰው ወይም ከሌላ አካል ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ሰውን ከአፈር ካበጀው በኋላ የራሱን እስትንፋስ እፍ አለበት:: እግዚአብሔር ይህን በማድረጉ ለሰው ልጅ የራሱን ሕይወት እንዳካፈለው ነው የምናየው:: ይህም የሰው ሕይወት ምንኛ ውድ ዋጋ ያለው እንደሆነ ያሳያል:: እግዚአብሔር የሰጠውን ውድ ስጦታ ማንም ከማንም ሲነጥቅ አይገባም::

ሰው ከእግዚአብሔር ያገኘውን ሰብአዊ መብት፣ እኩልነትና ክብር ሌላው ኢ-ሰብዊ በሆነ ድርጊት ሲነጥቀውና ያለ አግባብ ሲጠቀምበት ሲፈልግ እግዚአብሔር ዝም አይልም:: «ስለ ድሆች መከራ ስለ ችግረኞች ጩኸት እግዚአብሔር አሁን እነሣለሁ ይላል» (መዝ.12:5):: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስለ ሰዎች እኩልነት፣ ነጻነትና ፍትህ እግዚአብሔር የተለያዩ ነቢያት እያስነሣ እንዲናገሩ ያደርግ እደነበረ ከቃሉ እንመለከታለን::

«በሰማርያ ተራራ የምትኑ ድሆችንም የምትበድሉ ችገረኞችንም የምታስጨንቁ ጌቶቻቸውንም አምጡ እንጠጣ የምትሉ... ጌታ እግዚአብሔር እናንተን በሰልፍ ዕቃ ቅሬታችሁንም በመቃጥን የሚወስዱበት ቀን እነሆ፣ በላያችሁ ይመጣል ብሎ በቅዱስነቱ ምሎአል:: ጻድቁን የምታስጨንቁ ጉቦንም የምትቀበሉ በበሩም አደባባይ የችግረኛውን ፍርድ የምታጣምሙ፣ ስለዚህ ጌታ የሠራዊት አምላክ እንዲህ ይላል:- በአደባባዩ ሁሉ ላይ ዋይታ ይሆናል በየመንገዱ ሁሉ ላይ ወዮ፣ ወዮ ይባላል፣ በመካከልህ አልፋለሁና በወይኑ ቦታ ሁሉ ልቅሶ ይሆናል ይላል እግዚአብሔር (አሞ.4:1፣2፣ 5፣10-24) እንዲሁም ነቢዩ ሚክያስ «ሰው ሆይ፣ መልካሙን ነግሮሃል እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?» (ሚክ. 6፣8) በተጨማሪም አሞጽ 8፣4--10 ያንብቡ::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለፍትሕ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶ እናገኛለን:: በተለይ በመዝሙር መጻሕፍትና በትንቢተ ኢሳያስ ስለ ፍትሕ በስፋት ተጽፎአል:: መጽሐፍ ቅዱስ የፍትሕ መጓደልን ከኃጢአትና ከእግዚአብሔር ቍጣ ጋር ያገናኘዋል:: እንዲሁም ከጽድቅና ከድነት



ጋር ተያያዥነት እንዳለው ይገልጻል:: እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች ሲገልጥ «... እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ ከእኔም በቀር ማንም የለም» ካለ በኋላ ከእርሱ ጻድቅና ከእውነት ሥራ የራቁና ፍትሕን በማጉደል በእልኸኝነት ጸንተው የቆሙ ሰዎች እንዳሉ ይናገራል (ኢሳ. 45፣21፤ 46፣12-13፤ 51፣5፤ መዝ. 36፣6-7፤ 40፣11፤ 71፣15፤ 98፣2፤ 103፣17):: ስለሆነም ለሰዎች እውነተኛ ፍትሕና ጽድቅ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር የፍትሕና የጽድቅ፣ የምሕረትና የእውነት አምላክ ነው:: በሰዎች ኑሮ እውነተኛ ፍትህና ሰላም እንዲኖር ይፈልጋል:: እርሱ ኃጢአትን (ክፉ ሥራን) እጅግ ይቃወማል:: በሰዎች መካከል የሚደረገውንም ግፍ ከልቡ ይጠላል::

እንዲሁም የፍትሕና የጽድቅ ጉዳይ ከመሲሁ ነጻ አውጪነት ጋር እንደተጠቀሰ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ኢሳ. 9፣6፤ ኤር. 23:6፤ ማር. 1፣15፤ ሮሜ 1፣15-17፤ 3፣5፤ 21-22፤ 25-26፤ 10፣3):: በተለይ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከሰዎች የነፍስ ድነትና በጊዜው ከነበረው የአስተዳደር ጭቆና ነጻ ስለመውጣት ይናገራሉ:: ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጽድቅና ሰላም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰፊ ትምህርት አስተምሮአል (ማቴ.5፣1-13):: ነገር ግን ከማስተማር አልፎ በዘመኑ የነበሩትን አለቆችና ባለሥልጣናት ያለፍርሃት ገሥጾአቸዋል (ማቴ.23፣4-31)::

ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችም በዘመናቸው ፍትሕና ሰላም ሲጓደል በዝምታ አልፈው አያውቁም ነበር:: ንጉሥ ዳዊት ኦርዮንን በግፍ ባስገደለው ጊዜ ናታን... ይህን ግፍ የሠራኸው አንተ ስለሆንክ ሞት ይገባሃል በማለት ደፍሮ የእግዚአብሔርን መልእክት አስተ ላልፎአል (2ኛ ሳሙ.12፣1-7)::

ንጉሥ አክዓብ ናቡቴን ገድሎ መሬቱን በቀማ ጊዜ ነቢዩ ኤ ልያስ «ቤትህን ፈጽሞ አጠርጋለሁ፣ ሚስትህን ኤልዛቤልንም በናቡቴ እርሻ ውስጥ ውሾች ይበሉአታል» የሚል ጠንካራ መልእክት ተናግሮአል (1ነገ. 20፣17--22)::

ንጉሥ ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት በዓመፅ አግብቶ ስለነበ ረ መጥምቁ ዮሐንስ በግልጽ ተቃውሞ አደረገ:: እስከ ሞትም ተፈ ረደበት (ማቴ. 14፣1-12):: እነዚህ አገልጋዮች ለምሳሌ ያህል የተጠቀሱ ናቸው እንጂ አብዛኛው የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ ድሃና ደካማ ወገን ላይ ማንኛውም የግፍ ሥራ ባለሥልጣን ሲፈጽም ዝም ብሎ አያውቁም::

ክርስትና ጀርባችንን ለዓለም ለጥተን የምንሸሽበት ወይም ዓለማዊነትን የእኛ የምናደርግበት ሕይወት አይደለም። ክርስትናችን ከገሃዱ ዓለም አስወጥቶን ሐሳባውያን ብቻ አያደርገንም። በዙሪያችን ከሚፈጸሙ ኢ-ፍትሐዊ ነገሮችም ጋር እንድንተባበር አይጋብዘንም። ክርስትና አብ ልጁን ወደ ዓለም እንደላከውና ለዎችን ከነፍስና ከመንፈስ እስራት እንደፈታቸው ሁሉ እኛም በኢየሱስ ተልከን በዓለም ውስጥ ለሚገኙ ኅብረተሰቦች የነጻነትና የፍትሕ፣ የሰላምና የፍቅር መልእክት የምናስተላልፍበት ሕይወት ነው።

ያለፉት ነቢያት ስለ እግዚአብሔር ፍርድ፣ ጽድቅ፣ እውነት፣ ነጻነትና ፍትሕ በነገሥታትና በገዥዎች ፊት ያለፍርሃት እንደተናገሩ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ የእግዚአብሔርን መልእክት ማስተላፍ ይጠበቅባታል። እንዳለፈው ዘመን ሁሉ ዛሬም የመናገር መብት የሌላቸው፣ ከሰዎች እኩል ተፈጥረው በበታችነት የተፈረጁ፣ ለሚና ተቀባይ አጥተው በአለቆችና በባለሥልጣናት ተረግጠው የሚኖሩ አሉ። እንደነዚህ ላሉት ማን የችግራቸው ተካፋይ ይሆን? ማንስ ይሟገትላቸው? የችግረኛው ሰው ብሶት ግድ የሚለው የፍቅር ሰው ማን ነው? ቤተ ክርስቲያን ጥሪዋና አገልግሎትዋ መሆኑን ተረድታ ድምፅ ለሌላቸው ድምፅዋን ለማሰማት ተስፋ ለሌላቸው ተስፋ ለመሆን አባሎችዋን ማስተማርና ማዘጋጀት ያስፈልጋታል። የዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ለችግረኞች ጠበቃ ሆኖ መቆምን ያመለክታል። በየትኛውም የዓለም ክፍልና ዘመን ሙሉ በሙሉ ፍትሕና ሰላም ይኖራል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። ለዓለም ፍትሕና ሰላም የሚመጣው በጦር መሣሪያ ሳይሆን እግዚአብሔርን በመፍራት፣ እውነተኛና ያልተዛባ ፍርድ፣ የዜጎች እኩልነትና ነጻነት ሲገኝ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር በቃሉ የሚያስጠነቅቀንን መልእክት ለማግኘት የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እናንብብ (ኤር. 22፣3-4፤ ኢሳ. 58፣3-8፤ 59፣6-8)። ቤተ ክርስቲያን ሰላምን፣ ጽድቅን፣ ነጻነትን፣ እኩልነትንና ፍትሕን የምትፈልግና የምትመኝ ብቻ መሆን የለባትም። ከምኞት አልፋ እነዚህ ሁሉ በኅብረተሰቡ መሐል እንዲሰፍኑ የራሰዋን አስተዋጽኦ በተጨባጭ ሁኔታ መተግበር ይጠበቅባታል።

የቤተ ክርስቲያን ዲቁና አገልግሎት ለችግረኞች፣ በእግዚአብሔር መልክ እኩል ተፈጥረው እኩልነትን ላጡ፣ መብት እያላቸው ሰብአዊ መብትና የፖለቲካ ነጻነት ላጡ እንድንቆም የሚያነሣሣን አገልግሎት ነው።



በእግዚአብሔር ቃል የሚያምን ክርስቲያን ሁሉ የቃሉን መመሪያ መከተልና ተግባራዊ ማድረግ ይገባዋል። የእግዚአብሔር ቃል «ለድሆችና ለድሀ አደጎች ፍረዱ፣ ለችግረኛውና ለምስኪኑ ጽድቅ አድርጉ፣ ብቸኛውንና ችግረኛውን አድኑ፤ ከኃጢአተኞችም እጅ አስጥሉአቸው (መዝ. 82፣3-4) ወደ ሞት የሚነዱትን ታደግ፣ ሲታረዱ የተወሰኑትንም አድን። እነሆ ይህን አላውቀውም ብትል ልቦችን የሚመረምር እርሱ አያስተውልምን? ነፍስህንም የሚመለከት እርሱ አያውቅምን? ለሰውስ ሁሉ እንደ ሥራው አይመልስለትምን?» (ምሳ.24፤11-12) በማለት ያስጠነቅቃል።

ፍትሕና ሰላም ተሟጦ ጥቂት ሰላም ባለበት ዓለም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የችግረኞች አፍና እጅ አድርጎ ካስቀመጣት በሰዎች መካከል ፍትሕና ሰላም ለምን ይጎድላል? ቢባል መልሱ ከእርስ በርስ መተሳሰብና ፍቅር መጉደል የተነሣ ነው። በዓለማችን ያሉ ሕጎችና ሥርዓቶች ከኅብረተሰብ ወደ ኅብረተሰብ ሊለያዩ ይችላሉ። ለምሳሌ፡- ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር፣ ንጉሣዊ አገዛዝና በሕላዊ ሥርዓት (ደንብ) ሊኖር ይችላል። ከእነዚህ ሕጎችና ሥርዓቶች ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጣት ዘላለማዊና የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል አላት። ይህም የፍቅር፣ የሰላም፣ የእኩልነትና የፍትሕ ሕግ ነው።

ዛሬም ለእግዚአብሔር ሕይወታቸውን የሰጡ ለባልንጀራቸው እውነተኛውን ፍትሕና ሰላም የሚፈልጉ ክርስቲያን ወገኖች በየአካባቢያችን ይኖራሉ። ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት እኅት ለጉዳይ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ ቀበሌዎች ወደ አንዱ ስትሄድ አንድ ምስኪን ድሀ ሰው ለመብቱ ወደ ቀበሌ ጽሕፈት ቤት ሄዶ የደረሰበትን ችግር ለቀበሌው ሹም ሲናገር ትሰማ ነበር። የቀበሌው ሹም ፈጽሞ አላናግረው ብሎ ሲያመናጭቀው አይታ ወደሚመለከተው ሁሉ በመሄድ ጉዳዩን ማስፈጸም ችላለች። ሌሎቻችንም ብንሆን የሰዎችን ችግር እንደራሳችን ቸግር ብንቈጥር፣ ስለእነርሱ ድምፃችንን ማሰማትና መሟገት እንችላለን።

በመሆኑም ሰብአዊ መብቶች እንዲጠበቁና የተረጋጋ እንዲሁም ዘላቂና አስተማማኝ ኑሮ ያለው ኅብረተሰብ እንዲፈጠር ለማድረግ ቤተ ክርስቲያን በተደራጀ የዲቁና አገልግሎት ሥራ የሕዝቦችንና የመንግሥትን ሥልጣንና ኃላፊነት አጠቃቀም በየጊዜው እየተከታተለች ማገልገል ይኖርባታል። ይህም ማለት እንደ እግዚአብሔር ቃል

በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ፣ የመንፈሳዊና የባሕላዊ እሴቶች ጉዳዮች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ መሳተፍ የሁሉም ምእመናን ኃላፊነት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ይህን በሚመለከት የቤተ ክርስቲያን ዲቁና አገልግሎትን በሚከተሉት መንገዶች መተግበር ይቻላል::

- ስለ ሰላም ግንባታና ለሌሎች መሟገትን በሚመለከት ሕዝብን ማደፋፈርና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤን ማለጨበጥ::

- በብሔራዊ የሕገ መንግሥት ሥራና ማሻሻያ ጉዳዮች ላይ ሐሳብ በመስጠት መሳተፍ::

- ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ ሕጎችና ደንቦች በትክክል መተ ግበራቸውን እንዲሁም ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደ ረጃም ሆነ በሀገራችን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ብዙ ጥሪትና ሀብት እየተከፈለበት ያለው የጾታና የሕፃናት መንከባከብ ጉዳዮች ውስጥ ብቁ ተሳትፎ ማሳየት ነው:: ይህን በሚመለከት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያን የዲቁና ኃላፊነት ይኖራታል:: ለዎች በዕለታዊ ኑሮአቸውም ሆነ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ (በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በመልክዓ-ምድራዊ አሠፋፈር፣ በፖለቲክ፣ በኢኮኖሚና በእውቀት እድገት ደረጃ) ያለ ምንም ልዩነት አብሮ የመኖርና የመሥራት ልምድና ባሕል እንዲያዳብሩ ግንዘቤን መስጠትና ማደፋፈር ይገባል:: ስለዚህ ልዩነትን በአንድነት አንድነትንም በልዩነት ጠብቆ ለዎች በፍቅርና በመቻቻል እንዲኖሩ ማድረግ የእያንዳንዱ ምእመናን ኃላፊነት ነው::

- ስለ ዲቁና አገልግሎት የመነቃቃት ትምህርትና ስልጠና መስጠት::

- ስለ ሁለንተናዊ እድገትና ራስ-መቻል ሂዴት እቅድ ማዘጋጀትና መተግበር ::

- በማንኛውም ቦታና ጊዜ በማንኛውም አካል ሰብአዊ መብቶች ሲጣሉ በቤተ ክርስቲያን ደረጃም ሆነ እንደ አንድ ግለሰብ ምእመናን ጣልቃ መግባት ይጠበቅባቸዋል::

- ቤተ ክርስቲያን ለብአዊ መብቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች



ላይ በተጠናከረ መልኩ በየደረጃው ጥናቶችን፣ ትንተናን፣ ምርምርን፣ ክትትልን፣ ግምገማን፣ የኅትመት፣ የምክር አገልግሎትና የምክክር ሥራዎችን ማካሄድ ይጠበቅባታል::

በአጠቃላይ መልኩ የቤተ ክርስቲያን ዲቁና አገልግሎት ራዕይውን፣ ዓላማውንና ግቦቹን መተግበር ያስፈልጋል:: በራላችን ሀብት እኛው ሠርተን የምድራችን አሬንጓዴ እንዲያብብና ለሌሎች የሚተርፍ ፍሬ እንዲያፈራ የሚናደርግ እኛው ስለሆንን ምዕመናን ዲቁናን በትክክል መረዳት ያስፈልጋቸዋል:: በሌላ መልኩ ዲቁና የእሁኑን ኅብረተሰብ ብቻ በማገልገል ዓላማ ላይ ያተኮረ ሥራ ሳይሆን በቀጣይነት ለሚመጣው ትውልድ መሥራትን ያጠቃልላል:: ስለዚህ ዲቁና ሕይወትን የሚለወጥ የለውጥ ሂደት አገልግሎት (Life Changing Ministry=> Transformational Ministry)ነው:: በዲቁና አገልግሎት አገልጋዩም ሆነ ተገልጋዩ ለለውጥ የሚራመዱ አካሎች ናቸው:: ዲያቆናት የተቸገሩትን ለመርዳት እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ይዘው እንደ አንድ የእግዚአብሔር ነቢይ ስለ ድነት እያስተማሩ፣ ኃጢአትን ኃጢአት ነው እያሉ፣ ፍትሕን እየገለጡና ቅን ፍርድ እየለጡ ወደ አገልግሎት መስክ የወጡ አገልጋዮች ናቸው:: በተቃራኒው ደግሞ ከችግረኞች ጎን ቆመው ስለ እነርሱ የሚጮኹ ተሟጋቾች እንደሆኑም እንመለከታለን:: ስለዚህ ምዕመናን የለውጥ ነቢያት ሆነው ለለውጥ መኖርና ማገልገል እንደሚገባቸው መገንዘብ ያስፈልጋል:: በተመሳሳይ መልኩ የዲቁና አገልግሎት በተለይ በእሁኑ ጊዜ በዓለም ዓቀፍም ሆነ በአገራችን ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ያለው ሥራ ስለ ጾታና የሕፃናት መብቶችንም የሚያጠቃልል አገልግሎት ነው::

### 4.3 የጾታና የሕፃናት መብቶች

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለዎችን በጾታ (ወንድና ሴት)፣ በዕ ድሜ (ሕፃን፣ ወጣት፣ ጎልማሳና አረጋዊ)፣ በኢኮኖሚ (ድሃ ሀብታም)፣ በማኅበራዊ መዋቅር (የተሻለና ያልተሻለ፣ ጨዋና የተረሳ)፣ በኃይማኖት (ያመነና የላመነ) እንዲሁም በጤና (ጤናማና በሽተኛ) ብላ አትለይም:: በአንዳንድ ባሕሎችና የሃይማኖት ክፍሎች የጾታ ልዩነት ሲደረግ ይታያል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ስውን ለው ብሎ የጠራው ወንድና ሴት አድርጎ ሳለ ነው:: ወንድ ያለሴት ሴትም ያለወንድ የሰው ዘር ሆነው ሊኖሩ አይችሉም:: ዓለምን ሞልቶ የተረፈው የለው ዘር ዘር በሙሉ ከሁለቱ ጾታዎች የተገኘ ሰብአዊ ፍጡር ነው:: የለው ዘርም

በምድር ሲበዛ የቻሰው በሁለቱ ጾታዎች መካከል በተፈጠረው እውነተኛ የፍቅር ግንኙነት ነው። ሰዎች ከመጀመሪያው ወንድና ሴት ሆነው ሲፈጠሩ ከጾታ ልዩነት የተነሣ የመበላለጥ ስሜት አልነበ ረም። ነገር ግን ሰው በኃጢአት በመውደቁ በወንድና በሴት መካከል መለያየት ሲፈጥር እንመለከታለን። ከዚህም የተነሣ የጾታ ልዩነት በመፈጠሩ ሴቶችና ሕፃናት በኅብረተሰቡ ዘንድ በቂ ተቀባይነትና ቦታ የላቸውም። ስለዚህም ካሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ሴቶችና ሕፃናት የተረሱ ሆነው ይታያሉ። ይህ አመለካከትና እምነት ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። .«አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና»(ገላ. 3፣28)። በተመሳሳይ መልኩ « ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሉአቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና» (ማር.10፣14)። «እናንተም አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቈጡአቸው» (ኤፌ.5፣4)።

አላይ ከተጠቀሱት ክፍሎች የምንማረው ሕፃናትን ተንከባክበን ማሳደግንና በሕይወት የመኖር መብታቸውን መጠበቅን ነው። ሕፃናት በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በኢ-ፍትሐዊ ድርጊቶች በአካል፣ በመንፈስና በሥነ-አእምሮ ኑሮአቸው እንዳይጎዱ በጥንቃቄ በእግዚአብሔር ቃል እንድናሳድጋቸው ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቶናል። ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱት እኩል መብት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። በተለያዩ ምክንያቶች የሚያስጠጋቸውን ወገን አጥተው በዘመናችን በጎዳና የሚተዳደሩ ሕፃናትን ሁሉ ልክ በወላጅ ዘንድ እንደሚኖሩ ሕፃናት ልናያቸው ይገባል ። ብዙውን ጊዜ ለጎዳና ተዳዳሪ ሕጻናት ያለን አመለከከት የተሳሳተ በመሆኑ ልጆቻችንን ለመገሠጽ ስንል የጎዳና ተዳዳሪ ልጅን ምሳሌ ተጠቅመን መምከር እንወዳለን። ይህ አስተሳሰብ እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆነና በሕፃናት መካከል ልዩነት የሚፈጥር አስተሳሰብ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል። ስለዚህ የጾታም ሆነ የዕድሜ ልዩነት ሲጠፋ ማኅበራዊ መብት ይከበራል።

በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚደረጉ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥትና ከኅብረተሰብ ጎን ሆና በትምህርትዋ ማውገዝና የጾታ ልዩነትን ማስወገድ ሥራዋ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባታል። ሴቶችን በሚመለከት በአገራችን በሕብረተሰቡ ዘንድ ያለው የተዛባ የጾታ ግንዛቤ በርካታ የኃይል ተግባራት በሴቶች ላይ እንዲፈጸሙ ምክንያት ሆኖአል። በመሆኑም በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የኃይል ተግባራት እንዲወገዱ ሕብረተሰቡና



ቤተ ክርስቲያን የተዛባው የጾታ ልዩነት ለመለወጥ አማራጭ የሌለው ዘላቂ መፍትሔ ነው። የኃይል ተግባራት የምንላቸው የሚከተሉትንና ሌሎችንም ነው።

- ማንኛውንም የጾታ ጥያቄ መሠረት በማድረግ በማሕበራዊም ሆነ በግል ሕይወት ውስጥ በሴቶች ላይ አካላዊ፣ ወሲባዊና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት ወይም ሥቃይ ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል፣ እነዚህንም ተግባሮች ለመፈጸም የሚደረጉ ዛቻዎችን ወይም ያለአግባብ ነጻነት መግፈፍን የሚያጠቃልል የኃይል ተ ግባር ናቸው።
- ሴቶችን አስገድዶ መድፈር፣ ለወሲባዊ ድርጊት ማጋለጥ፣ በሥራ ቦታ፣ በትምህርት ቤትና በሌሎች ተቋማት ለወሲባዊ ጥያቄዎች ሰለባ መሆናቸው፤ መጥለፍ፣ ለሴት አዳሪነት መዳ ረግ፣ የዝሙት ተግባር መሥራት፣ የሌሎች መጠቀሚያ መሆንና የመሳሰሉት በሙሉ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ በደል የሚያደርሱ የኃይል ተግባራት ናቸው። እነዚህ ኢ-ፍትሐዊና እኩይ ተግባራት በተጠቂ ግለሰቦች ላይ የሚያደርሱት የደኅንነት፣ የሞራል ቀውስና የጤንነት ችግር (የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት) ብቻ ሳይሆን አንዲት ሀገር በፖለቲካ፤ በማኅራዊና በኢኮኖሚ ቀውስ ማጥ ውስጥ እንድትሠቃይ የሚጋብዝና ለድህነት ማስፋፋት ዋነኛው መንገድ ይሆናል።

የኃይል ተግባራትን መፈጸም ብቻ ሳይሆን ሲፈጸሙ አይቶ ዝም ማለት ከሰብአዊነትና ከመንፈሳዊነት የራቀ ሕይወት ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ቤተ ክርስቲያን የተቃውሞ ድምፅዋን ማሰማት አለባት። ከዚህም አልፋ ሴቶች ከወንዶች እኩል ክብር፣ የትምህርት ዕድል፣ የሥራና የአገልግሎት ድርሻ እንዲሁም በኢኮኖሚ እኩል የማደግ ዕድል እንዲራቸው ማበረታታትና ማደፋፈር ይጠበቅባታል። ስለዚህ የሁሉም ሰዎች እኩልነታቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ መኖር እንዲችሉ አስፈላጊውን የዲቁና አገልግሎት መስጠት ተገቢ ነው።

የዲቁና አገልግሎት አንዱ ክፍል ግፍን፣ አድልዎን፣ የጾታና የዕድሜ ልዩነትን፤ ዘረኝነትን፣ ጭቆናና መድልዎን መቃወም፣ በምትኩ ሁሉም ኅብረተሰብ በፍቅርና በአንድነት በሰላም የሚኖርበትን መንገድ መፈለግ ነው። ለዚህም ተግባራዊነት ቤተ ክርስቲያን የዲቁና አገልግሎትን ማደራጀትና ማቀናጀት ይጠበቅባታል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዓለም ሕዝብ ኃጢአት ነፍሱን ሊሰጥ የመጣ ቢሆንም ክሶች ይቀርቡበት የነበረው የበዎችን ክፉ ሥራ አ ያ ጋ ሰ ጠ በመቃወሙ እንደነበረ እንመለከታለን። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በሴቶችም ሆነ በሕፃናት ላይ የሚደረጉትን ኢ-ፍትሐዊ ድርጊቶች በዝምታ ሳያልፍ ለእግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ የማይመቹትን የባሕል ስንሰለቶች ሁሉ በሥልጣን እየበጣጠሰ የተጎዱትንና የተጨቆኑትን ወገኖች ሁሉ በፍጹም ፍቅር ያገለገለ ዲያቆን ነው። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የሰውጥ ወኪል(ሐዋሪያ) ሆና በዲቁና አገልግሎትዋ በማንኛ ውም ሁኔታ ውስጥ የኢየሱስን አገልግሎት ምሳሌ መከተል ያስፈልጋታል።

## 4.3 ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ጉዳዮች መሳተፍ አለባትን?

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ለዓለም ሕዝብ የምታስተላልፍ የኅብረተሰብ ክፍልና መንፈሳዊ ተቋም ናት። መንግሥት ደግሞ ኅብረተሰብን ለማስተዳደር ከኅብረተሰብ የተሾመ አንዱ አካል እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል። እነዚህ ሁለቱ ክፍሎች የሚያወጡአቸው ደንቦችና ፖሊሲዎች የኅብረተሰቡን ደኅንነትና ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታና የሀገሪቱን ሁለንተናዊ እድገት በሚያበ ረታታ መልኩ መቅረጽ አለባቸው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት (ኢፌዲሪ) አንቀጽ.11(1-3) መሠረት «መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ እንደሆኑ፤ መንግሥታዊ ሃይማኖትም እንደማይኖርና መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ» ይገልጻል። ይህም ማለት በዲሞክራሲያዊ ርዕዮተ-ዓለምና ተግባራዊ ልምምድ መሠረት ሁለቱም አካላት የቆሙት ኅብረተሰብን ለማገልገል እስከሆነ ድረስ፣ የየራሳቸው የሥራ ድርሻና መመሪያ ይኑራቸው እንጂ በኅብረተሰቡ የሚደርሰው የፍትሕና የሰላም መጓደል እኔን አይመለከተኝም ማለት የሚቻል አይሆንም። ነገር ግን የተለያዩ ተቋሞች ቢሆኑም የሀገሪቱን ሕገ መንግሥት በማይጻረር መልኩ አብሮ መሥራትን የሚያጠቃልል ነው። ለምሳሌ:- የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በብሔራዊ ደረጃ እንደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ሆና ባለት ፖሊሲ መሠ ረት «በሁለመናዊ ወንጌል ሁለመናዊ ሰውን ማገልገል» ነው። ይህም ቤተ ክርስቲያኒቷ ዲያቆናዊት ቤተ ክርስቲያን መሆንዋን ያሳያል። ዲያቆናዊት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አምና የተቀበለችሁን የእውነት ወንጌልን ተግባራዊ ታደርጋለች። የእግዚአብሔርን መንግሥት ባሕርይ



በኅብረተሰቡ መካከል እውን ታደርጋለች። ይህ ደግሞ የሚተገበረው በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳዳራዊ አደረጃጀትም ሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ምእመናን በሁሉም ደረጃ በሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎ ነው።

ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል እየኖረች እንድትሠራ ክተፈለገ እግዚአብሔርን መምሰል ይኖርባታል። የፍትሕና የሰላም መጓደል በፖለቲካ ገዢዎች ላይ ብቻ የሚታይ ነው ወይስ በሌሎችም? ሁሉም ሰው እኩል ፍትሕና ሰላም አግኝቶ እየኖረ ነውን? ይህ ጉዳይ አጠያያቂ ሳይሆን አይቀርም። ሰው ሁሉ በነጻነት፣ በእኩልነትና፣ በሰላም ክብሩ ተጠብቆለት መኖር ይፈልጋል። ለሰው ልጅ ነጻነት ከምግብ፣ ከልብስ፣ ከሥራ፣ ከመጠለያና ካሰው ኅብረት ሁሉ በላይ ነው። ክብሩ ተጠብቆለት ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ፣ የማሰብ፣ የመናገር፣ በግፍ ወደ ማረሚያ ቤት ያለመጣል፣ የሃይማኖት ነጻነትን ማግኘት ይፈልጋል። እነዚህ ከእግዚአብሔር የተሰጡ ነጻነቶች ሲጓደሉ ቤተ ክርስቲያን በተመልካችነት ማለፍ የለባትም።

አብዛኛውን ጊዜ መንፈሳውያን ነን የምንል ሰዎች ፖለቲካን ከቤተ ክርስቲያን የራቁና ለየት ያሉ ሰዎች ብቻ የሚያከናውኑት ጉዳይ አድርገን እንገምታለን። ነገር ግን ፖለቲካ የማይመለከተው ግለሰብና ኅብረተሰብ በምድራችን የለም። የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ በአገር ዜግነቱ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብቶች እሉት። እንደዚሁም በአገር አስተዳደር ላይ ሐሳብ የመስጠት፣ ተሳትፎ የማድረግ ወይም የመካፈል ነጻነት ሊኖረው ይገባል። አንዲት አገር መልካም ዜጋን ለማፍራት እውነተኛና ያልተዛባ ለሕዝቦች እኩልትና ነጻነት የቆመ የፖለቲካ አመራር ያስፈልጋታል። ለዚህም ግብ መምታት እንደ እግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ መልካም አመራርና አስተዳደር መገንባትን ይጠይቃል። ይህ ደግሞ የሚሆነው በሕዝቡ ተሳትፎ ነው።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ፖለቲካንና ሃይማኖትን መለየት ካልቻ ለች ሊቸግራት ይችላል። ፖለቲካ ራሱን የቻለ ሳይንስ ሲሆን፣ ሃይማኖትም ራሱን የቻለ የእምነት መሠረትና መመሪያ አለው። ጆን እስቶት ስለ ፖለቲካና ቤተ ክርስቲያን ሲናገሩ«ፖለቲካ ማለት በሰፊው አነጋገር የአንድ ሀገር ሕይወት ኑሮና የዜግነት ኃላፊነትን ይመለከታል። ስለዚህም በኅብረተሰብ ውስጥ ያለንን ጠቅላላ ሕይወታችንን ያመለክታል።ፖለቲካ በኅብረት የመኖርን እውነት ያሳያል። በጠባብ አገላለጽ ፖለቲካ ማለት የአስተዳደር ሳይንስ ነው። ክልማትና ከፖሊሲዎች ጋርም ይቈጠራል። ስለሆነም ለማኅበራዊ ለውጥ ኃይል ማጠናከሪያ ነው» ብለዋል ።

እኛ ክርስቲያኖች ስለፖለቲካ ስናስብ ከጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና የሕይወት ምሳሌ መማር ያስፈልገናል። ኢየሱስ ሰማያዊውን መንግሥት በምድር ሲመሠርት የፖለቲካ አመራር ሲጨብጥ አልመጣም። የእርሱ መንግሥት ሁሉን ሰመግዛት የሚችል ሥልጣን አለው (ዳን. 4፣34-35፤ማቴ. 28፣18)። ይሁን እንጂ የኢየሱስ ጠቅላላው የምድር አገልግሎት ወደ ኅብረተሰብ ዘልቆ በመግባት ማንኛውንም ዓይነት የሕዝብ ችግር መካፈል ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ የፖለቲካ መሪ ባይሆንም፣ ከዓለም ፓለቲካ ርቆና በሰማይ ዙፋን ተቀምጦ የእግዚአብሔርን መንግሥት አልመሠረተም። ይልቁንም ለኅብረተሰብ የሚመቸውን ሁሉ በማድረግ በጊዜው ከነበሩት መሪዎች ጋር ፊት ለፊት እየተጋፈጠ ሕዝቡን ፍትሕና ሰላም በሌ ሰበት መንገድ ይመሩ የነበሩትን ሲቃወማቸው ነበር (ማቴ.23:1—30)።

የእርሱ ደቀ መዛሙርትም የዚህችን ዓለም ጨለማ እንዲያበሩ፣ መራራውን ኑሮ እንዲያጣፍጡ ብርሃንና ጨው ሆነው የእግዚአብሔ ርን ባሕርይ በዓለም ላይ በቃልና በተግባር እንዲያንጸባርቁ ታዝዘዋል። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰቡ ሁሰንተናዊ የኑሮ አቅጣጫ የሚታየውን መራራ ኑሮ ለማጣፈጥ፤ በፖሰቲካ መስክ ያሰውን የአገዛዝ ጨለማ ለማስወገድና የሰዎችን መንፈሳዊና ምድራዊ ኑሮ ለመለወጥ በሁሉም አንጻር ልታገለግል ከጌታዋ አደራ ተቀብላለች(ማቴ.5፣13-16)።

ክርስትና፣ የመጣውን ነገር ሁሉ አንገታችንን ደፍተን የምንቀበልበት ሳይሆን ክፉውን ከፉ መልካሙንም መልካም ነው ብለን የምንለይበት ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች በየግላቸው እንደ አንድ ሰማያዊና ምድራዊ ዜጋ በፖለቲካ ይሳተፋሉ። የመምረጥ፣ የመመረጥ፣ ሐሳብ የመስጠትና የመቀበል፤ የመተቸትና የመቃወምም ኃላፊነትም አለባቸው።

አንዳንዴም እግዚአብሔር በእንደዚህ ዓይነቱ ቦታ በክልልና በአገር ደረጃም ራሳቸውን የሰጡና እርሱን እየፈሩ ኅብረተሰብን እንዲያገለግሉ ታማኝ ልጆቹን ሲሾም ይችላል። ክርስቲያን በግሉ በፖለቲካ ጉዳይ አያገባኝም ማለት የለበትም። በአገር ዜግነት የአገሩ ጉዳይ ያገባዋል። ስለ አገሩ መናገር፣ መጻፍ፣ ስብሰባዎች ላይ ተገኝቶ ገንቢ ሐሳብ መስጠት፣ ስችግረኞችና ለተጠቁት መቆም፣ ሰሕዝቡ ሰላም፤ ፍትሕና እኩልነት ማስብና መሥራት፣ ከራሱም



የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ማድረግ ይርኖበታል። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረም የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር መስጠት ይጠበቅበታል (ማቴ.22፣15-22፤ 17፣24-27)። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ግብር ገብሮአል። ከዚህም በምድራዊው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባሮች ውስጥ መካፈሉን እንመለከታለን።

ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካን ነገር በጦር መሣሪያ አትፈታም። በትምህርትዋ በኑሮዋ የተበላሸውን የዓለም ታሪክ የምትቀይርበት የእግዚአብሔር ኃይል በእጅዋ አለ። ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምናየው እንደነማርቲን ሉተር ያሉ የቤተ ክርስቲያን አዳሾች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተበላሹ አሠራሮችን በትምህርታቸው ተቃውሞ እያሰሙ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ችለዋል። አሁንም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቂ እውቀት ያላቸው የለውጥ ፈር ቀዳጅ ዲያቆናት ያስፈልጉናል።

ስለዚህ ምዕመናን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ዲያቆናዊት ቤተ ክርስቲያንን እውን ለማድረግ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮሚያዊና መንፈሳዊ ዘርፎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ብቁ ተሳትፎ የማድረግ መስኮታዊ ኃላፊነት መኖራቸውን በአንክሮ መገንዘብ ያስፈልጋል።

በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በመንግሥት ቢሮዎች ግፍና በደል የተ ፈጸመባቸው ችግረኞች የሚያሰሙት የጩኸት ድምፅ ሲኖር ይችላል። ለምሳሌ፡- ከፖለቲካ አመለካከትና ርዕዮተ-ዓለም የተነሣ የሚሰደዱ፣ የሚታሰሩ፣ ከድህነትና ከበሽታ የተነሣ የጎዳና ተዳደሪዎችና አረጋውያን የመሳሰሉ የተረሱና የተጣሉ፤ መማር ሲችሉ የትምህርት ዕድል የተነፈገባቸው፣ የደመወዝና የሥራ እድገት ያጡ፣ በህብታሞች ጉልበታቸው የሚበዘበዝ ሠራተኞች፣ እኩል ተፈጥረው በዝቅተኛ ዓይን የሚታዩ፣ ከጾታና ከዕድሜ የተነሣ ልዩነት የሚደረግባቸው አንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሲኖሩ ይችላሉ። ከመልካም አስተ ዳደርና አመራር ጉድለት የተነሣ የሕዝቦችና የተፈጥሮ ጥሪት (ሀብት) መጎሳቆልና ለድህነት መሠረታዊ ምክንያት መሆን የመሳሰሉ ጉዳዮችን በብርቱ መከታተልና ማስተካከያ እንዲደረግ ድምፅ ማሰማት ያስፈልጋል። እነዚህንና ሌሎችንም ድርጊቶች አይቶ መናገር ወንጀል ነውን? አይደለም። ይልቁስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማገልገል ነው። ሰዎች ከእኔነት ተላቅቆ ሰርስ በርሳቸው የሚሻለውን ነገር እንዲያስቡና እንዲያደርጉ መልካም ግብረገብ እንዲሰፍን የሚያበረታታ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን «ሰዎች ሲያድርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ

እናንተ ደግሞ አድርጉላቸው (ማቴ. 7፣12) ይላል።

ይህ መስኮታዊ ቃል የገባት አንዲት እኅት ሰዓደኛዋ ያደረገችላትን የሚመለከት ምስክርነት እናንብብ ።
በአዲስ አበባ ከተማ ሁለት ምስኪን ቤተሰቦች በአንድ አካባቢ ይኖሩ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ለጽዳት ሥራ ማስታወቂያ ወጣና ሁለቱም ተወዳደሩ። ከሁለቱ ሰቶች መካከል ባልዋ የጥበቃ ሥራ የነበረው ሰው ውድድሩን አለፈች። ውድድሩን ያላለፈችው ጓደኛዋ ግን እርስዋም ሆነች ባልዋ ምንም ዓይነት ሥራ የሌላቸው ነበሩ። ይህች ያለፈች እኅት ወዳወዳደራት አስተዳዳሪ ሄዳ «እኔና ጓደኛዬ ተወዳድረን ነበር፣ ነገር ግን እርስዋ ልታልፍ አልቻለችም። እኔ ከእርስዋ የተሻለ ኑሮ ስላለኝ፣ እባክዎን በእኔ ቦታ በዚህ ጽዳት ሥራ እርስዋ ገብታ እንድትሠራ ያድርጉአት እንደ እኔው ጎበዝ ናት» በማለት ስምና እርስዋ ባለፈችበት መሥሪያ ቤት አስቀጠረቻት።

ልክ እንደዚህች ሴት ለማድረግ ራስን የሚያስክድ ለውጥ በሕይወታችን መታየት አለበት። አለበለዚያ መንፈሳዊያን ነን እያልን ለችግረኛውና ከእኛ ለባሰው በልንጀራችን የማናስብ እንሆናለን። ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ «ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁ ለእኔ አደረጋችሁት » የሚለውን ምሳሌ በመጠቀም ላጡ፣ ለተራቡ፣ ለታሠሩና በልዩ ልዩ መከራ ውስጥ ለሚገኙ እግዚአብሔር ከሰጠን ነገር እንድናካፍላቸው ይናገራል (ማቴ. 25፣35)።

ከዚህ በፊት የተለመደው የሀገር ውስጥ ዜጎች ሲቸገሩና ሲራቡ ከእርስበርስ በሚገኘው በሀገር ውስጥ ጥሪት ሀብት መረዳዳት ሳይሆን ከባሕር ማዶ ወገኖች በሚሰጠው ልግስና ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው። ቤተ ክርስቲያንም ከዚህ ልምድ ውጪ መሆን አልቻለችም። ነገር ግን የዲቁና ትምህርት ቤተክርስቲያን ከዚህ አስተሳሰብ ወጣ ብላ አባሎችዋን ለሌሎች የሚተርፉ እንዲሆኑ ማዘጋጀት እንድትችል የሚያደርግ አገልግሎት ነው። ይህን ማድረግ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቷ ዓለም አቀፋዊውን ዲቁና አገልግሎት ትቃወማለች ማለት ሳይሆን መሠረታዊ የሆነ ምዕመናናዊ ድቁናን በተቀነባበረ ሁኔታ ማደራጀትን ያመላክታል ። እኛ ደግሞ ብዙ ሀብትና ንብረት ባይኖረንም የሌሎችን እጅ ከመጠበቅ ይልቅ ያለችንን ማካፈል ስንጀምር እግዚአብሔር ይባርከናል።

እንግዲህ ዲቁና በማካፈል የሚባዛ አገልግሎት ነው። ተባዝቶ ደግሞ ለብዙዎች የሚተርፍና ሌሎችን የሚለውጥ የለውጥ



አገልግሎት ነው። አምላካችን እግዚአብሔር አዲስ ነገርን የሚያደርግ የለውጥ አምላክ ነውና።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ቃላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም ስጥ።
   ሀ/ ፍትህ ለ/ ሠላም ሐ/ እኩልነት መ/ ዕርቅ
2. ሰብአዊ መብቶች ማለት ምን ማለት ነው? መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውነቶችን ግለጽ።
3. የማኅበረ ምዕመናን ዲቁና አገልግሎት ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ ለመሆን ምን ማድረግ አለባት ትላለህ?
4. በቤተ ክርስቲያን የነቢይነት ዲቁና አገልግሎት (Prophetic Diakonia) እና የፖለቲከ አስተዳደር ምንነትና ግንኙነት እንዲሁም ልዩነት ግለጽ።
5. ቤተ ክርስቲያን ባንድ ሀገር የፖለቲከ ጉዳዮች ውስጥ በምን መልኩ መሳተፍ ይኖርባታል? ገደቡስ እስከ ምን ድረስ ነው ብለህ ታስባለህ?
6. ባጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰቧ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲከዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ውስጥ ተቀዳሚ ድርሻዋ ምን ምን እንደሆነ ዘርዝር። ምዕመናን ድርሻቸውን እንዳይወጡ የሚያደርጉ ተግዳሮቶች ካሉ ጥቀስ። መፍትሔዎቻቸውስ?

# ዋቢ መጻሕፍት


1. Alemu Ermias, The Attitude Towards work among Evangelical Christians with the reference to Kambata Church, MYTS, Addis Ababa, May 15, 2000Miller L.
2. Africa Advocacy Public Policy Newsletter, Issue 7, USA, January 2003Royokas
3. Byrne Tomy, Working for Justice and Peace, Practical guide, NDOLA, Zambia, 1998
4. Collins R. Cary, Christian Counseling by Word Incorporated, USA, 1973
5. Coppes J. Leonard, Report of the Committee to Study the Principles of Diaconal Ministry (A paper from the Minutes of the Fifty-first General Assembly (1984) and presented to the 48th General Assembly, 1987.
6. Darrow, Discipline Nations, The power of Truth to Transform Cultures, USA, YWAM Publishing, 1984
7. Dictionary of Ecumenical Movement, Great Britain, 1991
8. Edward K. Perry, Deaconos a biblical theological sketch, New York: USA, 1979
9. Eerdmans Brill, The Encyclopedia of Christianity (Vol.1)
10. Elwell Walter, A.Baker, Theological Dictionary of the Bible, Grand Rapids, Baker, 1996
11. Hunter J. Rodney, Dictionary of Pastoral Care and counseling, Abingdom press, 1990
12. Kerston Perry Edard, A biblical theological and Practice Sketch, Upper New York Synod, 1976
13. Nicholas Lossky (Editor), Dictionary of the





Ecumenical Movement, Great Britain, 1991

14. Report of the Committee to Study the Principles of Diaconal Ministry (From the minutes of the Fifty-first General Assembly (1994, pp.135-167), Submitted by Leonard J. Coppes, 2005
15. Riikka and Kiessling Klaus, Spititus Lux. Caritas, International Congress in Deacony, Lahti, Finland, Lahden Diaconal
Institution of Lahti, 1999
16. Stott John, Issues Facing Christians Today, London, 1990
17. Tony Byrne, C.S.SP. Working for Justice and peace, A Practical guide, NDOLA: Zambia, 1988
18. Walter Elmwell, Evangelical Dictionary of Theology, USA: 1989
19. ---------------------, DIAKONIA Towards Christian Service for our Time (Useful information for church workers in Africa), The Africa Desk of the World Council of Churches commission on Inter-Church Aid, Refugee and World Service, Geneva: Switzerland, Dec., 1990
20. ------------------------, LWF Report, Prophetic Diakonia: "For the Healing of the World" Johannesburg, South Africa, November 2002
21. ------------------, Lutheran Encyclopedia, Concordia Publishing House, 1975.
22. ------------------, New Catholic encyclopedia, USA,

Vol. 3,4,8, 1967

23. ------------------, ዲቁና ምንድንነው? የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መከነ ኢየሱስ፤ ወንጌል ክፍል አ.አ. 1980 (ትርጉም)

24. አወል አብዱሩህማን፤ ኢ.ስ 1994 (ቃለ መጠይቅ)

25. ንጽረተ-ዓለም እና እድገር ድህነትን ለመቀየር የእውነት ኃይል፤ አ.አ. 1993

26. ዮሐንስ ሳንድቬድ፤ የጥንንትዋ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ መክነ ኢየሱስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ አ.አ. 1980

27. የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መከነ ኢየሱስ አስተ ዳደር ጉባዔ ጽሑፍ፤ አ.አ. ግንቦት 1964

28. የሴቶች መብት፤ የኢ.ወ.ቤ.ክ.መ.ኢ. ሠላም ቢሮ፤ አ.አ. 1993

29. የሴቶች መብት፤(ያልታተመ ጽሑፍ)፤ አዲስ አበባ፤1993 ዓ.ም

30. ዲሞክራሲ ምንድን ነው? የኢ.ወ.ቤ.ክ.መ.ኢ. የሠላም ቢሮ፤አዲስ አበባ፤19---ዓ.ም

31. ቄስ/ ዶር. እሸቱ አባተ፤ ዲቁና /የፍቅር አገልግሎት/ (ያልታተ መ ጽሑፍ)፤ አዲስ አበባ፤ (ቀን---)

32. ------------------, ዲቁና ምንድን ነው? የኢ.ወ.ቤ.ክ.መ.ኢ. ወንጌል ክፍል የተዘጋጀ፤ አዲስ አበባ፤ 1980 ዓ.ም